# 24

ተጫንቀውና ተጫምቀው፤ እስትንፋሳቸውን፣ ስሜታቸውንና አከላታቸውን ተወራርሰው፤ በፍቅር ሀይል የእርካታና የደስታ ድካም አዝሏቸው እንደተቃቀፉ በሰመመን ወድቀዋል::

ቀድሟት ነቃና የግራ ክንዱን እንዳንተራሳት ከአንገቱ ቀና ብሎ ቁልቁል አስተዋላት:: ያለምንም ሲጋት ክንዱ ላይ ካሸለበ ገጽታዋ ፍቅር፣ ውበትና እምነትን አነበበ:: ግንባሯን ሳም አደረገና ዘወትር ይህን በመሰለ ውሎአቸው እንደሚያደርገው በቀኝ እጁ ጣቶች ሚዶ ሠርቶ የተበተነን ፀጉሯን ቀስ አድርጐ መላግ ያዘ:: ባለፈው ሰሞን አሉባልታ ሰምቶ ራሱን ሲረብሽ መስንበቱን በቁጭት አስታወሰና ሀብቴንም ሳቢንም በልቡ ረገማቸው::

“እባቦች! የተንኮል መርዛቸውን ረጭተው ሊያለያዩን ነበር . . . እኔኮ እሚገርመኝ በመፋቀራችን የሚያጡት በመጣላታችን የሚያገኙት ጥቅም አለ?” አለ የሀሳብ ድምጹን ከረርና መረር አድርጐ:: “ውሸታሞች! ውሸታሞች ናቸው::” ብሎ ለመደምደም ሞከረ:: -ህሳቡን::

በዚህ አቋሙ ላይ ግን የህሊና ቅሪት ሆኖ የተደበቀ ጥርጣሬው ጣልቃ እየገባ ረበሸውና እንደገና ትኩር ብሎ ተመለከታት:: አንዳች የክህደት፣ የጥላቻና የተንኮል ምልክት ያገኝ ይመስል::

‘ሰው ልቡን ይመስላል? እንዲያ ቢሆን ምንኛ ደግ ነበር:: ሰው ልቡን አይመስልም እንጂ ቢመስልማ ጥርጣሬ እሚሉት የእምነት ፀር ጠፍቶ ከልብ የቋጠሩት ጥሩና መጥፎ ከግንባር ላይ በግልጽ ይነበብ ነበር:: የእርሱም ህሊና ወይ እምነትን ወይ ክህደትን ከገጿ ላይ አንብቦ በአንድ አቋሙ ይፀና ነበር::’ ለማንኛውም ትኩረትን እንደሚሻ ጥልቅ የቅኔ ሰንኝ ደግሞ ደጋግሞ አነበባት::

“ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ጊዜ ያፈቀርኩት አንተን ነው” የምትል መሰለው:: ገና ሲገናኙና ከዚያም በኋላ በየአጋጣሚው ስትለው ስተዘምረው የቆየችው ቃሏ ነው::



መጀመሪያዋን ሌላው ቢቀር ጠብቃ ባቆየችው እና በፈቃደኝነት ባስረከበችው የተፈጥሮ ክብሯ አረጋግጠላታል:: መጨረሻዋስ? . .በማመንታት ሞንቅላቱን ወደ ትከሻው ዘንበል ቀና እያደረገ የማያውቀው የፍቅር ባላንጣውን አስታወሰ:: ቀይ ይሁን ጥቁር የማያውቀው የትንሳኤ ዘገባኤ ማተሚያ ቤት ሠራተኛ:: እናም በሀሳቡ የገመተውን ምስል ሰጥቶት ከዳርምየለሽ ጋር ያላቸውን ታሪክ ሠራው::

‘ጅላጅል መላይ ሰው ነው:: እሱ እንኳን ከውጭ እንጂ ውስጡን በማያውቀው የነዳርምየለሽ ቤት በምግብ አሳብቦ ወጣ ገባ እያለ ሲቃለዳት:: ከዚያ ቤቱ ጭር ሲል በተፈጠረው አጋጣሚ ተጠቅሞ ሲዳራትና ሲላፋት:: . . ተያይዘው እንደዋዛ ከአልጋ ሲወድቁ ወይንም ደግሞ በቁማቸው . . .’

“ሺት!” አለና ሳይታወቀው ተበሳጭቶ እጁን አወራጨ::

“እንድሽ ምን ነካህ?” አለችው አንገቷን ያንተራሳት እጁን ሲፈንቅል በድንጋጤ ከወደቀችበት ሰመመን ነቅታ::

በህሊናው በቀረፀው ሀሳብ ሳቢያ ሳይታወቀው መሳሳቱ እራሱንም ስላስደነገጠው አፉን ዘግቶ ቀረ::

ዳርምየለሽ የፊቱን መለዋወጥ አስተውላ ምን እንደነካው ደጋግማ ጠየቀችው:: ሊነግራት አልቻለም:: ምን ብሎ? አድሮበት ስለነበረው ጥርጣሬና ቅናት እንደሁ ማክሰኞ ዕለት በሩቂያ አማካኝነት እንደተገናኙ እያለቀሰች ምክንያቷን ስትነግረው ተቀብሏታል:: በጠና ታማ መስንበቷን፤ ቀጠሮ እየሰጠ ችው የቀረችበት ምክንያትም እንደምንም ልታገኘውና ልታየው ጉጉትና ናፍቆት እያደረባት ነገር ግን ለመውጣት ስትሞክር ባለመቻሏ እንደሆነ ሌላም ሌላም::

እንዲያ ስቅስቅ ብላ እያለቀሰች ስትናገር እርሱ በጥያቄና መልስ እያዋከበ እንደሌላው ጊዜ ፖሊሳዊ ማጣራት ለማድረግ በፍቅር የለዘበ አንጀቱ አልቻለለትም:: እንደ ብርቱ ዝናብ ጉንጮቿን የረገጠው የእንባ ዶፍ በልቡ ከሚፈሰው ፍቅራዊ ፏፏቴ ስሜት ጋር ተቀላቅሎ የፈጠረበት የእምነት ጐርፍ በውስጡ ሲያቆጠቁጥ የነበረውን ጥርጣሬ ጠራረገበት:: ይልቁንም የእርሱም እንባ ተንቆርዞ እያባበለና እያጽናና ነበር ወደቤቷ የሸኛት::

ከዚያ በኋላ ራሱ በተጨባጭ እስካላጋጠመው ዳግመኛ የሰው ወሬ ላይሰማና ያለፈውንም ከሆዱ አውጥቶ እንዳፈቀራት ሊቀጥል ወሰኗል:: አሁንም ከተጋደመችበት ቀና ብላ ክንዶቿን በአንገቱ ዙሪያ ስትጠመጥም ስውር ሀሳቡ ሸሽቶ ከህሊናው ጀርባ ተደበቀ:: ሙሉ ደረቱን አስጠግቶላት ክንዶቹን በብብቶቿ ሥር አሳለፈና ጀርባዋን እያሻሸ ፀጉሯን በጣቶቹ እየላገ ሲገናኙ

ጀምሮ ያሳለፏቸውን ጥሩ ጥሩ የፍቅር ጊዜያት በስመመን ጠራቻው::

ለጋዜጣው ዝግጅት ክፍል የተለያዩ መጣጥፎችን በማቅረብ ባደረገው ጥረት ከፍሪላንስ ሠራተኛነት ወደ ኮንትራት ቅጥር በተዛወረ ሰሞን ነበር:: አንድ ቀን እሱና ሀብቴ ዝናቡ ከሥራ በኋላ አብረው ወዲያ ወዲህ ሲሉ የከሰዓቱን ፈረቃ ጨርሶ በየአቅጣጫው ከሚተምመው የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪ መሀል ወገቧ ላይ ደርሶ ጫፉን እንደዋዛ በብር ላስቲክ ሸብ ያደረገችው ረዥምና ጥቁረቱ ማራኪ ፀጉሯ ካይኑ ገባ:: በፀጉሯ የተያዘው ዓይኑ እጥር ብሎ ወገብ ከዳሌ፣ ባት ከተረከዝ፣ ትከሻ ከደረት ለይቶ ክፍልፍል ያለ ትክለ ሰውነቷን በአድናቆት ፈዞ አስተዋለው:: መደበቅ ስላልቻለ ለሀብቴም አሳየውና አድናቆቱን ተጋሩ::

"እንልከፋት" አለው ሀብቴ አስፋልቱን አቋርጣ በቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን በኩል ወደ ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ አቅጣጫ ስትይዝ ወደ እርሷም እያፏጨ:: እርሱ ግን በሴት ጉዳይ ላይ የልቡን ወኔ ስለሚያውቀው ፍላጐቱ ቢኖረውም በዓይኑ ብቻ ተከተላት::

"ቦካህ እንዴ? ምነው ዝም አልክ እየራቀች እኮ ነው::" አለ ሀብቴ::
"ምን ልበል ታዲያ! አላንቃት::"
"እንልከፋት አልኩህኮ"
"ምን ብለን ነው የምንለክፋት? እንደ ዱርዬ በመንገድ ያየነውን ሁሉ መልከፍ ደስ አይልም::" አለ እንዳለ ይሉኝታና ፍርሀት ተጭኖት::
"እኬ! ምን ብለን እንደምንለክፋት አሳይሃለሁ::" አለና በቆመበት ትቶት እያፏጨ ተከተላት:: -ሀብቴ::

እንዳለ ምን እንደሚባባሉ ባይሰማውም ፈንጠር ብሎ ይመለከታቸው ነበር:: እንዳልተግባቡ ያስታውቅ ነበር:: በመሀል ወደ እርሱ ሰረቅ አድርጋ ስታይ ያደረበትን ድንጋጤና መሸበር እስከመቼም አይረሳው::

"ጋግርታም ጨጨፆ ናት!" አለ ሀብቴ መንጭቃ ካመለጠችው በኋላ በቁጭት እየተመለሰ::
"እኤምኮ ነገርኩህ:: ሳታውቃት ሳታውቅህ ምን ብላ ትቀርብሃለች? ልጅቷ ደግሞ ከሁኔታዋ ገና ምንም የማታውቅ የቤት ልጅ ትመስላለች::" አለ እንዳለ::
"እሱ እንኳን የወጣላት የተቃጠለች ጭስ ናት:: ታስታውቃለች::" አለ ሀብቴ::
"አትመስለኝም:: እንደዚያ ብትሆን ኖሮ እንኳን ተከትለሃት ልትኮላተር በፉጨትህ ትቆም ነበር:: እንደዛ ከማመናጨቅም ይልቅ በምላሷ አቅልጣህ ነበር የምትሄደው:: ይቺ ግን ር̣ግጠኛ ነኝ ሌላው ቀርቶ ወንድ በፍቅር ጨብጧት



አያውቅም::" አለ ረዥም ጊዜ እንደሚያውቃት ሁሉ::
"አላወቅካትም:: ስትሪክት የሆነችው ራሷን ልታስወድድ ነው::" አለ ሀብቴ እያጥላላ::
"አሁንማ በቃ ተዋት:: ስትሪክትም ሆነች ስትሬት እምቢታዋን አሳይታህ ሄደች" እንዳለ ማጣጣሉ ከማጣት የመጣ 'ሲያጡ መጥላት' መሆኑ ስለገባው ከልቡ በሸቆ::
"እኔማ ቅድሙንም አንተ ፈልገሃት መልከፍ ስለፈራህ ላቀላጥፍህ እንጂ ለራሴ የምፈልጋት ዓይነት አይደለችም" አለው ሀብቴ::
"እሱን እንኳን ተወው:: ምንም የሚወጣላት አይደለችም:: ዞሮ ዞሮ ለሁለታችንም ሳትሆን ሄዳለች:: እርሳት::"

እንዳለ ከሀብቴ ፊት 'እርሳት' ብሎ ግዴለሽ ቢመስልም እንደ አፉ ሁሉ ልቡ በቀላሉ አልረሳለትም:: ለሊቱን ሲያስባት አደረ:: በማግስቱም ቀኑ አልገፋ ብሎት ሲቀመጥ ሲነሳ ዋለና ከሥራ እንደወጣ ወደ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ብቻውን አመራ:: ከትምህርት ቤት እስክትለቀቅ ወዲያና ወዲህ እየተንቆራጠጠ ጠበቃት:: ስትመጣ ግን ሊያናግራት አልደፈረም:: ሠረቅ አድርጋ ስታየው ልቡ እየተንተረተረ ግንባሩን አስመትቶ በዓይኑ ሸኛት:: ከዚያ በኋላ በየቀኑ ሳይሰለች ጠበቃት:: ሳያናግራት::

በመሥሪያ ቤቱ ታዝዞ ለአንድ ሳምንት ክፍለ ሀገር ሲሄድ ፍቅርና ትዝታን ከተጋራት የረዥም ጊዜ ፍቅረኛው እንደተለየ ሁሉ ቅር ቅር እያለው ነበር:: ሥራውን እየተጣደፈ ጨረሰና በናፍቆት ተወጥሮ ተመለሰ::

በተለመደው ቦታና ሰዓት ዓይኖቹን እያቅለበለበ ሲጠብቃት በሚያውቀው ርጋታና የፊት መኮሳተር መጣች:: ድንገት ስታየው የደስታ ከሚመስል ድንጋጤ ጋር ያሳየችው ፈገግታ ድፍረት ሰጠውና በሰላምታ ቀረባት:: -ተቀራረቡ::

ከዚያ ወዲህ አብረው ያሳለፏቸው የፍቅር ቀናት ወራትና ዓመታት አንዱ የአንዱን ድምር እያሰረና እየቀመረ ከማለፉ በቀር እንደ ብረት በጠነከረ እምነትና መተሳሰብ የገነቡትን የፍቅር አጥር የነቀነቀ መቃቃር ቢኖር የሰሞኑ ብቻ ነው::

አንገት ለአንገት ተያይዘው ከተመለከቷቸው የፍቅር ሲኒማና ቲአትሮች፤ ተጋርተው ካነበቧቸው ልቦለዶችና ካደመጧቸው ሙዚቃዎች ጥሩ ጥሩውን ሁሉ በራሳቸው እየመሰሉ ጣፋጭና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አይጠገብ የፍቅር ህይወት ነው ያሳለፉት::

አልፎ አልፎ በአነጋገርና በሀሳብ አለመጣጣም ቢጋጩም ኩርፊያቸው

እንደ እናትና ልጅ ካፍንጫቸው አያልፍም:: በማግስቱ ተፈላልገው ሲገናኙ ያለፈው ግጭታቸው ለዕለቱ መሳሳቂያና የጨዋታ መክፈቻ ከሚሆናቸው በስተቀር ቂም አሳድረው አያውቁም::

"ለምንድነው ግን ህብቴ ሲጀመር ጀምሮ ስለዳርምየለሽ ጥሩ ነገር የማያወራው!" አለና አለበ ወደ ኋላ ተመልሶ የራሱንና የዳርም የለሽን የፍቅር ጉዞ እየገመገመ የቆየው ሀሳቡ አሁን ላይ ሲደርስ:: ለስሞኑ የእርሱ ሆድ መሻከር የህብቴና በእርሱም አማካኝነት የላቢ ጋይድ ሚና ጐልቶ እየታየው:: ዳርምየለሽም ብትሆን ለህብቴ ያላትን ጥላቻ እንደዋዛ ቢሆንም ደጋግማ ነግራዋለች::

"እንዲሁ ሳየው ያስጠላኛል" ትለዋለች:: ለምን እንደምትጠላው ጠበቅ አርጐ ሲጠይቃት:: ለዚህም ነው ልቡ በእርሷ ላይ ቅሬታን ባዘለበት በነዚያ ቀናት ምናልባት የጠላችው ስለእርሷ የሚያውቀው ሚስጥር ቢኖር ነው የሚል ግምት ያደረበት:: ሁለቱም በእርሱ ምክንያት ሲገናኙ የሰላምታ ልውውጣቸው ጥላቻቸውን የሚያንፀባርቅ እይደለም:: በተለይ ህብቴ በንጹህ ስሜት የሚያናግራት ለመምሰል ይሞክራል:: ታዲያ . . .

ጉንጭ ለጉንጭ ተሳልፈው እንደተቃቀፉ ትከሻው ላይ ያዋለችው አገጯን ሳብ አድርጋ ከናፍሯ እየተንቀጠቀጡ ፍዝዝና ቅዝዝ ብላ አስተዋለችው:: ደጋግሞ መጠጣት እና በንጹህ ስሜት ቃላትን መለዋወጥ ጀመሩ::

"እንድሽዬ፣ መቼ ነው የእኔ ቤተሰቦች አውቀውህ ለትዳር የምንበቃው?"

"ካሁን በፊት ተነጋግረን ወስነንበት የለም እንዴ?" አለ ቅንድቦቿን በአመልካች ጣቱ እየኳለ::

ከአባቱና ታናሽ እህቱ ጋር ከሚኖርበት ጠባብ ቤት ወጥቶ ለራሱ የሚሆን ቤት እስከሚከራይ፤ እርሷም ትምህርቷን በከፍተኛ ደረጃ እስክትከታተል:: አለበለዚያም ውሎ መግቢያ የሚሆን ሥራ እስከምታገኝ በትዕግሥት ሊጠባበቁ ተስማምተው ነበር::

"ቢሆንም ሁለታችን ከተስማማን ውሳኔአችንን ማሻሻል እንችላለንኮ" አለችው::

"ለምን? እንዴት አድርገን ማሻሻል እንችላለን? በአሁኑ ጊዜ የቤት ኪራይ ለማግኘት ያለውን ችግር ታውቂዋለሽ:: ነው ወይስ እዚያች እግር ከራስ ሆነን እምንኖርባት የአባቴ ቤት ሌላ ቤተሰብ መስርቼ በስተርጅና ማረፊያውን ልቀማው?"

"እኔ እንደሱ አላልኩም"



"ታዲያ ሌላ ምን አማራጭ አለን?"

"ለምን ደባልም ቢሆን አንገባም? ለእኔና ለአንተ አንድ ክፍል ቤት ትበቃናለች:: ዋናው ፍቅሩ ነው:: 'ፍቅር ካለ አንድ ቂጣ ለዘጠኝ ያጠግባል' ይባል የለም? በደባል ተከራይተው አንድ አልጋ በምታክል ክፍል የሚኖሩ ብዙ ባልና ሚስት አውቃለሁ::"

"ግን ምን ያህል ተደስተው ወይንም ተማርረው እንደሚኖሩ ታውቂአለሽ? ከቤት ቤት ሲባረሩና ሲሳደዱ ሁልጊዜ አዲስ እየሆነ በማይሞቅ ጎጆአቸው ተሰላችተው የተጋቡብትን ቀን እንደረገሙና እንዳጥላሉ የሚኖሩ፤ የኑሮ ምሬታቸውና ችግራቸው ፍቅራቸውን አቀዝቅዞት እስከመፋታት የደረሱም ብዙ ናቸው:: እኛማ ቀድሞ ነገር ቤቱስ ቢገኝ ማንኪያና ሹካ እንኳን የሌለን ባዶ እጅና እግሮች አንድ ቤት ገብተን የምንመሠርተው ትዳር አይታየኝም:: ትዳር ማለት ቤትና ፍቅር ብቻ አይደለም::"

"ሌላ ምን ያስፈልጋል? ገንዘብ እንደሆነ ለጊዜው አንተ የምታገኘው ደሞዝ ባያንደላቅቅ ጉሮሮአችንን ለመክደን ሳይበቃን አይቀርም::"

"አይበቃንም ዳርም:: አንደኛ ነገር ምንም እንኳን ሠርቶና ውሎ ለመግባት መፍጨርጨሩን ባያቆም ወደ ዕድሜው ጣሪያ የሚገሰግስ አባትና ከጥገኝነት ያልተላቀቀች እህት እንዳሉኝ አትርሺ:: የእኔን ርዳታና ድጎማ ይፈልጋሉ:: ሁለተኛ ነገር ደግሞ እነርሱ እንኳን ባይኖሩብኝ በአሁኑ ወቅት የቤት ዕቃ አሟልቼ ጐጆ ለመውጣት አልተዘጋጀሁም:: ሌላው ቢቀር የሴት መሶብና ማቡኪያ፣ የመኝታ አልጋ፣ እንደዚ እንደዚ የመሳሰሉትን መሠረታዊ ጐጆ መውጫዎች መያዝ ያስፈልገናል:: ለዚያውም ቤተሰብሽ ያለሰርግ ለመዳር ፈቃደኛ ቢሆኑ ነው:: ካሁን ቀደም እንደነገርሽኝ ከሆነ በተለይ እናትሽ ድል ባለ ሠርግ ዓለማቸውን ማየት ይፈልጋሉ:: የኔ አባት እንኳን የባሰበት ድሃ በመሆኑ የአቅሙን ክልል ያውቀዋል::"

"እንድሽ፣ ለራስህ ክብዶ የታየህን በእነሱ ፍላጐትና ምኞት አታላብብ:: እኔና አንተ ከተስማማን እነሱን አይመለከታቸውም::"

"እንዴት አይመለከታቸውም? ይመለከታቸዋል እንጂ:: ያለ ሁለቱም ወላጆች እምነትና ድጋፍ ትዳርን መመሥረት ድስትን በሁለት ጉልቻ የመጣድ ያህል ያስቸግራል:: ትዳር ሦስት ጉልቻ ነው ሲባል አንዱ ጉልቻ የቤተሰብ ድርሻ ነው:: ቤተሰብ ያልደገፈው ትዳር ሁለት ጉልቻ እንደማለት ነው:: በሁለት ጉልቻ የተጣደ ደግሞ ካንድ በኩል ዘንበል ማለቱ አይቀርም:: ተደላድሎ እንዲቀመጥ ሦስተኛው ጒኖር አለበት::"

"በቃ ተወው:: እኔ ይኼን ሁሉ እንድትናገር አልነበረም" አለችና በቅሬታ አቋረጠችው::

"አንቺ ግን ዛሬ ምን አሳሰበሽ?" አላት ከጥቂት ዝምታ በኋላ ነገሩ ከንክኖት::

"እንዲሁ ነዋ! እንዴት ምን አሳሰበሽ?"

"አይ እንዳው ተነጋግረን የቆረጥንበትን ጉዳይ ሳይታሰብ እንዳዲስ

## 25

"ይኼ ሰውዬ እንዴት ነው እዚህ ቤት ሸር ጉድ አበዛሳ!?" አለች እናቷ ስለ ፈጠነ ውሎታ እንስተው ጥሩ ሰውነቱን ሲያዳንቁ ከአፋቸው ተቀብላ:: ሁለቱ እህቶቿን ጨምሮ ራት እየበሉ ነው:: "ደርሶ ቤተኛ የሆነበት ምክንያት አልገባኝም::"

"ምን አጠፋ ዳርምየለሽ? ባንቺ መታመም ምክንያት ከላይ ከታች እንደልጅ ስልከውና ሳሮጠው የሰነበትኩት እኔ ነኝ:: ሌላውን ትተሽ ዛሬ የታረደችውን ፍየል እንኳን መራቤቴ ድረስ ተሯሩጦና አላልኮ ያስመጣልኝ እሱ ነው::"

"አዲስ አበባ ፍየል ጠፍቶ ነው መራቤቴ ድረስ የተፈለገው?" አለች ዳርምየለሽ ነገሩ እያሳቃት:: ዛሬ፣ ገና ከዋለችበት ስትመጣ ጀምሮ ፊቷ ፈካ ብሎ ስለነበር ሁሉም ያሁኑን ሳቋን የተቀበሉት በያዝልቅልሽ ዓይነት ስሜት ነው:: ወይዘሮ ብዙ በተለይ እንደ ሰሞኑ ፈርተው ሳይሆን ዘና ብለው ነው የሚያናግሯት::

"መች እንደሱ ሆነና ልጄ፤ ማንኛውም ፍየልማ እዚሁ ሞልቷል:: የተፈለገችው ግን ያልተጠቃች ቀይ ፍየል ነበረች:: 'ቢቸግረኝ . . .' ምን አለች ነው የሚባለው ሴትዮዋ:: እኔማ አንቺ የዳንሽልኝ መስሎኝ እንጂ . . ."

"ምነው በቀደም ተነጋግረን የለም እንዴ? ዶሮውን አርዳችሁ የጣላችሁ ዕለት ሰዎቹ ከወጡ በኋላ አለመታመሜንና እንደዚያ ያለ አጉል እምነት አስፈላጊ እንዳልሆነ ነግሬሽ የለም?"

"እሱስ ነግረሽኛል" አሉ ዶሮ ያረዱ ዕለት ሳይሆን ማክሰኞ ማታ ያነሳችባቸውን ጥያቄ ይበልጥ እያስታወሱ:: "እኔ እንዲያው ፈልግልኝ ያልኩት ከዚያ በፊት በመሆኑ ካደከምኩት ብዬ እንጂ:: የሰው ውለታ መቼም ይከብዳል::"

"አላስፈላጊ ውለታ ነው"

"ቢሆንም፣ መቼም ግዴታ የለበት:: እንዲያው እግዚአብሔር የመረቀው ሆኖ እንጂ በሰው ጦስ፣ በሰው ጣጣ ማን ይገባል ልጄ? ሆነሽም አልሆንሽም ትልቅ ውለታ ነው የጣለብኝ::" አሉ ወይዘሮ ብዙ ለምን እንደጠላችው አልገባሽ ብሏቸው::

"የምን ጦስ ነው እሱ? ምንም ጦስ የለብንም"

"አለመሆኑን እኮ ያወቅነው አሁን ነው:: እስቲ ማን ነው እንኳን



ለሙቶትና ለሚበላ ዶሮ ቢሉ በግ እሰው ቤት ገብቶ የሚያርደው!"

"ምናለበት?" አለቻቸው ነገሩን በአነጋገሯ ብቻ ሳይሆን በትከሻዋ እንቅስቃሴም እያቃለለች:: እንዲህ ያለው አምልኮ ቀርቷል:: ለዚያውም ጐረቤት ለጐረቤት ወንድ ሲጠፋ ማረድ የቆየ ባህላችን ነው::"

"ማቲ እንኳን የእንቁጣጣሽ ዕለት ማታ እማማ ሸዋ ጠርተውት አርዶላቸዋል" አለች ኑንሽ ጣልቃ ገብታ::

"ዝም በይ አንቺ ቀዥቃዣ! ዛሬ ምን ነክቷታል ልጅቷ!? የጠየቀሽ አለ? እሱ እንደሆን እግዚያብሔር ሲፈጥረው ዳቢሎስን አስቀምጦ ነው::የተረገመ ልጅ:: ለመሆኑ የክርስቲያን ልጅ ክርስቲያን መስሏቸው ነው እሳቸውስ እሱን ሰው ብለው የሚያሳርዱት? ጾም አያውቅ ፀሎት እግዜር የረገመው ፍጥረት::" አሉ የዳርምየለሽን ንዴት በኑንሽ ተቆጥተው ነገሩን ለማረሳሳት እየሞከሩ::ኑንሽ በድንጋጤ አፏን ይዛ ቀረች::

"ወጣም ወረደ ፈጠነ እሚሉት ገልጃጃ እግሩ አላማረኝም:: የጤና ያርግለት ብቻ::" አለች ዳርምየለሽ የእናቷ ስሜት ቢገባትም ልትናገር ያሰበችው እንዳይቀር::

"ኧረ እሱ የጤና ነው:: ሰው ዝምድና ፈልጐ ሲጠጋ እንዲህ አይባልም" አሉ በትዝብት እያስተዋሏት::

"የምን ዝምድና? ብቻ በኋላ ነገር እንዳይመጣ እንጂ . . ." አለችና ልትናገር ያሰበችው ለራሷም ስላልጣማት አንጠልጥላ ተወችው::

ገና እነርሱ ቤት መብላት የጀመረ ሰሞን አቀራረቡ ወንድማዊ መስሏት ተዝናንታ ነበር የምትቀርበው:: አንድ ቀን በአራት ሰዓት ከሌሎቹ ቀደም ብሎ መጣ:: ብቻዋን ሳሎን ተቀምጣ ዳንቴል እየሠራች ነበር:: እንደገባ እያሳሳቀ ሰላምታ ሰጣትና ሊስማት ጐንበስ ሲል ሰድባና አመናጭቃ አስተወችው:: . . .' ይህ ነው ስለፈጠነ ስታስብ በህሊናዋ የሚመጣው:: ከዚያ ቀን ወዲህ ገና ስታየው ደሟ ይቆጣል:: ለእናቷ ግን አልነገረቻቸውም:: እርሱ ገፍቶ ሲያናግራት ከአንገት በላይ ታናግረዋለች:: በተረፈ ግን ፊት አትሰጠውም:: -ሰላምታ ብቻ::

ሰሞኑን ደርሶ ቤተኛ መሆኑና ጉድ ጉድ ማለቱም አዝማሚያው አላማራትም:: ከእርሱም ይልቅ በእናቷ የዋህነትና አዙሮ አለማየት ስትናደድ ነው የሰነበተችው::

❖

"አጉል ልማድ፤ ጉጂ ባህል የወለደው የእምነት ገመድ" አለች ለራሷ በማጉረምረም:: ምግቡን ከነመቅረቡም የረሳችው ትመስላለች::

"እህሉን አትበይም ይልቅ" አሉ እናቷ ነገር እየበላች መሆኑ አበሳጭቷቸው::

በዝምታ ጭንቅላቷን ነቀነቀች ኩተመስጦዋ ላለመውጣት፡፡ እነርሱም በቅቷቸው ይሁን ነገር ተስምቷቸው ማዕዱን ይዘው ተነሱ፡፡ እርሷ በተቀመጠ ችበት አቀርቅራ ቀረች፡፡ አጉል እምነትና ጐጂ ባህልን እያወገዘች፡፡ -በህሳቧ፡፡

የችግሯ፣ የጭንቀቷ ምንጭ ራሳቸው ሆነው ሳለ አለማወቅ ተብትቧቸው፣ በጥብቅ የክርስቲያንነት ዕምነታቸው ከለላ በደመነብስ ይሸሹትና ይርቁት ወደነበረው የፀባይ ጠንቋይ ደጅ በሽታና መድሀኒት ፍለጋ እንደወሰዳቸው ከሰሞኑ ድርጊታቸው ገምታለች፡፡ በደህና ቀን ያወግዙትና ያጥላሉት የነበረው የአጉል አምልኮ ገመድ በጭንቀታቸውና በችግራቸው ቀዳዳ ገብቶ እንደጠለፋቸው ሲሰማት ለዚያ ያበቃቸው የርሷ ሁኔታ መሆኑን አሰበችና ያን ያህል መሆን እንዳልነበረባት ፀፀትና ቁጭት አደረባት፡፡

"የቤት ጣጣ ጠስ ጥምቡሳስ ብሎ ነገር" አለች አሁንም ለራሷ በማጉረምረም፡፡

"አጉል እምነት ያመጣው ጣጣ፡፡ ድንቁርና የወለደው የፍርሃት የጭንቀትና የችግር መጠጊያ፡፡ መፍትሔውን በጀርባ አዝሎ ዞሮ ማየቱ ሲቸግር የአርባ አራቱን ደጃፍ ማጣበብ፡፡ በራስ አምሳል ለተፈጠረ ሰውና ሰው ለፈጠረው ረቂቅ መጢቅ እምነት መንበርከክ፡፡ . . ."



# 26

የገና ዕለት ነው፡፡ በስተምሥራቅ በኩል አጨንቁራ ለብ ካለው ሙቀቷ ጋር ስታጫውታት ያረፈደችው ጀምበር ከረር ብላ የአዲስ አበባን እርቃን መጥበስ ብትጀምርም፣ በዚህ የጥድ ሠራዊት በተጠንቀቅ በተሰለፈበት ቦታ ከአናት አናት የተያያዘ ፀጉራቸውን /የጥዶቹን/ አልፋ የረገጡትን ምድር እንደልቧ ለማቃጠል አልተመቻትም፡፡

ቦታው ጀርባውን በባህር ኃይል ለሸሮ ሜዳ፣ ደረቱን ከወንዝ ማዶ ለፈረንሳይ ለጋሲዮን፣ ግራ ሽንጡን ለራስ ካሣ ሠፈር /ኢየሱስ/ ቀኙን ለተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የሰጠው የቀድሞው መነን መናፈሻ ሲሆን በተፈጥሮ አቀማመጡ ያማረና በዕድሜ ረዝመው በሰል በሰል ያሉ የጥድ ዛፎች በብዛትና በሥርዓት ተሰልፈው የሚገኙበት ፀጥተኛ ሥፍራ ነው፡፡

በዚህ ጫካ መሀል አንድ መለስተኛ ቪላ በሰው እጅ ተከርክመው ባደጉና አሁን ግን ችላ ተብለው ሽረሪት ባደራባቸው አፍሮ ቅርጽ ጥዶችና በአበቦች ተከብቦ ይታያል፡፡ የቤቱ ዙሪያ አካባቢም ለብቻ ታጥሮ በሰውና በሀይለኛ ውሾች ይጠበቃል፡፡ ከዚሁ ግቢ ተነስቶ በአሜሪካን ኤምባሲ ጀርባ የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤትን አጥር በስተግራው ጨረፍ አድርጐ ወደ ቀኝ በመታጠፍ ከዋናው የሸሮ ሜዳ ስድስት ኪሎ መንገድ የሚቀላቀል ቀጭን አስፋልት ተዘርግቷል፡፡ ይኸው አስፋልት ወደ ግቢው ሲመለስ ያመጣቸው ሁለቱ የፍቅር ቤተኞች በስተግራ ለቀቅ አድርገውት ከዛፎቹ ሥር ይገኛሉ፡፡

ሥፍራው ፍቅራቸውን እንደወጡ ጀምሮ በርካታ ትዝታዎችን የተለዋወጡበት ነው፡፡ በተለይ የነፃው ዕሁድ ፕሮግራማቸው ከመጀመሩ በፊት ትኩስ የፍቅር ጊዜያቸውን በሰፋት ያሳለፉበት ነው፡፡ በረዣዥሞቹ ዛፎች ታዛቢነት የፍቅር ቃልኪዳናቸውን ያለቅለበት ያሠሩት በዚሁ ሥፍራ ነበር፡፡ መጀመሪያ ሲመጡ ከሰው ዓይን ለመሸሸ እና የፈለጉትን ያህል ባይሆንም የብቸኝነት ነፃነታቸውን ለማግኘት ነው፡፡ እያደር ግን ለቦታውም ፍቅር ያዛቸውና በርካታ እሁዶችን ተመላለሱበት፡፡ ተፈጥሮአዊ ውበቱን ከማድነቅ አልፈውም የሰው ጥረት ታክሎበት የህዝብ መናፈሻ ቢሆንና በተከለለው ግቢና ቪላ ሳይቀር እነሱም ሆኑ ሌሎች መሰሎቻቸው /ፍቅረኞች፣ ሠርገኞች፣ ጓደኞችና የተፈጥሮ ውበት ናፋቂዎች ሁሉ/ እንደልባቸው ሽር እያሉ እንዲዝናኑ 'ቢደረግ' ብለው

ተመኝተዋል:: እንዲያውም እንዳለ ይኼን ምኞቱን ተመርኩዞ ባንድ ወቅት "በተፈጥሮ ውበት የመዝናናት ባህልን ለማዳበር" በሚል ርዕስ በዓምዱ ሥር ባቀረበው መጣጥፍ ላይ በዋናነት ስለዚህ ሥፍራ ጠቀሜታ አትቷል::

ዛሬ ግን የሁለቱም ዓይኖች የቦታውን ውበትና ግርማ ለማስተዋል ታውረዋል:: የየልባቸውን ፍራቻና ጥርጣሬ ይዘው የጎሪጥ እየተያዩ እንደ ደረሱ ዳርምየለሽ በሶፍት ጠቅልላ የያዘቻትን የተጣጠፈች ወረቀት ሰጠችው:: በመገረም ፈገግታ ተውጦ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ ደግሞ ደጋግሞ አነበባት::

"ምን አላት መሰለሽ ሰውዬው?" አለ የሚፈታተነውን የስሜት ንዳድ ተቆጣጥሮ በሀሳቡ የመጣለትን ተረት በፈገግታ እያጣጣመ:: ተረቱን አንድ የአምዱ ተሳታፊ ልኮለት ለንባብ ካዋለው ቆየት ያለ ቢሆንም እንዳሁን ከልቡ ገብቶ አያውቅም:: ከራሱ ገጠመኝ ጋር አገናዘበና ከት ብሎ ሳቀ:: ንዴትና ብሽቀት የፈጠረው መራራ ሳቅ::

"የቱ ሰውዬ?" አለች አሳሳቁ ስላላማራት በምን ሊል ነው ስጋት እያስተዋለችው::

"አዳምጪኛ ልነግርሽ እኮ ነው" አለ አሁንም በሽሙጥ ፈገግታ እየሸረደዳት::

እሷ አላየችውም:: ባል ከቆጡ ወጥቶ ተንጠልጥሏል:: ሚስት ወፍጮዋን እየገረደፈች ታንጎራጉራለች::

'መሄድ መሄድ አለኝ መንከልከል መንከልከል
አፌ ባይናገር ሆዴ ይዟል ተንኮል::'

"ይኼንን የሰማው ባሏ ምን አላት መሰለሽ? ልደብድብሽ፣ ልመልስሽ፣ እንዴት ተደርጎ! አካኪ ዘራፍ! አላለም:: አልለመናትምም::

'መሄድ መሄድ ነው ወይ መንከልከል መንከልከል
ራሱን ሳይጎዳ ሰው አይጎዳም ተንኮል::' አላት ይባላል::

"እና!" አለች ተረቱ ከእሷ ችግር ጋር አልዛመድ ብሏት:: ይልቁንም የእንዳለ ተረትና ሰላቅ አበሳጭቷታል::

"አሁን ይሄን ተረት ምን አመጣው ታዲያ 'ማሞ ሌላ ፎቶ ሌላ' አሉ:: ይልቅ . . ." ስትል አቋረጣት::

"አትሳሳች! ሰውዬው ማሞ ቢሆንም ፎቶውም እኮ የእርሱ ምስል ነው:: ፎቶው ማሞን ይገልጻል::"

"አልገባኝም! ምን ልትለኝ ፈልገህ ነው?"

"እሱማ እንዴት ሊገባሽ ይችላል! እኔም ሳላረፍድ አልቀረሁም::"

"ለምኑ?"

"ተረቱን ለመንገሩ ነዋ!"



"እንዴት!"

"ተይ እንጂ ዳርምየለሽ! ለምን እንደ አላዋቂ ታደናቁሪኛለሽ:: እኔኮ እሚገርመኝ! እስከመቼ በኩኩሉ ጨዋታ ተሸነጋግለን እንዘልቃለን?" አለ አንዳች እውነት ከግንባሯና ከዓይኖቿ ያነብ ይመስል ትክ ብሎ እያስተዋላት::

እንደወትሮው ቢሆን ከተቋጠሩ ቀናድቧ ሥር ቅዝዝ ያሉ ዓይኖቿን ሲያይ መረበሽና መጨነቅ አስተክዞት ያስቆጣትን ወይንም ያሳዘናትን ነገር ለማወቅ በጥያቄ እየወተወታትና እያጽናናት ግራ ተጋብቶ ይቅበጠበጥ ነበር:: አሁን ግን በትእዝብት ተወጥሮ በብስጭትና በመበለጥ ቁጭት ተጠፍሮ ለእርሷ የሚሰማው ርህራሄ የቀረው አይመስልም:: ከደረት ኪሱ ሲጋራ አውጥቶ ለኮሰና ትንፋሽ እስኪያጥረው በረዥሙ ሳበ::

"እንድሽ ፣ ዛሬ ምን ነክቶሃል? የምታወራው ሁሉ እንቆቅልሽ ነው የሆነብኝ:: የማይደረስበት መልስ የሌለው እንቆቅልሽ:: ማለት የፈለግከው ነገር ካለ ለምን በቀጥታ አትነግረኝም?" አለችው::

"ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ አሉ" አለ ግራ የተጋባች መምሰሏ ገርሞት::

"እንዴ! አማርኛህ ሁሉኮ ተረትና ቅኔ ሆኗል" ንዴቷን መገረሟ በልጦት ሳትወድ ፈገግ አደረጋት::

"ሳያውቅ የማያውቅ ቢነግሩት ይይዛል:: አውቆ የማያውቅን ግን ምን ማድረግ ይቻላል:: ከነተረቱም 'አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም' ይባል የለም:: ስሚ!" አለ የገጽታው ጥቁር ፍካት በጥልቅ የቅሬታና የቁጭት ጭጋግ እየተጣለ:: ደብዛዛ ፊቱ ተኮማትሮ::

"አውቀሽ ላለማወቅ ብትሞክሪም፣ ሀቅን በዳርዳርታው አንቺነትሽን በመስታወት ላለማየት ዓይንሽን ጨፍነሽ ብትሸሺም እኔ እንዳንቺ የድብብቆሽ ጨዋታው አይሆንልኝም:: እና እነግርሻለሁ:: እውነት ውሸት ብለሽ እንድታረጋግጪልኝና እንድታስተባብይ ግን አልፈልግም::"

"ምንድነው እሱ? እኔ . . ." ብላ የጀመረችውን ሳትጨርስ በቁጣ አምባረቀባት::

"በቃሽ!"

ደግነቱ ያሉብት አካባቢ የተሞላው ጆሮ በሌላቸው ዛፎች ነው እንጂ በዚያ ቁጥራቸው ልክ የተሰበሰቡት ሰዎች ቢሆኑ ኖሮ እንደመብረቅ በወረደው ድምጹ ተሸማቅቀው እርስ በእርሳቸው በተላተሙ ነበር:: ዳርምየለሽማ አገር ምድሩ እንደዞረባት ከተደገፈችው ግንድ ጋር ተጣብቃ ቀርታለች::

"ካሁን በኋላ ምንም ጥያቄ፣ ምንም ማስመሰል አልፈልግም:: ጆሮሽን ብቻ፣ ጆሮሽን ብቻ ነው ላንዴም ለመጨረሻም ጊዜ የምጠይቅሽ ነገር ቢኖር::

በተረፈ ይበቃሻል::

“የማሰብ ህይሌን አሳጥተሽ በማላውቀውና በማልፈልገው የጡንቻ ልሳን እንድናገር አትገፋፊኝ:: ሲያስቅስ የከረመ አንጀቴን፣ ታምኖ ባለመታመን ጥይት፣ በክህደት የቆሰለ ልቤን በእሾህ እንደበትሽ አትውጊብኝ:: የጭቃ እሾህ መሆንሽን፣ መሠሪነትሽን ሳላውቀው ከተደበቀው ሰይጣናዊ ገጽታሽ በላይ በመላእክት ቅዱስነት መስዬሻለሁ:: አምኜሻለሁ:: ወድጄሻለሁ:: አሁንም እንኳን ቢሆን እወድሻለሁ:: እምነቴ ግን ቀስ በቀስ እየሟሟ መልሼ ሳረጋውና ስሰበስበው ብከርምም ለህይወቴ ማጣፈጫ የጥሩ ፍቅር ማረጋገጫ ሊሆንልኝ አልቻለም::

“‘ብርሌ ከነቃ አይሆንም እቃ’”

“ኧረ ተው እንዳለ! አታስጨንቀኝ” አለች በማታውቀው ብሶቱና ባልጠበቀችው ምሬቱ ሰክራ ከተደገፈችው ግንድ ሥር ተንሸራትታ መሬት በመያዝ እየተንሰቀሰቀች::

“እኔ . . . እኔም እወ. . .” እንደ ብርድ ደረቷን የሚሰብቃት እልህና ሀዘኗ ህቅ አድርጐ ያዛት:: በአንድ እጇ የልቧን መውጣት ትከላከል ይመስል ደረቷን ደግፋ በሌላኛው እጇ ከዓይኖቿ ወደ ጉንጯ የሚፍሰቀለቅ እንባዋን መጥረግ አይሉት መታጠብ ሙሉ ፊቷ ላይ አጥመቀመቀችው::

“እኔ አይደለሁም የማስጨንቅሽ የሚያስጨንቅሽም የሚያስለቅስሽም የገዛ ድርጊትሽ ነው::” አለ እንደከዚ በፊቱ በእንባዋ ተበልጦና ተታልሎ ላለመረታት ፊቱን ወደ እማያያት አቅጣጫ እያዞረ::

“ይበቃኛል የእስካሁኑ:: ከእንግዲህ፣ እንኳን አንዲት በእምነትና በህይወቴ የተጫወተች ከህዲ ቀርቶ ፍቅርና ጠረኗን ሳልጠግብ የተለየችን እናቴ እንደገና ተፈጥራ ብታለቅስና ብትለምነኝ የሚመለስ ልብ የለኝም:: የዓመታት ድብብቆሽሽን ሰምቼ እንዳልሰማሁ ራሴን ስሸነግልና ሳታልል መቆየቴም ይቆጨኛል:: ምን ላድርግ፣ እወድሽ ነበራ:: የፍቅር ልቤ ታውሮ ጥሩ ጥሩሽን እያሰብኩኝ የሰማሁትን የጠረጠርኩትን ሁሉ ሰረዝኩት” አለ ዓይኖቹ የቋጠሩትን እንባ በቀኝ እጁ የመዳፍ ጠርዝ እያፈረጠ::

“በስተመጨረሻ ግን አስማየቴን ተማምነሽ፣ አለመጠርጠሬን ገምተሽና ንቀሽ የሸረብሽው የተንኮል ድር ከፊቴ ላይ ሲያገጥብኝ፣ ይባስ ብለሽ ደግሞ ቤት ለቤትሽ ተልከስክሰሽና ንጹህ ፍቅሬን አርክሰሽ የቋጠርሽውን የበደል ፍሬ! ህም! . . .” ከንፈሩን ገጥሞ ወደ መሬት አቀረቀረ:: -እየታየው::

በፍቅር ስም ተታልሎና ተበልጦ ሳይውልበት የያዘችውን ዘር የእኔ



ነው ብሎ ሲቀበል፣ የእርሱ እንዳልሆነ ልቡ እያወቀ ኮትኩቶና አሳድጐ በስተመጨረሻ በባለቤቱ ሲነጠቅ፣ ይልቁንም ከዚያ በፊት ለፍቅሯ ሲል መቀበሉንና የልቡን ቆራጥነት ማጣት ካየች በኋላ ዲቃላዋን ከነፍቅሩ አስታቅፋው ስትሰወር:: እናም እሱን ለከፋ ችግር አጋልጣ ወደ ተሻላት ዘወር ስትል:: . . . ሌላም ሌላም መጥፎ ሀሳብ እንደ አሁን እንደ አሁን ተስምቶት ጭንቅላቱን ነቀነቀ::

ዳርምየለሽ በበኩሏ በማታውቀው ክህደቷ ምክንያትነት በፍቅር ሲያቆላምጣት ልቧን እየነዘረ በስሜትና በጉጉት እንድታዳምጠው ያስገድዳት ከነበረው ገናና እና ማራኪ አንደበቱ የሚወጡት የወቀሳ ቃላት የእንዳለ ሳይሆኑ የሰይጣን ቁጣ ሆነውባታል:: ጭንቅላቷን ጉልበቷ ላይ ባስደገፈቻቸው እጆቿ መሃል ቀብራ እንደተቀመጠች ሀሊናዋ የሰማውን ደግሞ ደጋግሞ እየደወለባት በህዘን ተሸማቀቀች::

በመሀከላቸው በተፈጠረው ዝምታ ሳቢያ በአስፈሪ ቅዠት ተውጣ ስትጨነቅ የቆየች መስላትና ወደ እውኗ ለመመለስ ሞከረች:: ነገር ግን ከእውን ወደ እውን መሸሽ ከባድ ነው:: ከእውን ወደ ህልምም ከዚያው የበለጠ ከባድ ነው:: በገሀዱ ዓለም የገጠመን እውነታ ዓይንን ጨፍኖ ከመጋፈጥና ከመቀበል በቀር ምንም ዐይነት ማምለጫ መንገድ የለም:: አማራጭ ቢኖር የት እንደሚያደርስ የማይታወቀው ሞት የሚሉት የህይወት በኋላ ህይወት ብቻ ነው:: በተረፈ እስከመጨረሻው የእስትንፋስ ጠብታ ሀሊና የቀረጸውን ሲደውልና ሲያስተጋባ ከራስ እየሸሹና እየተጣሉ እንገትን ቀብሮ መኖር::

ዳርምየለሽ በህልምና በእውን የተጭበረበረ አደቧን ገዝታ ከምትወደውና ከሚወዳት የችግሯ የደስታዋና የፍቅሯ ተጋሪ ጋር ሆና በሳቅና በጨዋታ በመረዳዳትና በመተዛዘን ለመገኘት ያደረገችው እንደገነት የራቀ ምኞትና ሙከራ አልተሳካላትም::

አንገቷን እንደቀበረች የእንባ ጉም በጋረዳቸው ዓይኖቿ ወደ ግንባሯ ሲያፍ አስተዋለችው:: በመጨረሻው የሀዘንና የጥላቻ ስሜት:: ብዙ መናገር ብዙ መጠየቅ ፈለገች:: ሙልጭ አድርጋ ሰድባውና አመናጭቃው የልቧን ህዘንና ጭንቀት ልታስወጣም ተመኘች:: ከናፍሯ ላይና ታች በማሽን እንደተገጠመ የብረት መንትያ ተጣብቀው አልላቀቅ አሏት:: ዓይኖቿ ግን ታጥፈው ከተቋጠሩ ቀናድቧ ጋር ተራድተው የውስጧን ይናገራሉ::

እንዳለም ሊናገር የፈለገውን ያህል መቀጠል ተስኖት ዝምታውን ከሀሳቡ ጋር እያወያየ ቆየና ሠረቅ አድርጐ ተመለከታት:: ዓይኖቹ ወደ ነበሩበት አልተመለሱም:: በማግኔት እንደተሳበ ብረት መስመራቸውን እስተካክለው ቀሩ:: ሙሉ ፊቱን መልሶ አፈጠጠባት:: እንደዛ የተንሰቀለቀችው ለማስመሰልና

ለማታለል መሆኑ ተሰማውና በልቡ ሳቀባት::

ዳርምየለሽ አስተያየቱ ቢያስፈራትም ከዝምታው የእርሷን ቃል ለመስማት እየጠበቀ ስለመሰላት እንደምንም ራሷን ተቆጣጥራ ጠየቀችው::

"ምን እንዳደረኩህ ለምን አትነግረኝም? ይኼ እንደሆን በሁለታችንም ስህተት . . ." አለችና መሬት የወደቀውን ወረቀት አየት አድርጋ ንግግሯን ሳትጨርስ አቋረጣት::

"በሁለታችንም ስህተት!?' አለ ቃሏን እንደ ገደል ማሚቶ ከፍ አድርጎ እየደገመ::

"ስሚ! እንዳለ ማለት ጡጦ እሚጠባ የሦስት ወር አራስ አይደለም:: ከሁለት ወር በፊት ታመምኩ ብለሽ የፍቅር ጀርባ ጉድሽን ለታስቀምጭ በፍቅር ስም ተበልጨ ይሁን አልኩኝ:: ሳውቅ እንዳለወቀ ሆኜ:: አሁን ደግሞ ይባስ ብለሽ ጓዳ ለጓደ ስትልከሰከሽ የቋጠርሽውን ጽንስ የሁለታችንም ስህተት እያልሽ ታላዝኚብኛለሽ::

"ብልጥ የሚበልጠው አንድ ቀን ነው:: ሁለት ጊዜ ሞኝነት የለም:: ይልቅ ሳይመሽብሽ ያሳሳተሽን፣ የልጅሽን አባት ፈልጊ:: ሁሉንም ነገር ደርሼ በታለሁ:: ጊዜና ትዕግስትን ይጨርስ እንጂ የደፈረስ መጥራቱ የተደበቀም መውጣቱ የማይቀር ነው:: እስከዚህ ድረስ ነበር የሆዴን በሆዴ ብዬ ለራሴ እስኪከለትልኝ የጠበቅኩት::"

ዳርምየለሽ በመጨረሻ ተስፋ መቁረጥ ተስፈንጥራ ተነሳችና ንዴት ያገረጣው ፊቷን ጣዕረሞት አስመስላ፣ ካፏ እሳት የሚወጣ ያህል እያቃጠላትና እያንገበገባት "ከሀዲ!" ብላ ጮኸችበት::

እልህ እንደተናነቃት እየተንቀጠቀጠች ጥፍር የሌላቸው ጣቶቿን ለቡጭሪያ አይሉ ለማነቅ ወደፊቷ አስቀድማ ተወረወረች:: እንደሰው ሳይሆን እንደተቆጣ ነብር ፈርጧት ወደ ኋላው ሸሸት ሲል ያለ ሀይሏን በእርሱ ላይ ለማሳረፍ ተጠቅማ ነበርና ከቆመችበት ዘቅዛቃ የመሬት ቅርጽ ጋር ተዳምሮ ሚዛኗን አሳታት:: በግንባሯ ተደፋች::



# 27

በፍቅር ላይ ጀገንኩ ብሎ ውስጥ ውስጡን በጥርጣሬ ሲያር የነበረ አንጀቱ ከቆረጠለት ወይንም ቆረጠልኝ ካለ፣ በህሊናው ጥልቅ ጉድጓድ ሲጨስና ሲያጨሰው አርሱ ግን በፍቅር ሃይል ሲያበርድና ሲያቀዘቅዘው በሸፍንፍን የቆየ በደሏ በግልጽ መንደድና መጠፉን መቋቋም አቅቶት የቆሰለ ልቡን ለማሻር፣ የተረፈ ህይወቱን ለማዳንና መበለጡን ለመብለጥ ረመጡን ከነፍሙ አውጥቶ ወደ ባለቤቱ ከደፋ ዓመታት፣ ወራትን ሳይሆን ቀናትን አስቆጥሯል:: አፎይ ለማለት:: ዳግመኛ ፍቅር በሚሉት ገመድ ላይጠለፍ:: አፍቅሮ ላያምን፣ አምኖም ላይበለጥ፣ ተበልጦ ላይቀና፣ ቀንቶ ላይቃጠል::

አንዳሰበው ግን አልሆነለትም:: ይልቁንም ለብእናው ባዶ ሆኖበት ሀሳብ ትዝታ፣ ጭንቀትና ፍርሃት እየተመላለሱ ሲረግጡት፣ ሲያሳዝኑትና ሲያስጨንቁት የሀሊና ረፍቱን አጥቶ ነው የሰነበተው::

"የጥላቻ እናቱ ፍቅር ነው ማለት ነው?" አለ በብርድ ልብሱ ተጠቅልሎ ዓይኖቹን እንደ ሀሳቡ እየጨመቀ:: "መሆን አለበት" አለ የሀሳቡን ጥያቄ በሀሳቡ እየመለሰ::

"ፍቅር እሳት ነው:: ጥላቻም እሳት ነው:: ሁለቱም ሸሽት የማያርቃቸው የደም ውስጥ እሳቶች ናቸው:: ፍቅርና ጥላቻ ተቃራኒ ናቸው ያለው ማነው? ተቃራኒ የሚያስኛቸው ምንድነው?" አለ በሀሊናው በዘረጋው የውይይት መድረክ ለሚያደምጡት የማይታዩ ታዳሚዎች::

"ፍቅር በደስታ፣ በመልካም ሥራና አስተሳሰብ፣ በቅንነትና በሰላም የሚገለጽ ንጹህ ብሩህ ስሜት ነው:: ጥላቻግን በሀዘን በክፋትና በተንኮል፣ በፀብና በጉዳት የሚገለጽ የተጠከለ ስሜት ነው:: ይኼ ነው ተቃራኒ የሚያደርጋቸው" አለው ከማይታዩት የሀሳቡ ተካፋዩች አንዱ::

"ታዲያ ለምን ሁለቱም ሥቃይ ይሆናሉ? ለኔ ሁለቱም አንድ ናቸው:: ልዩነታቸው ያለው በውዴታና በግዴታ ከመቃጠሉ ላይ ነው:: ያፈቀረ ሲነድ ይስቃል:: በጥርጣሬ መንደዱን፣ በቅናት መቃጠሉንና ማረሩን በፍቅር ሥም ይሁን ብሎ ሰላምና ደስታን እያዛጋ ራሱን ለፍቅር ሲማግድ ይኖራል:: የኋላ

ማረሳሻ ያለው አድርጋ ስላሰበችው ቅር አላት።

"ቁርስ ልሠራ ነው!"

"ለማን?" አላት "አባባ እንደሆን ጃንሜዳ እንዳደረ ነው። እኔም ወደዚያው ልሄድ ነው። ለራስሽ ነው፣ ቀስ ብለሽ ብትነሺ ይደርሳል" አሁን እኮ በጣም ጥዋት ነው።

"ለምን? ቁርስ በልተህ አትሄድም እንዴ? አሁን ይደርሳል።"

"አልበላም። እንዲያውም መድረሴን እንጃ። ከመጀመሪያው ጀምሬ ልከታተለው ነበር ያሰብኩት። መድፍ ሲተኮስ እየሰማሁ እሱቲ ምን አጋደመኝ።"

"እንዲሁ ሆነህ ልትሄድ ነው ታዲያ!"

"ምን ሆኛለሁ?" አለ ህሳቧ ቢገባውም ሲያደናግራት። እርሷም አልለቀቀችውም።

"ገላህን ታጥበህ፣ ልብስህን ቀይረህ አትሄድም? ታቦት የሚወጣው ገና በአራትና በአምስት እኮ ነው።"

"ገላዬን ሰመለስ እታጠባለሁ። ልብሱም የለበስኩት ይበቃኛል። ምን እኔ ልሞሽር አልሄድ።"

"እንዴ! ጥምቀት እኮ ነው ቀኑ። ነጭ በነጭ እንኳን ባይኖርህ ሱፍህን አለዚያም የታጠበ ልብስ ልበስ። አምና ሸር ብለህ እንዳልዋልክ! ካቻምናም እንጃ። እንደዚህ ሆነህ ነው ከእርሷ ጋር የምትውለው?"

"ከማን?" አለና ማንን ለማለት እንዳሰበች ስለገባው እሷ እስክትነግረው አልጠበቀም። "እኔን ነው ልብሴን የምትፈልገው? ይሄ እሷን አይመለከትም።" አላት ባጭሩ እንድትተወው ሳይታወቀው ፊቱን ክስክስ እያደረገ።

"እንዴት አይመለከታትም? ባንተ ባይሰማህም እሷ እንተ እንድታምርላት፣ እንድትደምቅላት መፈለጓ አይቀርም። እኔም ብሆን በእህትነቴ ኬክ ከመሰለች ጓደኛህ ጋር ኬክ መስለህ ብትውል ደስ ይለኛል።" አለች የፊቱ መከሳተር ውስጥ ውስጡን ቢያስደነግጣትም የግድ ልታሳስቀው እየሳቀች።

"ኬክ ብትሆን ከረሜላ ለራሷ ነው።"

"እንዴት! ላንተም ነው እንጂ"

"ኡፍ . . . እሱቲ ተይኝ!" አለና ለፊቱ ውሃ ፍሊጋ ሲነሳ ቀድማ አቀረበችለት። እሱ ሲታጠብ ከፊቱ ቆማ በሀሳብ ሰመጠች።

ለወትሮው ውሎ ሲመጣ ማታ ማታም ሆነ በእረፍት ቀናት እቤት ሲውል ከሷ እና ከአባታቸው ጋር ይጫወት ነበር። ሰሞኑን ግን ቀልድ የለም ጨዋታ፤ የሚፈልገውን ከመጠየቅና ለተጠየቀው ከመመለስ በስተቀር የውትሮ ፀባዩ ተቀይሯል። አምሽቶ መጥቶ፣ እንዳንዴ ራት ሳይበላ እንዳንዴም ነካ ነካ አድርጎ በሙተው እንደገባ ይተኛል። ጧትም ሲነሳ የቀረበለትን በልቶ ያለምንም ትርፍ ንግግር 'ደህና ዋሉ' ብሎ ይወጣል።



ባብዛኛው የሚሠሩበትን ሆቴል የቡና ማሽን እንደታቀፉ አምሽተው ሥራ ባይኖርም የትም ውለው ከሚገቡት አባታቸው ይልቅ ይህንን የባህሪ ለውጥ ልብ ብላ ያስተዋለችው እሷ በመሆኗ ስትጨነቅና ስትጠበብ ነው የሰነበተችው።

አንድዬ ወንድሟን ትወደዋለች። እንዳለ ወንድሟ ብቻ ሳይሆን እናቷም ነው። እህቷም ነው። ጓደኛዋም ነው። አንዳንዴም ከአባቷ በላይ አባቷ ነው።

ከፎቶአቸው በቀር ጥቁር ይሁኑ ቀይ የማታውቃቸው እናቷ የሞቱት በሷ መወለድ ምክንያት መሆኑን ከተዉላት ታሪክ ባሻገር የእናትነት ለዛቸውን ቀርቶ እስትንፋሳቸውን ከዘጠኝ ወር የማህፀን ዝምድና በላይ ለማግኘት አልታደለችም። እሱንም ይሙቅ ይቀዝቅዝ፣ ይመች ይቆርቁር ለይታ የማታውቀው፤ ለማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር የተሰጠ የህይወት መጀመሪያ ዘመን በመሆኑ በአንጻራዊ ግንዛቤ የምታስበው እና የምትረዳው ነው። ከዚያ በቀር የእናትን ክፋት ይሁን ደግነት አታውቅም። በደመነፍስ ከህይወቷ አንድ ትልቅ ነገር እንደሚጎድላት ከሚሰማት በስተቀር እናቴ ይኼን አደረገችልኝ ወይንም ይኼንን አደረገችኝ ብላ የምትጠቅሰውና ትዝ የሚላት ነገር የለም።

በምትኩ የእናት ያህል የሚጨነቅላትና የሚያሰብላት ታላቅ ወንድሟ እንዳለ እናቷ ነው። ሲያማት በግርጌ በራስጌዋ ታጥፎና ተዘርግቶ፣ ሲርባት ከላይ ከታች ወጥቶና ወርዶ፣ እንባዋን አንብቶ ሳቋን እየሳቀ 'አለሁሽ' የሚላት እሱ ነው። አባቷ እንደሆን በተፈጥሮ ህሳብ የለሽ ናቸው።

እንዳለ የቤተሰቡን በተለይም የእህቱን የሃላፊነት ቀንበር መሸከም የጀመረው ገና ከህጻንነት ዘመኑ አንስቶ ነው። ሊስትሮ ጠርጉ፣ ዘምቢል ተሸክሞና ሎተሪ አዙሮ ያገኛትን ይዞ እየገባ ከዳቦ የማያልፈውን የአባታቸውን ቀለብ አሻሽሎ በወጡም በእንቁላሉም በእንጀራውም፤ ገቢው ከፍ ሲልም ሥጋ ሳይቀር ገዝቶ በመቀየር ከእህቱ ጋር ተካፍሎ እየበላ ለራሱ ድሪቶና ቁምጣ እየለበሰ መናኛ ቢሆንም ለእህቱ አዲስ ገዝቶ እያለበሳት የራሱን እድገት ሳይጨርስ ባለው አቅም ተንከባክቦ ነው ያሳደጋት። ለትምህርቱ ባለው ፍቅርም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቋል። እርሷንም ተቆጣጥሮ ስላስተማራት ዘንድሮ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ትወስዳለች።

፨

በተለይ ሥራ ከያዘ ጀምሮ በሚያደርግላት የሞራልና በቂ የመማሪያ መሣሪያዎች ድጋፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ በትምህርቷ እየጐበዘችና እየተሻሻለች ነው። እርሱም ሳይሰለች ከራሱ ይልቅ የርሷን ችግር እያስቀደመ ያሟላታል።

አስቴር ለእንዳለ ያላት ፍቅርም ከዚህ ሁሉ የመነጨ ነው። ውሎ እሚገባ አይመስላትም። እንደ ጥሩ እናት ትለስትለታለች። ትናፍቀዋለች። እርሱ ለእሷ እንደሚሆንላት ሁሉ እርሷም ትሆንለታለች። ፊቱ ፊቷ ነው።

ሲስቅና ሲቀልድባት ደስ የሚላትን ያህል ገጽታው ሲጠቁር ፊገግታው ሲሰበር ልቧ ይሰበራል::

ሰሞኑንም ህሊናዋ ሰላሙን አጥቶ ነው የሰነበተው:: ምን እንደሆነ ለማወቅ አሰሳሰላ የገመተችው ጉዳይ ቢኖርም ምን ብላ እንደምትጠይቀው ጨንቋት፣ ለዚያውም የፊቱ አለመፈታት አስፈርቷት ነው የሰነበተችው:: ዛሬ ደግሞ ይባስ ብሎ ከመኝታው አጣልቶ ብርድ ልብስ የሚያስወረውር ብስጭት ይሁን ቅዝት አየችበት::

"እንድዬ! ለምን ታስጨንቀኛለህ? እኔ እህትህ አይደለሁም? ከመቼ ወዲህ ነው እንደዚህ ዓይነት ፀባይ ያመጣኸው?" አለች እንባዋ መጣሁ መጣሁ እያላት::

"ምን አደረግኩሽ?" አለ ደንገጥ ብሎ ፀጉሩን ውሃ በነካ እጁ እያሸ::

"ሰሞኑን ሁሉ ልክ አይደለህም:: አንድ የሆንከው ነገር እንዳለ ይገባኛል::"

"ምንም አልሆንኩም:: ያሳየሁት ለውጥ አለ እንዴ?"

"በጣም ነዋ! አይታወቅህም ማለት ነው?"

"ይቅርታ እሰቱ! ዝም ብዬ ነው::"

"ዝም ብለህ እንኳን አይደለም:: ታዲያ ከመሬት ተነስቶ የሚያስኮርፍና ብርድ ልብስ የሚያስወረውር ምን ነገር መጣ?"

"ባንቺ አይደለም:: . . . ማለቴ ምንም አልሆንኩም::"

"በኔ ነው አላልኩም:: አንድ ነገር ግን ሆነሃል:: ተጣላችሁ እንዴ?

"ከማን ጋር?" አላት ሚዶውን ፀጉሩ ላይ ሰክቶ በጥያቄ አስተዋላትና::

"ከዳርምየለሽ ጋር" አለችው ልቧ ቢፈራም ግልጽ አድርጋ::

"ቡዳ!" አላት በሆዱ ያን ያህል ማወቋ አስገርሞት::

"አልተጣላንም"

"አትደብቀኝ ተጣልታችኋል:: ይኸው እዚ ቤት ከመጣች ስንት ጊዜዋ! ለምን ቀረች? አንተም ብትሆን ሰሞኑን ስለሷ ማንሳት ትተሃል::"

እንዳለ ሊደብቃት እንደማይችል ያውቃል:: አሁን ቢያስተባብልም ወደፊት ማወቋ የማይቀር ነው:: ደግሞስ ከፍቅረኛው ቢጣላ ከእህቱ ምን አስደበቀው::

"ካልሽስ አልደብቅሽም:: ተጣልተናል::" አላት::

"ለምን? ጥሩ ልጅ እኮ ናት::"

"በጊዜው"

"አሁን ታዲያ ምን ተፈጠረ?"

"እሱቱ አሁን ልነግርሽ እምችለው ጉዳይ አይደለም:: ጊዜ እሚጠይቅ



ስለሆነ በደንብ ቁጭ ብለን እነግርሻለሁ:: አሁን ይረፍድብኛል::"

"ነገሩስ እሺ! ግን ለዚህ ብለህ ነው ልብስህን ሳትቀይር ግዴለሽ ሆነህ የምትወጣው?"

"በሱ ምክንያት አይደለም:: የዛሬው የጥምቀት ውሎዬ ከሌላው ጊዜ ይለያል::"

"እንዴት?"

"ለሥራ ነዋ የምወጣው:: ለጋዜጣ ዝግጅት የሚሆኑኝን አንዳንድ ነገሮች ለማግኘት" አለና ኮቱን ደርቦ የሚያስፈልጉትን የጋዜጠኛ መሣሪያዎች ከያዘ በኋላ ተሰናብቷት ወጣ::

በህሳብ እንደሰመጠች ሸኘችው:: ከሦስት ክንድ ተኩል ለማያልፍ ቁመቱ ያጠረችውን በር እንደ ልማዱ ዝቅ ብሎ አለፋትና እቻ ለእቻ ተጠጋግተው በተደራረቱት ቤቶች መሃል ሁለት ሰው ተራ እምታስገባዋን መተላለፊያ ተከተላት:: ጣደፍ ጣደፍ እያለ::

"ምን አጣላቸው ይሆን?" አለች እሱቴር ለራሷ:: ዳርም የለሽን ገና ያየቻት ዕለት ነበር የወደደቻት:: ከዚያ በኋላም ደጋግማ ስትመጣና አንዳንዴ እንዳለ ሁለቱንም ቴአትር ወይንም ሲኒማ ጋብዟቸው ወይንም ወደ መናፈሻዎች አካባቢ ይዟቸው ሲሄድ ባደረጉት መቀራረብ በደንብ አውቃታለች::

ከውብቷ ባሻገር በፀባይዋና በአእምሮ ብስለቷ በተለይም ለእንዳለ ባላት ከፍተኛ ፍቅር እሷም ወዳታለች:: በጥሩ አፍቃሪነቷ አድንቃትማለች:: እቤታቸው ስትመጣ ቁጭ ብድግ ብላ ነው የምታስተናግዳት:: የምትወደው ወንድሟ የሚወዳት በመሆኗም በእርሷ ላይ ሳይቀር የእህትነት ስሜት አሳድራባታለች:: ብቻ በምኗም በምኗም ጥሩ ልጅ ናት:: ወንድሟም ቢሆን በፀባዩ በእውቀቱና በእርጋታው ጥሩነቱ ከእርሷ ቢበልጥ እንጂ የሚያንስ አይደለም::

"ታዲያ ምን አጣላቸው? ጥፋተኛ ማንኛቸው ይሆኑ?"

እርሷ ልትመልሰው የማትችለው ጥያቄ::

ለጊዜውም ቢሆን ሰላም ከነሳው ሀሳቡ ስለገላገለው ለምሳ ወደ ቤቱ መሄድ አላሰበም።

ጠዋት ከጥምቀተ ባህሩ የአቡኑ ቡራኬ ጀምሮ ሥርዓተ ሀይማኖቱን ሲከታተል ነው የዋለው። ታቦታቱ ወደ የመጡበት ሲሸኙም የአቦና የእየሱስን ታቦት ካጀቡት የፈረንሳይ ሌጋሲዮን ምዕመናን ጋር ተቀላቅሎ እየሱስን አስገብቶ ተመልሷል። የብዕር ጣቱ እስከቻለ ማስታወሻው ላይ ከትቧል። 'ቀልጣፋ ጆሮ' በሚላት ትንሿ መቅረፀ-ድምጽም ደህና አድርጐ አድምጠባታል። ለሥራው የሚጠቅመውን በግሉ ያስደነቀውን፣ ያስደሰተውን . . . ገጠመኙን ሁሉ ከብዙ በጥቂቱ አሰባስቧል።

ከአንድ የሰንበት ትምህርት ቤት ድንኳን ገባና ጥግ ይዞ ተቀመጠ። በቴፕ የተቀረጸ ያሬዳዊ የካህናት ዜማ ይሰማል። የሰንበት ትምህርት ቤቱ ወጣት መዘምራን እንደመድረክ ተለይቶ በተዘጋጀላቸው ሥፍራ ተቀምጠ ዋል። መዘምራኑ በተቀመጡበት ተቃራኒ ከዋናው ድንኳን ተያይዞ በተቀጠለ ሌላ አነስ ያለ ድንኳን ውስጥ እየተዘጋጀ የሚመጣው አምባሻና ዳቦ ቁርጥ፣ ሻይና ለስላሳ ድንኳኑን በሞላው ህዝብ ይነሳል።

አንድ ነጠላውን እንደ ቄስ ጋቢ ያጣፋ ታዳጊ ወጣት "እርስዎስ ምን ላምጣልዎት?" አለ ወደ እንዳለ ጠጋ ብሎ።

"አንድ ለስላሳና አንድ ዳቦ"

"የፈረንጅ ነው ያበሻ ዳቦ?"

"የትኛው ነው ያላችሁ?"

"ሁለቱም"

"ያበሻ ይሁን" አለ እንዳለ ሁለቱም ያገር ሆኖ ሳለ የፈረንጅ ያበሻ ማለቱን ባያምንበትም ክርክሩን ስላልፈለገ።

"ሂሳብ ቅድሚያ ነው"

"ስንት ነው?"

ሂሳቡን ሲነግረው ለመክፈል ባያቅማማም ከህሊናዊ ትዕዝብት ግን ወደኋላ አላለም።

"ዋጋቸው እንዴት ነው፣ ውድ አልሆነም!?" አለ ሳይታወቀው አጠገቡ ወደተቀመጡት አዛውንት ዞሮ።

"ምን ይደረግ ልጄ! ዘመኑ ነዋ! ዘመኑ! ሁሉ ንግድ ሆኗል። ጠበል ጠዲቅ የሚሸጥበት ጊዜ!" አሉ አዛውንቱ እሳቸውም የዋጋው ጉዳይ ከንክኗቸው ኖሮ።

"ምናለበት ቢሸጥ! ገንዘቡ እንደሁ ዞሮ ዞሮ ያው ለቤተስኪያኒቱ ነው። ያደለው ከዚህ በላይ ስንቱን ይሰጥ የለም" አሉ ከመጀመሪያው አዛውንት



ቀጥለው የተቀመጡ ሁለተኛ አዛውንት።

"እንዲያው መስጠትማ አንድ ስም ነው። መችስ ሰው ለእምነቱ ያልሰጠ ለምን ሊሆን ነው። ሁሉስ የግዜር አይደለም? ይኼ ግን ደግ አይደለም። የገንዘብ መውደድ ያስመስላል። ለስላሳው እንኳን ከነጋዴ የአስራምስት ሣንቲም ብልጫ። ሻዩ እንደዛ። ዳቦዋን ሳሊንክ አሳክለው ካያ ሳንቲም። በእውነቱ ልክ አይደለም። በዚ ቢሉ በዚያ ንግድ ሆኗል" አሉ ሽማግሌው እየተማረሩ።

"ባመት አንድ ቀን ተሸጠና አሁን ንግድ ሊባል ነው?"

"የምን አንድ ቀን? በማሪያም፣ በገብርኤል፣ በሚካኤል፣ በታቦታቱ ንግስ እየተመኘኘ የሚነገደውስ? አሁንማ እንዳውም ጠበል ሳይቀር በገንዘብ እየተሸጠ ነው።"

"እረ በስመአብ ይበሉ! ፀበል ደሞ የት ነው የተሸጠው? ለምን ክፉ ይናገራሉ?" አሉ ሁለተኛው አዛውንት።

"መሸጥ ተዚ በላይ ምናለ? አሁን በቀደምለት ልጆቼን ጠበል እንዲያመጡ ልኬ ባዶአቸውን ተመለሱ። ምነው ብል ጠበሉ ቤት ሊታደስ ስለሆነ እርዳታ መስጠት ያስፈልጋል ተብለን አሉኝ።"

"ይኼማ ታዲያ ምን አለበት፤ ጠበሉ ቤት ቢሠራ ለኛው ነው።"

"አይደለማ! ሁሉም ዐይነት አለው። 'ልናሰራ ነውና ያላችሁን ሠንዝሩ' ማለት ደንብ ነው። ሳንቲም ያልሰጠ አይቀዳም ማለት ግን ንግድ ነው። ሃይማኖት እንዴት በገንዘብ ይሸጣል? ጠበል ለአማኞች እንጂ ለባለገንዘቦች ብቻ መሆን የለበትም። በውነቱ ደግም አይደል" አሉ የመጀመሪያው አዛውንት ጠበሉን የከለከሏቸው ከጐናቸው የተቀመጡት የውይይት ተጋሪአቸው እንደሆኑ ሁሉ ዓይናቸውን ጐልጉለው በማፍጠጥ።

"ፍጹም ሀሰት ነው። እንዲህ ያለውን ቃል እርስዎን ከመሰለ ክርስቲያን መስማቱ በጣም ያሳዝናል።"

እንዳለ ጣልቃ ሳይገባ ንግግራቸውን እንደዋዛ እየሰማ ሳለ ልጁ የታዘዘውን ይዞለት መጣ።

ሁለቱ አዛውንት በ'ፀዲቅ' ለምን ተሸጠና -ይሸጥ ያነሱት ክርክር የፍታትና የቀብር፣ የንስሃና የሌሎችም ሀይማኖታዊ ጉዳዮችን ከገንዘብ ጋር መቆራኘት አስነስቶ በማውገዝና በመደገፍ አነታረካቸው። እንዳለ በክርክራቸው ጣልቃ መሰንዘር የሚቃጣው ሀሳብ ቢኖረውም ግጭት ውስጥ እንዳይገባ ስለፈራ ትኩረቱን በሚበላው ዳቦና በልቶ ሲጨርስም በድንኳኑ ዙሪያ በተለጠፉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ላይ አሳረፈ። ጎትጎች ክርክራቸውን ላለመስማት።

"የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው"

"በድፍረት፣ በትዕቢት፣ በመናቅም በጻድቅ ላይ የሚናገሩ የሸንገላ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ።"

"በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉ ይጸድቃሉ እንጂ ህግን

የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉም::"

"እየተጠራጠርክ እግዚአብሔርን ሁለት ልብ ሆነህ አታገልግል::"

ቤተሰባዊ የሃይማኖት ውርሱ ኦርቶዶክስ ቢሆንም ለሀይማኖት ያለው ፍቅርና አክብሮት ከራሱ እምነትነት ይልቅ ሰዎችን በአንድ አቅጣጫ ለማሰባሰብ፣ ህይወትን ለመቆጣጠርና ለመምራት ካለው ሃይል አንጻር ነው:: 'ምንም ይሁን ምን እምነት ጥሩ ነው' ብሎ ያምናል::

እምነት ህሊናን ይገዛል:: እምነት የሌለው ሰው የሚመራው በደመነፍስ ነው:: አንድ ዓይነት እምነት የሌለው ሰው ጨካኝ ነው:: ሰው በህሊናውም ሆነ ከህሊናው ውጪ የሚያምነው፣ የሚፈራውና የሚያከብረው ነገር ሊኖረው ይገባል:: እግዚአብሔርን ከልቡ የሚያምን 'በእግዚአብሔር!' ሲሉት ከጥፋት ይመለሳል:: ለቸገረው ያዝናል፤ ለራሱም ይጽናናል:: በጣኦትም በቃልቻም እንኳ የሚያምን እንዲሁ ነው:: በራሱ ህሊናም ቢሆን ጥሩ እምነትን የገነባ:: ወሳኙ በማን ወይንም በምን ሳይሆን በአንድ ልብ በአንድ ነገር ከማመኑና ራስን ለዛ ለአመኑበት ነገር ከማስገዛቱ ላይ ነው::

"ዘመኑ ነው፣ ዘመኑ" አሉ ከጐኑ ያሉት አዛውንት ከተከራካሪያቸው ጋር ያጡትን ተደማጭነት ከእርሱ ለማግኘት አንገታቸውን መልሰው::

"እንዴት አባባ?" አለ እንዳለ ሃሳባቸውን ለመስማት ጓጉቶ ሳይሆን ሲያናግሩት ዝም እንዳይላቸው ያህል::

"ስምንተኛው ሺህ ነዋ! በስምንተኛው ሺ ምን የማይሆን አለ!"

"ሰባተኛና ዘጠነኛ የሌለው ስምንተኛው ሺ:: መጣ መጣ ደረሰ እንደተባለ፣ እሱ ግን ሁሌም ወደፊት እንደሸሸ እሚኖር የማያልፍ ስምንተኛው ሺህ!" ሲል በልቡ ተቸና "አባባ ስምንተኛው ሺህ ደረሰ እንዴ?" በማለት ጠየቃቸው::

"ታዲያሳ! እንግዲያማ በጤና ነው ይኼ ሁሉ መዓት! ሴት ተወንድ እኩል ነኝ ካለች፣ ልጅ ሽማግሌ አባቱን አስቀምጦ እኔ ላውራ እኔን ስሙኝ ማለት ከጀመረ፣ ሴት ሱሪ ለብሳ ጠመንጃ ከታጠቀች፣ አደባባይ፣ ሸንጐ ወጥታ ከፈረደች፤ ይኼ አይደለም ስምንተኛው ሺ ማለት?" አሉት::

"ይኼማ ከዘመን ጋር የሚመጣ የአስተሳሰብ ለውጥ ነው:: አባቴ ከእርስዎ ባላውቅም፣ ጥንትም እግዚአብሔር ሔዋንን ሲፈጥራት ለአዳም አጋሩ እንድትሆን፣ አንድ አካል አንድ አምሳል እንዲሆኑ እንጂ አዳም የበላይ እሷ የበታች እንዲሆኑ አልነበረም::" አለ እንዳለ ሳይታወቀው ወደ ውይይታቸው እየገባ:: በንግግሩ መሃልም እጁን ወደ ደረቱ የውስጥ ኪስ ሰደድ አድርጎ 'ቀልጣፋ ጆሮውን' ቆነጠጣት:: እንድታዳምጥለት::

"ቢሆንም፣ ቢሆንም የኔ ልጅ፣ ያ ሌላ ይኼ ሌላ:: እኛ እምናውቀው በኛ ብቻም ሳይሆን በአባቶቻችንም ጊዜ ከዚያ በፊት ሁሉ ሲወርድ ሲዋረድ እንደመጣው፤ ሴት ልጅ አፈር ብላ ወደ ጓዳ፣ ልጅም እንደልጅነቱ ወደ



እኩዮቹ አለዚያም ወደ ጓዳ ነው:: ሴት የወንድን ሥራ ከቀማችማ እኔ ገብቼ ወጥ ላበስል ነው እንጀራ? ወይስ እኔም እሷም አደባባይ ከዋልን ማንኛችን ያበስልነውን ልንበላ ነው? የባልና የሚስት ልዩነቱስ ምኑ ላይ ነው?"

"ገዝታችሁ ነዋ! ወይንም ሆቴል ገብታችሁ:: እንደዘመኑ ትዳር የትም ሠርታችሁ የትም በልታችሁ ማታ ብቻ ሳዳር ተያይዛችሁ ወደ ቤት:: ቤርጐ እንደሚታደረው" አሉ ሁለተኛው አዛውንት ድንገት ጥልቅ ብለው:: እንዳለ ጣልቃ ከገባ ወዲህ ገለልተኛ ሆነው ሲያዳምጡ ነበር የቆዩት::

"ኧረ እኔስ ቸሩ መድሃኔአለም ይመስገን በደህናው ጊዜ ነው የፈጠረኝ:: እንዲህ ተገላቢጦሹ ሳይመጣ:: ይብላኝ ለዘመኑ ወጣት እንጂ ሚስቴም የኔ ቢጤ አሮጊት፣ አትቀብጥም፤ ብትሞክረውም አሳያታለሁ" አሉ የመጀመሪያው::

እንዳለ ሁለቱ ሽማግሌዎች እንዲያ በነገር ሲናቆሩ ያልቆዩትን ያህል እንደገና አንድ ሆነው ከርሱ አንጻር መሰለፋቸውና በአንድ ሃሳብ መደጋገፋቸው ባያስደንቀውም የዘመን ፀበኝነታቸው ግን ሳያስገርመው አልቀረም::

"ምናለበት?" አለ ህሳቡን ይቀበሉኛል ብሎ ሳይሆን ተንጠልጥሎ ለቀረው የመጀመሪያው አዛውንት ጥያቄ መልስ በመስጠት ሳቢያ ስሜታቸውን ለመጐትጐት::

"ምናለበት? ሁለቱም ሥራ ውለው ከገቡ ተረዳድተው ራታቸውን ቢያበስሉ መተዛዘንን መተሳሰብን ያሳያል እንጂ የወንድየውን ክብር አይቀንስም::"

"እንዴ ምን ማለትህ ነው! ይቀንሳል እንጂ:: ወንድ ልጅ ሽንኩርት መክተፍ ከለመደ የጥይቱ ነገር አከተመ ነው" አሉ ሁለተኛው አዛውንት::

"ምን ጥይቱ ብቻ! አደባባይ ቢውል አይረታ፣ ማረሻ ቢይዝ አይሄድለት፣ ዝናር ቢታጠቅ አያምርበት:: ኧረ ሱሪውም ሱሪ አይመስል:: እንኩቶ ሆኖ ነው የሚቀር" አሉ የመጀመሪያው::

"ኧረ ወዲያ!" አሉና ቀደሙት እንዳለ ሊናገር ሲል ሁለተኛው አዛውንት "ኧረ ወዲያ! ወንድ ልጅ ጉልቻ ለጉልቻ መርመጥመጥ ካበዛ ቀበቶውም አይጠብቅለት:: ሴቲቱማ ምን ታድርግ ጭንቅላቱ ላይ ሲያስቀምጣት::"

"ሴቶቹማ ምን ያድርጉ? ስልጣኔ! ነፃነት! እኩልነት! -እያለች በባሏ ላይ ትዝመት እንጂ:: ገና ወንዶችም ያርግዙ ሳይሉን አይቀሩም" አሉ የመጀመሪያው አዛውንት::

እንዳለ፣ አንድም የሁለቱ ቅብብሎሽ እድል ስላልሰጠው አንድም የእርሱ ተቃራኒ አስተሳሰብ መሰንዘር አለቦታው ከማያስፈልግ የከረረ ሙግት ውስጥ መግባት እንጂ ለውጥ እንደማያመጣ ስላጤኔ አፉን ይዞ በትዕዝብት ማዳመጡን መረጠ:: የፈለገውም ይኼንኑ ነበር::

"አሁን የኔ ልጅ አለ" አሉ ሁለተኛው አዛውንት ቀበል አድርገው ወሬአቸውን እየደራረቱ:: "ፈረንጅ አገር ተምሮ መጥቶ አባርታማ ነው

እሚኖረው:: አንድ ሜንጦ ሚስት አለችው:: እኛ ሳንድረው ተዚያው አብረው ሲማሩ እሷም ተዚ ነው የሄደችው ተፈጣጥመው አመጣት:: መቼስ ምን ልበላችሁ የቆንጆ ብላሽ፣ የመጨረሻ ብላሽ ናት:: ይኼ ሰማያዊ ሽራ እሚመስል ልብስ አለ፤ ተዚያው ነው ይዘውት የመጡት 'ራንገረሉ' ነው 'ራንገሌሪ' ይሉታል . . ."

"ራንግለር?" አለ እንዳለ በንግግራቸው ጣልቃ ገብቶ:: ወዲያውም የራሱን በውይይቱ ተሳታፊነት ለማስታወስ::

"እ! እሱን ጃኬትና ሱሪውን ሁለቱም አንድ ዐይነት ለብሰው ለምን አይመጡም! ገና እንደተመለሱ ሰሞን ነው:: ሁለቱም ወንድ መስለው:: ትንሽ ጠጉሯ ብቻ ጠቅለል ጠቅለል ማለቱ እንጂ አንድ ሆነው:: ጠጉሬ ቆሞ ከእሷ ፊት እንዳልናገረው ይሉኝታ ይዞኝ ብሽቅ እንዳልኩኝ ወደ በረንዳ ተጠቃቅሰው ወጡና እንዳው ቡል! . . . ቡል! . . . ሲያደርጉት ትዕግስቴ አልቆ ብድግ አልኩኝ:: 'ውጡ ከዚ! ይዘህ ውጣ!' በቁጣ! ከዚያ ወዲያማ ማን ገላግሎኝ:: ሙልጭ አድርጌ ሰደብኳቸው:: ኧረ እንዲያውም በል በል እያለኝ ከዘራዬን ስነቀንቅ እግዚአብሔር ይስጠው ልጁ አመዱ ቡን እንዳለ ቃል ሳይተነፍስ ተያይዘው ሄዱ::"

"ምኑን ነው የሚያቦኑት?" አሉ የመጀመሪያው አዛውንት::

"ያንኑ ትምባሆአቸውን ነዋ! የሱ ሲነደኝ እንዴት የሴት ትምባሆ አቡናኝ ይዞ ይመጣል ብዬ እኮ ነው::"

"ብቃ ተጣላችሁ?" አለ እንዳለ ጨዋታቸው ፈገግ እያደረገው መጨረሻቸውን ለማወቅ ጓጉቶ::

"ምን ከዚያ በኋላ! እምቢ ብዬ በስንት ወሩ ሽማግሌ ይዞ ይቅርታ ጠየቀኝ:: እሷም አብራ:: ተዚያ ወዲህ እኔ ዘንድ ሲመጡ ተጠንቅቀው ነው:: ብቻ አሁንም ቢሆን ነገረ ሥራቸው አያምረኝም:: የሚበሉት ገዝተው ነው:: ልብስ እንኳን ባጣቢ ነው:: ታዲያ ይቺ ምን ሴት ናት? ቡሃቃ አታውቅ ሌማት:: ቡና እንኳን በኩረንቲ ለማፍላት ተራ ገብተው ነው:: ታዲያ አንዳንዴ ሳስበው ንድድ ያደርገኛል:: የዘመኑ ትምህርት ህሞት ይሰልባል መሰለኝ:: የተማረ ነው የሚባልለት ሁሉ እኮ ጭራሽ የወንድ አሞት የለውም:: ሚስቱን ጠበቅ አድርጎ እያጋጨ መያዝ ሲችል መወያየት መነጋገር ይሉሃል:: ሊያጠፋው ጉድጓድ ከሚምስለት እና ከሚዝትበት ጋር ቀድሞ መሠንዘር እያለ መወያየት መግባባት ይሉሃል:: ሁሉ በውይይት ሁሉ በንግግር:: ኧረ ወዲያ! ምናቸውም አይጥመኝ::"

"ዘመኑ ነዋ! ዘመኑ!" አሉ የመጀመሪያው አዛውንት ቀበል አርገው:: አሁንም መደምደሚያቸውን ወደተነሱበት የዘመን ኩናኔ እየመለሱ:: እንዳለ ጥርሱን በይሉኝታ ቢከድንም ፈገግ እንዲል አስገድዶታል:: የአዛውንቱ ንግግር::

"ስምንተኛው ሺህ! ፈጣሪ አምላክ እሱ ያዘዘው አይቀርም:: 'ያን ጊዜ ተጠንቀቁ ብሏል:: ምጽአቱ እየተቃረበ ነው:: ለዚህ ነው የምድር አበሳዋ የበዛው::"



"እሱማ ነው:: እኛ አንማርም እንጂ ከዚህ በላይ ምን ምልክት አለ!" አሉ ሁለተኛው አዛውንት::

"መጻፉ 'ህፃን ልጅ በእናቱ ሆድ ጥርስ አብቅሎ ይወለዳል' እንዳለው ይኸው ተወለደ:: ሌሎችስ ቢሆኑ ገና በእናታቸው ማህፀን በስለው ነው የሚወጡት:: ከዛሬ ልጆች አፍ የሚወጣውን አዋቂ አይናገረውም" አሉ የመጀመሪያው::

"እኔ እምለው? ውነት ነው እንዴ ይኼ ወሬ?" አሉ ሁለተኛው አዛውንት በጉጉት::

"ታዲያሳ? ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ነው አሉ የተወለደው:: ጥርስ አብቅሎ ፀጉሩ ሸብቶ፣ አፍ አውጥቶ . . ."

"ኧረ ባክዎ!?"

"እናቲቱ በድንጋጤ ወዲያው ሞተች አሉ:: ሲስተሯ ታምማ በነፍስ ትጠበቃለች ይባላል::"

"በስማም ወልደ መንፈስ ቅዱስ! ቁጣ ነው እንጂ:: እኛ አንማርም" አሉ ሁለተኛው አዛውንት በገጽታቸው ጭምር እያጋነኑ::

"ጊዜ እማያመጣው ምን አለ? ስምንተኛው ሺ!" አሉ አሁንም የመጀመሪያው አዛውንት:: እንዳለ የውስጥ ግራ ደረት ኪሱን ቀስ ብሎ ዳበሰ:: የለንበት ትምህርት ቤት መዘምራኑ ተነስተው አስተባባሪያቸው ሲያጨበጭብ ለምቶ ነው:: አዛውንቶቹም ገና ሊናገሩ ያሰቡት መኖሩ ከገጽታቸው እያስታወቀባቸው አፋቸውን ያዙ::

መዘምራኑ እየወረቡና እያሸበሸቡ በማጨብጨብ ልብን በሚለረስር፤ እንኳንስ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮችን ሌላውንም ቢሆን በሚማርክ እና በሚመስጥ ህብረድምጽ ጥዑመ ዜማቸውን እያለዋወጡ ማሰማት ጀመሩ::

"በጐል በጐል
ለባ ለገል . . .
"ዓለም ዓለም
መድሃኔ ዓለም::
"ምህረት ምህረት
የጌታዬ እናት . . .
"እናመስግንሽ የዓምላክ እናት በዝማሬ
የዓለም ቤዛ ነውና የማህፀንሽ ፍሬ::. . .
"በዮሐንስ ተጠመቀ
ያንቺን . . .
በቸርነቱ አወቀን
ከበደል አራቀን:: . . ."

እንዳለ እንዲህ ያለውን ዜማ በሚፈልገው መጠን ጠዋት ስለተከታተለ

የቀረውን ሥራ ለማጣራት አዛውንቶቹን ተሰናብቶ ወጣ:: ጠዋት ምን ያህል እንደተከታተሰና ምን ምን እንደቀረው ለማረጋገጥ በድንኳኑ ጀርባ ደረቱን ለቸሬ ሠፈር ሰጥቶ መሬት ሣሩ ላይ ተቀመጠ::

ያልተስተካከለ አራት ገጽ ሞንጫጭሯል:: ከዚያ ሁሉ ግርግርና ሥነ-ሥርዓት በማስታወሻው ያስቀረው ብዙ መስሎት ነበር:: ነገር ግን ትንሽነቱ ተሰማው:: መቅረፀ ድምጹን ወደ ኋላ መልሶ ከፈታት:: የሰማችውን መድገም ጀመረች:: "ጉልቻ ሰጉልቻ መርመጥ. . ." አሁን ድንኳኑ ውስጥ የቀዳው በመሆኑ ዘጋውና ከኪሱ የመጀመሪያውን ከር አውጥቶ ቀየረ:: ጥሩ ይዞስታል:: ግማሹ ላይ የደረሰበትን የአቡኑ ቡራኬ፣ ከቀሳውስቱና ዲያቆናቱ ያሬዳዊ ዝማሬ፣ ከአማራው ላሌ ጉማ፣ ከዶርዜው ጀነኖ፣ ከትግሬው ጉመዬ፣ ከኦሮሞው ቢሌ፣ ከጉራጌው ላሌ ላሌ. . . ከኈረምሶች ኦርሞኒካ፣ ከኈልማሶች ቀረርቶ ከባልቴቶች ጭብጨባ. . . ከሁሉም ከሁሉም ቀነጫጭባ ይዛለታለች:: እልፍ እልፍ እያደረገ በማጠንጠን ይዘቷን ካረጋገጠ በኋላ በሰበሰበው ማስታወሻ ታግዞ በአምዱ ላይ የሚያስፍረውን ምርጥ መጣጥፍ ከአሁኑ አሰበና ልቡ በደስታ ተሞልቶ ተነሳ:: ለጽሑፉ የሚሰጠውን ርዕስ እያሰላሰለ::

"እምነት የገነባው ባህል" ወይንም "ባህላችን የታሪክ አንድነታችን አሻራ::" ወይንም "ጥምቀት - ትኩረት የሚገባው መንፈሳዊ ቅርስ" ሌላም ሌላም::

አቅጣጫ ያልተመረጠላቸው እግሮቹ አንዱ ሌላውን እየቀደመ በዝግታ ተፈራርቀው በግርግሩ መሃል አሹለከለኩት:: ከልቡ ባልሆነ ቅኝት ስብስቦሽ እየመረጠ ጥቂት ወዲያ ወዲህ እንዳለ አንዲት አነስተኛ የሰው ቀለበት ትኩረቱን ሳበችውና ቆም ብሎ ማዳመጥ ያዘ::

"ፒሪሪም ፒሪሪም የሚለው ቀሚሷ
እንደ ቀርኖ ዱቄት ይጣፍጣል እ. . ."
"ሚያው ሚያው"
"ኧረ ሚያው ሚያው ሚያው"
"ሚያው ሚያው"
"አራት ኪሎ መንገድ ይሸጣል ጥፍጥሬ
ፖሊስ ምን አገባው በገዛ. . ."
"እዛ ማዶ ጋራ ያለው. . .
ጉድ አይቼ መጣሁ . . . ሳር ሲበላ::"
"እዛ ማዶ ጋራ አገኘሁ ቀይ ዱላ
ሴቶች የሚወዱት አጥንት ያለው. . ."

በማይሰባበር አንድ ዜማ ግጥሙን የሚያከታትለው ቃጭልማ ድምጽ የአውራጁን የዕድሜ ግምት ቢነግረውም ጠጋ አለና ወደ መሃል አንጋጠጠ::



በአስራዎቹ መጀመሪያ ዓመታት ላይ የሚገመት ታዳጊ ነው:: በኈረምሶች ታጅቦ እንደተቀመጠ ከመሬቱ ያነብ ይመስል አንገቱን አቀርቅሮ ነው የሚያወርደው::

"እዛ ማዶ ጋራ ተክያለሁ ሙዝ
የሚበላ ሳይሆን የሚወዛወዝ. . ."

"ሚያው ሚያው" ይላል ዙሪያውን የከበበው አዳማቂ በጭብጨባ እያጀበው:: "አንዴ !ሞቅ አርጉት እንጂ! ቸብ ቸብ" ይላሉ ኈረምሶቹ እየተነሱ ክቦሹን በመዞር አየር የተሞላ ላስቲክ ሲፈነዳ የሚሰጠውን ዓይነት ድምጽ የሚያወጡ ሽካራ መዳፎቻቸውን እያጋጬ:: ሞቅ ይላል ጭብጨባው:: የበቃው ተመልካች ሲሄድ አዲሱ ይመጣል:: ሳያውቅ ተጠግቶ ከልጁ እንደበት የሚወጡት ፀያፍ ግጥሞች የቀፈፉትም ከዳር ይመለሳል::

እንዳለ በበኩሉ በልጁ፣ በል በል በሚሉት ኈረምሶችና እንደ ድንቅ ትዕይንት እያደነቀና እየተሳሰቀ በሚያጨበጭበው ተመልካች፣ ከዚያም መለስ እግሩ አድርሶት እንደሰማ ከዳር እየኮነነና እያንቋሸሸ በሚያልፈው ላይ ሁሉ አስተውሎቱን አለዋወጠ::

"የባህል አረማሞ!" አለ በውስጡ ሲያብላላው የቆየውን ትዕዝብት ድምጽ አውጥቶ በሁለት ቃል እየቋጨ:: ሌሎቹንም ተመሳሳይ ክቦች የማየት ፍላጐት አደረበት:: ጧት የሚፈልጋቸውን ባህላዊና ሀይማኖታዊ ሥርዓቶች ለመከታተል ሲጣደፍ ለነዚህኞቹ ትኩረት አልሰጣቸውም ነበር:: አሁን ግን ከመልካምና ማራኪው የባህል ትዕይንት ጐን በየጊዜው የሚያቆጠቁጡትንም የነባሩ ባህል ተጻራሪ ገጽታዎች ማየትና መገምገም አስፈላጊ ሆኖ ታየው:: እናም ወደ ዋናው የእግር ኳስ ሜዳ /ስድስት ኪሎ በር አቅጣጫ/ ዓይኑን አስቀድሞ እግሮቹን አንቀሳቀሰ:: ሞተር የለሽና ባለሞተር ቢስኪሌቶች ከሜዳው ክልል ሳይወጡ እየተተራመሱ ይሽከረከራሉ:: ባለቤቶቻቸው በዙርና በሰዓት የተጋለቡበትን ኪራይ ይሰበስባሉ:: ህጻናትና ኈረምሶችን ያለማምዳሉ:: ድብ ድብ፣ ሌላ ሌላ፣ ላጥ ላጥ፣ ኩሽና ሌሎችም ስም የለሽ የቁማር ዘሮች ደርተዋል::

የበዓለ ጥምቀት ታዳሚው እንደየመሰል መሰሉ ተከፋፍሎ በተወሰነ አካባቢ መሰባሰቡ በየዓመቱ የተለመደ ቢሆንም ዛሬ ሥራዬ ብሎ ሲያስተውለው እንዳዲስ አስገረመው:: በተለይ ቁማርና ቁማርተኞች ከሌላው ባህላዊ ጨዋታ ተለይተው ከዓመት ዓመት በዚህ አካባቢ መሰባሰባቸው::

"ለቁማርና ለቢስኪሌት ብቻ ተብሎ በማስታወቂያ የተከለለላቸው አይመስሉም!" አለ በሃሳቡ::

ሙሉ ራንግለር ለብሶ የፀሃይ መነጽሩን ከግንባሩ በላይ ያቀና ወጣት ተረከዙ ላይ ተቀምጧል:: ከፊቱ ባነጠፈው ካርቶን ያኖራቸውን ሦስት የመጫወቻ ካርዶች አቀማመጥ በሁለት እጆቹ ቶሎ ቶሎ እያለዋወጠ ቆም ይልና ተጫዋች ይጋብዛል::

"ቀይዋን ያየ? ቀይዋን ያየ? ቀይዋ የታለች? ባምስት አስር፣ ባስር ሃያ፣ ባስራምስት ሰላሳ?"

ከበው የቆሙት ሁሉ 'ይቻት – ይቻት' ይጯጯሃሉ:: ከመኻላቸው አንዱ ብሩን ካርታዋ ላይ ጫን ያደርግና ቀይዋን ካገኘ በመደበው እጥፍ ሆኖ ይመለስለታል:: ጥቁር ከሆነ ደግሞ ገንዘቡ ለአጫዋቹ ገቢ ይሆናል:: አዲስ የመጣ እንግዳ እዛው ቆመው ከነበሩት መሃል ማግኘታቸውን ያይና ብሩን መዝዞ ይመድባል:: ይቀልጣል:: እየተበሳጨ የመጀመሪያውን አስመልሳለሁ ሲል ሌላውን ያስወስዳል:: መደቡም ከፍ እያለ በትንሽ ገንዘብ ሲመድብ እንዲጨምር እየገፋፉ ባዶ ያስቀሩታል::

እንዳለ በልጅነቱ ሊለትሮ ሲጠርግ ሳለ ጨዋታውንም ሆነ የማታለያ ዘዴውን ስለሚያውቅ ራቅ ብሎ ሲያስተውል ቆየና ቁማር ተጫውቶ ኪሱን ለማሞቅ ሳይሆን ወጣቱን ለመፈታተን አሥር ብር አውጥቶ ተጠጋ:: ዝርዝር ብር ስላልነበረው::

"ቀይዋን ያየ? ቀይዋ የታለች? ሌላ! ሌላ!" አወጀ ወጣቱ:: እንዳለ አስሯን ብር ከማስቀመጡ በፊት በአምስት ብር መሆኑን ሲገልጽ ወጣቱ በአምስት እንደማይኼድ መለሰለት:: ብሯን ስላያት መሆኑ ገባውና ድፍኑን አንደኛው ካርታ ላይ አስቀመጠ:: 'ይቻት – ይቻት' የሚለው የሌላው ጩኸትና ውትወታ ቀብ አልሰጠውም:: ምድብ ሲነሳ አግኝቷል:: "ይኸው" አለ ወጣቱ::

"ብራቮ ቀንቶሃል!" አለው አንድ ለምርኩዝ ሳይሆን እንደ ቅንጦት ከዘራ የያዘ ሰውዬ ፈገግታ እየሰጠው:: ሦስት ብር መበላቱን ነገረው:: እንዳለ ለሰውዬው አፀፌታ ፈገግ እያለ የወጣቱን የእጅ እንቅስቃሴ ተከታተለው:: በድጋሚ 'ሌላ! ሌላ!' እያለ ሲወተውት ሃያውንም ብር አስቀመጠ:: "እኔም እስቲ ባንተ ዕድል ልጫወት" አለና ሰውዬውም አስር ብር አውጥቶ ጨመረ:: ሲገለበጥ ቀዩ ካርታ ነው:: ገና ሲጭኑ ላብ ላብ ያለው ቁማርተኛ እየተቅበጠበጠ አርባና ሃያ ብር አድርጐ መለሰላቸው::

"አሁን በቃኝ" አለ እንዳለ በዚህ ከቀጠለ በስተመጨረሻ ምን እንደሚመጣ ገምቶ:: ገና ካሁኑ ወጣቱና ከበው የቆሙት ተመልካች መሰል ጓደኞቹ ሲጠቃቀሱ ልብ ብሏል::



"እውነትህን ነው፤ እኔም በቃኝ:: ቁማር እንደሁ አንዴ ከያዙት በልበል ይላል" አለ ሰውዬውም ገለል እያለ::

"ና እንጂ የት ትሄዳለህ? ገና ትጫወታለህ" አለ ወጣቱ::

"በቃኝ!" አለ እንዳለ መንገድ እየጀመረ::

"በልተህ ነው የሚበቃህ? አራዳ!" አለና አንደኛው ተከትሎ ክንዱን ያዝ አደረገው::

"ካልተበላ በቃኝ ማለት አይችልም ማለት ነው?" አለ ሰውዬው ሁኔታቸውን ተመልክቶ::

"አንተን ማን ተናገረህ? አርፈህ ቀጥል" ወጣቱ እንዳለን ጠበቅ አድርጐ ያዘና ሰውዬውን በግልምጫ አንስቶ አፈረጠው::

እንዳለ ክንዱን ለማስለቀቅ ሲመናጨቅ ሰውዬው በያዘው ከዘራ ጉልበቱ ላይ ጨረገደለት:: የያዘውን ወጣት:: ሌሎቹ እንደከበቡት ሰውዬው ፈጠን ብሎ ሽጉጥ አወጣ:: በያቅጣጫው ድራሻቸው ጠፋ:: በከዘራ የተመታው ሳይቀር::

"የታባታቸው እነዚ ሌቦች" አለ ወደ እንዳለ ተመልሶ::

"አመሰግናለሁ! እርስዎ ባይኖሩ ኖሮ ሊጣሉኝ ነበር::" አለ ምስጋናውን ባንገቱም እየገለጸ::

"ምን መጣላት ብቻ፣ ይደበድቡህ ነበር::"

"አመሰግናለሁ!" አለ በድጋሚ::

"ወደ ውጪ ከሆንክ እስከ በሩ ልሸኝህ?" አለ ሰውዬው ሽጉጡን በሱሪው መታጠቂያ ሥር እየሸጐጠ::

"የለም ትንሽ ዘወርወር ማለት እፈልጋለሁ::"

"እንግዲያው አብረን እንሂድ እነዚህ ቀማኞች ካገኙህ ያስቸግሩሃል::"

"ደስ ይለኛል ጌታዬ!"

ተያይዘው መንገድ እንደጀመሩ በእንዳለ ጠያቂነት ስም ተለዋውጠው ተዋወቁ::

"እኔ ጋዜጠኛ ነኝ:: እርስዎ የት ነው የሚሠሩት?"

"እኔ ደግሞ 'ኡጂ' ነኝ:: ኡጂ እጅደለም የሚሉን ወዳጆቻችን፣ ፖሊስ" አለ ሰውዬው እየሳቀ:: 'ወዳጆቻችን' ያላቸው ሌቦችን ነው::

"አሃ! የሚስጥር ፖሊስ ነዎት ማለት ነው?" አለ እንዳለ ትንሽ ደንገጥ ብሎ በመገረም::

"መርማሪ ፖሊስ ነኝ:: በመቶ አለቃ ማዕረግ:: ዛሬ እረፍት ስለሆንኩ ነው የደንብ ልብሴን ያልለበስኩት:: ይኸውልህ ሥራ የፈታ ፖሊስ ቁማር ይጫወታል" አለና በራሱ ንግግር ከት ብሎ ሳቀ::

"እኛስ መች አረፍን" አለ እንዳለ አብሮት እየሳቀ::

"እንዲህ ነዋ! እናንተም አጫውታችሁ አጫውታችሁ ዞር ብላችሁ ትተቻላችሁ:: እኛም እንዲሁ አጫውተን አጫውተን ለቀም ነው:: የሥራው ፀባይ ነው፤ ያለዚያማ መች ይጨበጣሉ?" አለ መቶ አለቃው::

"ኧረ ካመጡትስ አንድ መልስ ያጣሁለት ጥያቄ አለኝ:: ይኼ . . ." ሲል እንዳለ መቶ አለቃ ጣልቃ ገብቶ አቋረጠው::

"አቶ እንዳለ አንቱ እምባል ነኝ እንዴ?"

"የለም መቶ አለቃ:: ካንተ ፈቃዱን እስካገኝ ለአክብሮት እንጂ በዕድሜ እንኳን የምንራራቅ አይመስለኝም::" አለ እንዳለ ለጥያቄው ተግባራዊ ምላሹን ስጥቶ:: መቶ አለቃ ደምሴን ከአርባ አምስት ዓመት በላይ ቢገምተውም ሊያስደስተው ከራሱ ሃያ ሰባት ዓመት ዕድሜ ጋር እያቀራረበው::

"እንዴ! እኔኮ ሰውነቴ ያሳጣል እንጂ ገና ሰላሳ ሁለተኛ ዓመቴን የያዝኩት ባለፈው ጥቅምት ነው::" አለ መቶ አለቃው እያስተማመነ::

በመቶ አለቃው የማይመስል ዕድሜ ከመገረም አልፎ በልቡ ቢታዘበውም በእድሜ ጉዳይ ብዙ ሰው እውነት እንደማይወጣው፣ አይ ቢሉትም እንደሚቀየም ጠንቅቆ ያውቃል::

"ገና ልጅ ነህ ማለት ነው! ሰውነታቸው ሞላ ያሉ ሰዎችኮ ያለ ዕድሜያቸው ነው ትልቅ የሚመስሉት"

"ይቅርታ ግን ጨዋታህን አቋረጥኩህ" አለ መቶ አለቃ::

"አይ ምንም አይደል" ብሎ ቀጠለ እንዳለ::

የኳስ ሜዳው አካባቢ በዓመት በዓመት የጥምቀት ዕለት የቁማር መደብ ሆኖ ሲውል ለምን ፖሊሶች እንደማይቆጣጠሩትና እንዲያውም ቦታው ሆን ተብሎ ለቁማርና ቁማርተኞች የተከለለ መምሰሉን አነሳበት:: መቶ አለቃ ደምሴ ስለጉዳዩ ጠለቅ ብሎ የተከታተለውና የሚያውቀው ነገር እንደሌለ ቢገልጽም የሚመልስለትን አላጣም::

በሱ አመለካከት ዕለቱ የህዝብ በዓል እንደመሆኑ አንዱ የሌላውን ደህንነትና ፍላጐት እስካልነካ በመረጠው መንገድ መዝናናትና መደሰት ይችላል:: በዚህ ተዝናኑ በዚህ አትዝናኑ ማለት አይቻልም:: ፖሊስ የሚከለክለውና የሚቆጣጠረው በቁማር ሳቢያ አምባጓሮና ዝርፊያ እንዲሁም ሌሎች ወንጀሎች እንዳይከሰቱ ነው:: በተረፈ ተስማምተው እና ጥሩ ነው ብለው ከተደሰቱበት ፖሊስ ጣልቃ ገብቶ የደስታቸው እንቅፋት መሆን የለበትም:: በተለይ ጥምቀትን በመሰሉ ህዝባዊ በዓላት የህዝብን ደስታ መጋፋት ያልተጠበቀ ውዝግብ ማምጣት በመሆኑ ሁኔታውን በቅርብ እየተከታተሉ መቆጣጠሩ በቂ እንደሚሆን ሰፋ አድርጐ አስረዳው::



እንዳለ መቶ አለቃው ከነገረው በላይ ሀሳቡን ቢረዳለትም የጋዜጠኛ ሱስ ሆኖበት መጠየቁ አልቀረም:: -ያልታሰበ ቃለመጠይቅ::

"ታዲያ - ይኼ ከጥሩ የደስታ አገላለጽ ባህላችን ጐን ለጐን እያቆጠቆጠ እንዲያውም ከዓመት ዓመት በተለይ በወጣቱ ዘንድ እየደራ የመጣው አልባሌ ልማድ እየቆየ ሲሄድ ዋናውን የበዓሉ ዓላማና ሥነ-ሥርዓት አይጋፋም?"

"ምን ታደርገዋለህ:: ነባሩም ባህል እዚህ የደረሰው በህዝብ ነው:: አሁን የምናየው ባህላችን ጥንት ሲጀመር እንዲህ ነበር ይመስልሃል? እርግጠኛ ነኝ በመጀመሪያው የጥምቀት በዓል ላሌ ጉማና ይኼ እምታየው የብሔረሰብ ጭፈራ እንዳልነበረ ነው:: መቼም ከኔ የተሻለ ታገናዝባለህ ብዬ እገምታለሁ:: የበዓሉ ዓላማ ህዝባዊ እንደመሆኑ በህዝብ ፍላጐት ወደ መጥፎም ይሁን ወደ ጥሩ ቢቀየር እንደበፊቱ መሆን አለበት ብሎ ለማገድ አይቻልም:: ባህልን ለማቀጨጭም ሆነ ለማዳበር ወሳኙ ሰፊው ህዝብ ነው::"

እንዳለ ጭንቅላቱን ነቅንቆ በመቶ አለቃ ሃሳብ መስማማቱን ገለፀለት:: በልቡም የማገናዘብ ችሎታውን አደነቀለት::

"አመሰግናለሁ መቶ አለቃ"

"ልትፅፍብኝ እንዳልሆን ርግጠኛ ሆኜ ነው የቀባጠርኩት:: እናንተ ጋዘጠኞችኮ አትታመኑም" አለ መቶ አለቃ ሁሌም ደስተኛ የሚመስለው ሰፊ ፊቱ ፈገግታ እየፈነጠቀበት::

"እንዴት?" አለ እንዳለ ጆሮውን አቁሞ:: መቼም ስለጋዜጠኛ የሚሰነዘር ጥሩም ሆነ መጥፎ ሃሳብ መስማት ያጓጓዋል::

"ለሥራ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ አትመርጡማ! ለግል ጉዳያችሁ በዋላችሁበት ሳይቀር ለሚዲያ እሚሆናችሁን ማሽተታችሁ አይቀርም:: በበኩሌ ጋዜጠኛና ደራሲ ከሚስቶቻቸው ጋር በሚስጥር ያወሩትን እንኳን ለጽሑፋቸው መንደርደሪያ ከማዋል የሚመለሱ አይመስለኝም" አለው እየሳቀ::

"እንዲህ ልካችንን ንገረን እንጂ!" አለ እንዳለም አብሮት ሳቀና::

"በነገራችን ላይ ግን የየትኛው መምሪያ ጋዜጠኛ ነህ?"

"ፕሬስ መምሪያ ነኝ:: አዲስ ዘመን ባህል ዓምድ::"

"አሃ! እንዳለ ተመስገን? አንቱንማ ካወኩህ ሰንበት ብያለሁ:: ዛሬ ጥሩ አጋጣሚ ነው ማለት ነው:: በጣም ከማደንቃቸውና ከምከታተላቸው ጥቂት ዝግጅቶች አንዱ ያንተ ዐምድ ነው:: ጥሩ ታዘጋጀዋለህ:: ይገርምሃል ከጋዜጠኞቻችን በጣት የሚቆጠሩትን ነው የማደንቀው:: በተረፈ ጋዜጠኛና የኢ.ሠ.ፖ.እ.ኮ. ካድሬ ልዩነታቸው አይገባኝም:: ይቅርታ አርግልኝና ብዙ ጊዜ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ከመከታተል ወይንም ጋዜጦችን በስም ልዩነታቸው ከማግበስበስ ሠርቶ አደር ጋዜጣን በሳምንት አንዴ አንብበህ መገላገል ይቀላል:: ያንኑ ነዋ አይንህ እስኪፈዝ ጆሮህ እስኪበጠስ የሚደግሙልህ:: የገደል ማሚቶ

ሥራ። ለምን ስለፖለቲካ ይጽፋሉ አይደለም። እሱም ቢሆን ሊፃፍለት ሊነገርለት የሚገባ አንድ ነገር ነው። ይሁን እንጂ ነጋ ጠባ በአንድ ዓይነት አገላለጽ እየደጋገሙ ማስልቸት ለሙያው ብቃት ያለመኖርን ያሳያል። ምናለ ስለሌሎች ጉዳዮችም ስለተፈጥሮ ውበት፣ ስለኪነ-ጥበብ፣ ስለ ማህበራዊ ህይወት፣ ስለአገርና ዓለም አቀፍ ተጨባጭ ዕውነታዎች ግንዛቤ የሚሰጡ ዝግጅቶችን በርከት ቢያደርጉ። ፖለቲካውንም ቢሆን የጓድ እንትናን አሥር አሥር ጊዜ ከመደጋገም በራሳቸው ጭንቅላት አስላስለው ለየት ባለ መልኩ ቢያቀርቡት ይቻላል። የሚወደድ ነገርም እኮ ቢሆን ሲደጋገም ስልችቶህ ትጠላዋለህ እንጂ ነጋ ጠባ ጭንቅላትህን ቢቀጠቅጡት አይገባህም።"

እንዳለ የፖለቲካ ውይይት ስለማይወድ በዝምታ ከማዳመጥ በቀር የድጋፍም ሆነ የተቃውሞ ሃሳብ መሠንዘር አልፈለገም። ጉዳዩ ግን እርሱንም ሁሌ የሚያበሽቀውና በርካታ የሙያ ባልደረቦቹንም የታዘበበት ነው። አንዳንዶቹ በቂ ችሎታና ልምድ እያላቸው ሳንሱርና ተጠያቂነትን በመፍራት ራሳቸውን ለአድርባይነት ያጋለጡ ሲሆን አብዛኞቹ ግን የሙያ ብቃትና ፍቅር ሳይኖራቸው በዘመድና በጉቦ ማለትም ፍሪላንስ ሠርተው ያገኟትን ከእነሱ ለቀደሙና ሳሳተፏቸው ጋዜጠኛ ያልሆኑ ጋዜጠኞች በመጋበዝና በማካፈል የተቀጠሩ በመሆናቸው ለድክመታቸው መሸፈኛ ለእንጀራቸው መተማመኛ ብዕራቸውን የሚቀለው 'አብዮታችን በድል ፈንድቶ' ዓይነት ጽሑፍ ነው። ለምን ቢሉ የአብዮቱ ወገን ወይንም አድናቂዎች ሆነው ሳይሆን ሳንሱር የማያግደው፣ ትችትና ግምገማ የማይደፍረው፣ ብዙ ልፋት ብዙ ድካምንም የማይጠይቅ በመሆኑ ነው።

በዚህ የተነሳ የጋዜጠኝነት ሙያ የተናቀ፣ጋዜጠኛም ማህበራዊ ደረጃው የወደቀ ሆነ። አንዳንድ አንጋፋና ሀቀኛ ጋዜጠኞችም ከአድርባይ ጋዜጠኞች እንጻር እየታዩ በባለሥልጣኖች ዘንድ እንደ ፀረ-አብዮተኛና እንደ ትምክህተኛ ተቆጠሩ። ለሞያቸው ክብር ሲሉ ታስረዋል፣ ከሥራቸው ተባርረዋል፣ አንዳንዶችም መድረካቸውን ተቀምተውና ሞራላቸው ወድቆ እንገታቸውን ቀብረዋል። የሙያ ፍቅራቸውን በመጠጥ ፍቅር ተክተው በልዘዋል፣ ፈዘዋል ደንዝዘዋል።

"አዝናለሁ! ከመተዋወቃችን አስተያየት ማብዛቴ ቅር አሰኘህ መሰለኝ?" አለ ዝምታው የመከፋት መስሎት።

"በፍጹም መቶ አለቃ! ይልቁን እውነትነቱ ተሰምቶኝ ነው።"

"ያንተን ዓምድ የምወዳት ከፖለቲካ ንዝንዝ ነፃ ስለሆነች ነው። በተለይ 'ከሠለጠኑት' የምትለዋ ንዑስ ዓምድህን በጣም ነው የምወዳት።"

"ከምን አንጻር?" ሲል ጠየቀው እንዳለ። ድፍን አድናቆት ሽንገላም ሊሆን ስለሚችል ሁልጊዜም አስተያየት ሲሰጡት በጥያቄ ሳይመዝን አይደሰትም፤ አያዝንምም። 'በምክንያት ያልተደገፈ አድናቆትም ሆነ ነቀፌታ ባዶ ነው' የሚል እምነት አለው።

"አንደኛ በተለያየ የዓለማችን ክፍል ስለሚገኙ የተለያዩ ህዝቦች ባህል



ግንዛቤ እንዲኖረን ያደርጋል። ሁለተኛ ደግሞ ራሳችን ያለንበትን በጉም ሆነ መጥፎ የባህል ቀደምትነትና ቀርነት እንድናነጻጽር ይጋብዘናል። አንዳንዶቹም የሥራ፣ የአኗኗርና የኢኮኖሚ ባህላችንን ለማሻሻል ጥሩ ትምህርት የሚሰጡ ናቸው።"

"አመሰግናለሁ! አየሃቸው አሮጊቷን?" አለው ባሻገር ሳሳ ብሎ ገና እሚቋቋም በሚመስል ጭፈራ መሃል ጎርደድ ጉርደድ ሲሉ አይቶአቸው።

"መነኩሴ ናቸው መሰል?" አለ መቶ አለቃም እያስተዋላቸው። ጨዋታ ይዘው ብዙ ክቦችን ሳያስተውሉ ነው ያለፏቸው።

"ቀስ ቀስ የሰውን ሥራ
ኧረ ቀስ የሰውን ሥራ"

ቢጫ የመነኩሴ ቀሚስ ከነቆቡ አጥልቀዋል። ከላይ እንደጋቢ ያጣፉት ጨርቅም የቀሚሳቸው ዓይነት ነው። መቋሚያቸውን አጋድመው እየወዘወዙ ዓይናቸውን በክቡ መሃል እያጨበጨቡ በሚጨፍሩት ሁለት ልጃገረዶች ላይ ሰክተዋል።

የጠይም ቆንጆ ናቸው። ዓይኖቻቸው እንደ አሮጊት የሞጨሞጩ ሳይሆኑ እንደ ጨቅላ ህፃን ጥርት ያሉ፣ ሉጫና ብርማ ፀጉራቸው ከቆባቸው አፈትልኮ 'ልታይ' የሚል፣ ክርክም ያሉ ጥርሶቻቸው ጥቂት ቢወይቡም የሚማርኩ። ገጽታቸው እንደ አሮጊት አልተጨማደደም። ትከሻቸው ሰፋ ሰውነታቸው ደንደን ብሎ እምብዛም ባልተጉሳቆሉ ባዶ እግሮቻቸው ላይ በመካከለኛ ቁመት የተተከለ። ባጠቃላይ ቴምድሮሳዊ ግርማን የተላበሱ ዘንካታ መነኩሴ ናቸው። ሴቴ ለዛውን ሳይለቅ ጎርነን ብሎ ጆሮን በሚያነቃ ድምጻቸው ያወርዳሉ። አጀብተኛው እያጨበጨበ ይቀበላቸዋል።

"እመቤቴ ወልዳው ተወልዷል ጌታዬ
ምን ይገዌ እቀርብ ይሆን ወየው መከራዬ።
የመከረኛ እናት እሷም መከረኛ
ኑሮው እንደ ምስኪን ሞቱ እንደቀማኛ።
ሰላሳ ሦስት ዓመት ሆነች አዘንተኛ።
ቀስ ቀስ የሰውን ሥራ
ኧረ ቀስ የሰውን ሥራ
ቸሩ መድሃኒአለም ታሪክህ ብዙ ነው
ዕንቁላል በላተኛ ሁሉንም አስገባው።
ጉግ ማንጉጉን ሁላ ወደ ደጅህ አምጣው።
ኧረ ቀስ የሰውን ሥራ. . ."

"ምን ታስባለህ ታዲያ?" አለው መቶ አለቃ ደምሴ።

"በሦስት ጆሮዬ እያደመጥኳቸው ነው" አለ እንዳለ 'ቀልጣፋ ጆሮውን'

ክፍ አድርጉ እንደያዙ።

"ማለቴ በዚችው በጃንሜዳ፣ በዚችው አንድ ቀን ያለው የዘመን ድብልቅልቆሽ አስገራሚ እኮ ነው!"

"በጣም! የእኚህ ደግሞ የተለየ ነው። ትክክለኛውን ሀይማኖታዊ ባህል እንደያዙ ናቸው።"

"ዘመናቸውን ነው የሚወክሉት" አለ መቶ አለቃ። "የእኛን ትውልድ ሲተቹት አትሰማም?"

"የእምነታቸውንም ደረጃ እንጂ! ትንሽ ባነጋግራቸው ደስ ይለኛል።" ክቡን እየፈለፈለ ወደ መሃል አለፈ።

"ነይ ነይ እምዬ ማርያም
ነይ ነይ በዛይት ዓለም።
ኧረ እቺ ስጋዬ ብላሽ ናት
ኧረ እቺ ስጋዬ ብላሽ ናት
በኩታ በቀሚስ ሳንቀባርራት
በፈረስ በበቅሎ ሳሞናድላት
በኦፔል መኪና ሳንፈላሰሳት
ኧረ እቺ ሥጋዬ ብላሽ ናት። . . ."

እማሆይ ወለተእግዚአብሔር ይባላሉ። የኪዳነምህረት ገዳም እቃቢት ናቸው። ዕድሜአቸው እምሳ እንድ ሲሆን የመነኩሱት በእሥራ አንድ ዓመታቸው ነው።

"ሳልመለኩስ ቤተለቤ አራት ዓመት ነው የቀጠቀጡኝ። ካላገባሽ ብለው። እኔ ግን ልቤ ወደ ቤተስኪያን ነበረና ወረሞ ሥላሴ /ወረሞ ነው እገሬ/ ነጋ እዚያ መሮጥ ነበር ሥራዬ። ታዲያ መነኩሲቷ እንቅርታም ናቸው። ሁለት እንቅርት ያንጠለጠሉ። 'እማሆይ' ይኼ ምንድነው? እላቸዋለሁ። 'እንቅርት ነዋ! እግዚአብሔር ለምንኩስና እንዲረዳኝ የሰጠኝ። በዚህ፣ ይሉኛል ግራና ቀኝ እንቅርታቸውን እየከፈሉ። 'በዚህ ውሃ በዚህ ጥሬ እይዝበታለሁ' እኔ ታዲያ 'እማሆይ ያለእንቅርት አይመለኮስም?' እያልኩ እጠይቃቸዋለሁ። 'አዎን ልጄ ካለእንቅርት አይመለከስም' ሲሉኝ ይከፋኛል። 'አምላኬ እንቅርት ስጠኝ!' እያልኩ እፀልይ ነበር። ለካስ እሳቸው እትዘልቅም ብለው እንዳልመለኩስ ሲያከላክሉኝ ነው። መቼም እንዴ እግዚአብሔር ልቦናዬን ወደ እርሱ እንዲሆን ፈቅዶ የለ? ከወላጆቼ ጠፍቼ ደብረ ሊባኖስ ሄድኩኝ። ሃያ ዓመት በየደብሩ ዞሬአለሁ። እኔ ያላየሁት የኢትዮጵያ ገዳም የለም። ክብሩ ይስፋ ለፈጣሪ። በልጅነቴ ከተመኘሁት ሁሉ ያላገኘሁት እንቅርትና ትምህርት ብቻ ነው።. . ."

"ዓለምን ምንኛ በደሏት! በጣም ጨካኝ ናቸው!" አለ እማሆይን ካነጋገረ በኋላ ተሰናብተውት የሚካኤል ታቦት ወዳለበት ድንኳን ሲያመሩ በዓይኑ እየተከተላቸው።



"ይኼን መላይ ውበት ለአርባ ዓመታት መከልከላቸው!" አለ መቶ አለቃም ፈገግታ እየቀደመው።

ወደ ሌላ ክብ አመሩ።

## 29

የጃንሜዳን ዝግጅት ከሞላ ጐደል ዳሰሰ የጀምበርን ማዘቅዘቅ የራሱንም መድከም አስተዋለና መቶ አለቃን ተሰናብቶ በስድስት ኪሎ አቅጣጫ ወዳለው በር አመራ:: ራሱን ረስቶ መዋሉን ከደስታ ቆጥሮ የሥራንና የማህበራዊ ኑሮ ተሳታፊነትን ፈውስ አያሰላሰለ:: ለመውጫው እንደቀረበ በድንጋጤ አይሉት ፍርሃት፣ እፍረት አይሉት ብሽቀት በተሳከረ ስሜት ቀጥ ብሎ ቆመ:: ተመልሶ በፈረሰ ክበብ ወይንም ደግሞ በአንደኛ ፖሊስ ጣቢያ በኩል ለመውጣት አሰበ::

"ግን ለምን ያፈገፍጋል? ወንጀል አልሠራ:: ለምን ቀጥታ አይወጣም"

ዓይኑ ግን እንደልቡ ደፋር አልሆነም:: የማይፈቅደውን እንዳያይ ፈራ::

"ለመሆኑ ማን ነው እሱ? . . . ማንስ ቢሆን ምን አገባኝ?" አለ ሃሳቡ እየተለዋወጠ::

በቀላሉ የሚያልፈው ጉዳይ አልነበረም:: ሲጋራውን በኃይል ሰቦ ተንፈሰና እንዳይታይ ርቀት ጠብቆ ተከተላቸው:: ባንድ ልቡ ለጥላቻው ማጥ በቂያ ለምክንያቱ ተጨማሪ ማረጋገጫ የሚሆን ገጠመኝ ለማየት ጓጉቷል:: በሌላኛው ደግሞ እስከ ቅርብ ጊዜ የሚወዳትና አሁንም ቢሆን በሌላ እጅ መግባቷን በዓይኑ ማየት የማይፈልግባት ዳርምየለሽ ከምን ጊዜው ሌላ ለምዳ ስትሽስኮረመምና ስትሳሳቅ ሳለማየት ፈርቷል:: ስሜቱን አስቆጥቶ ተከተላቸው::

ከጃንሜዳ ወጥተው ወደ ስድስት ኪሎ የሚወስደውን መንገድ ሲጨርሱ በአምሮፖ ሞተርስ በኩል አቋርጠው ቁልቁል ወረዱ::

"ወደ ቤቷ ነው ማለት ነው" አለ ለራሱ:: ጥምቀት ውለው ቢሆን እንዲህ ሲሽከረከር ያገኛቸው እንደነበር አስቦ ሌላ ቦታ መዋላቸውንና ጃንሜዳ ብዙ እንዳልቆዩ ገመተ:: አለባበሳቸውን ከኋላ ገመገመ::



እርሷ የለበሰችው የሚያውቀውን ቀሚስ ነው:: ቸኩርኩር ባለአበባ ከተረከዛም ጫማ ጋር:: ፀጉሯ እንደወትሮው ወደ ወገቧ ተለቅቋል:: አብሯት ያለው ሰውዬ አንድ ዓይነት ኮትና ሱሪ ለብሷል:: ካደገ በኋላ የልጅነት ጥብቆውን እንደለበሰ ህጻን የሰውነቱን ውፍረት የሚያስገምት:: ከፊቱ ሊያየው ባይችልም ቁመቱም ሆነ ሰውነቱ በሃሳቡ ከቀረፀው ጋር የተለየ ነው:: ዞሮ ዞሮ ግን ፈጠነ እሚሉት . . . መሆኑን ገምቷል:: በህሊናው ሳለበው ውሎአቸው የሩቂያ በሦስተኛነት መኖር እንደማያመች አገናዘበና ብሽቀቱ ቀነሰለት:: ሌላም ያላሰበው ነገር መጣለት::

ሰውዬው ከሩቂያስ ጋር ቢሆን?'

ያ ደግሞ የማይመስል ነው:: ከሰውዬው ጉን ያለችው ዳርም የለሽ ስትሆን ሩቂያ ከእርሷ ቀጥላ ናት:: ግፋ ቢል መሃላቸው ይሆን ነበር እንጂ ፍቅረኛውን ከዳር አርጐ ጓደኛዋን ከጐኑ የሚያደርግ ወንድ የለም:: ያም ሆነ ይህ ግን አንድ ነገር ርግጠኛ ነው:: ንጹህ ቦታ ለመዋላቸው::

'አይ ይኼም ሞኝነት ነው:: ከሩቂያ ጋር የተገናኙት ከሁለቱ ፕሮግራም በኋላ ቢሆንስ?'

ብሽቀቱ እንደገና ናረ:: ብሔራዊ ሙዚየም አጠገብ ባለው ፌርማታ ተከልሎ ቆመ:: እነርሱም ስለቆሙ:: በተቃራኒው የመንገድ ጠርዝ መብራቱ አጠገብ ደርሰዋል:: ጥቂት ተነጋገሩና ሰውዬው የዳርምየለሽን እጅ ያዝ አድርጐ እንደመጐተት አደረጋት:: ከሁኔታው ወደ አራት ኪሎ በኩል እንዲሄዱ የሚያግባባት፣ እሷም በተቃራኒው እጇን መጐተቷ ተቃውሞ መሆኑ ገብቶታል:: ከተደበቀበት ተንደርድሮ ሄዶ ማላቀቅ ከጀለው:: በሀሳቡም ሙሉ ትርኢቱን ሠራው::

'እንደደረሰ ሰውዬውን በቀኝ እግሩ ጫማ ጥፌ ዘርግቶት ከንዱን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጐ በኩራትና በንቀት ሰውዬውን እየገላመጠ ይዟት ሲሄድ. . .'

ወዲያው ግን የርሷ ተቃውሞ ረታና ሰውዬው እጇን ለቅቆ መንገዱን ወደ ቀኝ አሳበሩ:: እንደተሻገሩም ሰውዬጫና ዳርምየለሽ በአቋረጡበት አቅጣጫ መንገዳቸውን ሲቀጥሉ ሩቂያ ተሰናብታቸው ወደላይ መጣች::

"ሺት!" አለ ለራሱ ከትትሉን ስላቋረጠችበት ተናዶ:: ባለበት ሆኖ ጠበቃትና በፌርማታው ትይዩ ስትደርስ እርሱ በስተጀርባ ቶሎ ቶሎ ተራመደ::

ግንፍሌ ሆቴልን አልፈው ለቤቷ ተቃርበዋል:: ተከታትለው ሲገቡ እርሱ የቤተክህነትን አጥር ተደግፎ ቆመ:: ዓይን ኤክስሬይ አይሆንምና ከዚያ በላይ ማየት አልቻለም:: ብቻ እልህና ንዴት ተናነቀው::

"ምን አበሸቀኝ? ምንስ አገባኝ?" አለ በራሱ ተናዶ:: እንደሞኝ ሲከተላቸው መምጣቱ ቆጭቶት:: በስራችው ጥፋት ተነሳስቶ ራሱ ከተሰናበታት በኋላ ከማንስ ጋር ምንስ ብታደርግ ምን ቸገረው? ከእንግዲህ እንደሁ የእርሱ ልትሆን አትችልም::

"ነው ወይስ እንደገና የእኔ ትሆናለች?"

ያ ደግሞ ሰማይና ምድርን እንደማገናኘት የማይሆን፣ያለቀለት ጉዳይ ነው:: በምንም ይሁን በምን አይፈልጋትም:: ቢፈልጋትም ህይወቱን ለመመረዝና ራሱን ለመጉዳት ካልሆነ በቀር ከእንግዲህ ሳያውቅ እንዳሳለፋቸው የመጀመሪያዎቹ የፍቅር ጊዜያት በርሷ መደሰትና መመካት እንደማይችል ልቦናው ያውቀዋል::

'ታዲያ ለምን ይከተላታል?'

ለራሱም የማይገባው መልስ የሌለው ጥያቄ:: ሲጋራ ሊለኩስ ኪሱን ቢዳብስ ጨርሷል:: ስሜቱ ጨፍግጎ ፊቱ ጭስ እንደመሰለ ቁልቁል መንገዱን ቀጠለ::



# 30

የዳርምየለሽና እንዳለ ፍቅር ሲወጠን ጀምሮ በህብቴ የልብ ልብ ውስጥ ሳይታወቅ ያቆጠቆጠው ዕኩይ ምኞትና ፍላጐት ከሰሞኑ ወደውጪ እያበበ ነው:: ለሁለቱ ፍቅር ቀና አሳቢ፣ እንዳውም ምንም ትኩረት የሌለው መስሎ ቀስ እያለ ለእንዳለ የጋተው የጥርጣሬ መርዝ እንደምንም ሠርቶለታል:: በቀላሉ ግን አልነበረም:: በዳርምየለሽ ጉዳይ የእንዳለ ለወሬ ቁጥብ መሆንና በርሷ ላይ ያለው እምነት በር እየዘጋበት በነገር መሰርሰሩ በቃላት ማንኳኳቱ የዓመታት ጥረትና ትዕግስቱን ጠይቆታል:: ሰሞኑን ግን ያለጥርጥር ተሳክቶለታል:: ምንም እንኳን እንዳለ ሊደብቀው ቢሞክር "በጥበቡ" አውጣጥቶታል::

በዚያን ሰሞን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በእምነት የተዘጋ ልቡን ከፍቶ ያስገባበት የጥርጣሬ ሽውታ ተመልሶ የወጣ መስሎት ነበር:: ሆኖም ከሰሞኑ ተጠናክሮ የፈጠረው እውሉ ንፋስ በእንዳለ ልብ ተቋጥሮ የኖረውን ፍቅር ገለባ አድርጎ እንደጠራረገው ለማረጋገጥ በመብቃቱ ለብዙ ዓመታት የለፋበትን የምርምር ውጤት እንዳገኘ ሳይንቲስት ልቡን አስፈንድቆታል::

ሰሞኑን እንዳለ ጠረጴዛው ላይ በግንባሩ ተደግፎ ቁና ቁና እየተነፈሰና ሲጋራውን በላይ በላዩ እያቀጣጠለ ያበዛው ገለልተኝነት በምን ምክንያት እንደሆነ ለመገመት ባያስቸግረውም በሙከራው ተስፋ ቆርጦ ሌላ መላ ለመምታት ሲሰናዳ ለሁለቱ የወረደባቸው ለእርሱ ግን የወረደለት ዱብዕዳ ምንነት አልገባውም ነበር::

በእንዴት ያለ ሁኔታና በምን ምክንያት እንደተለያዩ አዝኖና ተክዞ ሲነግረው በልቡ ሳይሆን በምላሱ ጠርዝ ኀዘነለት:: የእንዳለን ልብ ያቆሰለው እራሱ የተከለበት መርዘኛ እሾህ መሆኑን እያወቀ ነቃይ መስሎ ዳግመኛ እንዳይሽር አፍረጠረጠበት:: አለስልሶም እያከከ ካሁን ቀደም የቀረውን ሁሉ ሰገሰገበት:: —ህብቴ::

"እኔ በፊቱንም ነግሬህ ነበር" አለው በእርሱ ጋባዥነት ከእንዳለ ጋር የእረፍት ሻይ እየጠጡ ነው:: "ከጅምሩም ቢሆን ያንተና የሷ መርፌ ቁልፍ መምሰል አላማረኝም:: አንተ ግን በጊዜው የሌላ ሊመስልህ ይችላል:: . . . እንዴ! ዘጠና ዘጠኝ ወንደላጤ ከሚንጋጋበት ቤት እንዴት ቁጥብ ሴት

ትወጣለች ብለህ ትጠብቃለህ? ከጭልፊት ሠፈር ጫጩት?"

"በዚ እንኳን አይመስለኝም::"

"ነው እንጂ! አሁንም አታምንም? ወንደላጤ ከቤት ቤት እየዞረ የሚያግርጠው ሆዱን ብቻ መሰለህ? ከድስትና ሞሰቡ ጋር ከተገኘች ቆንጆዋንም ነው አብሮ የሚቀምሰው:: የደባልና የወንደላጤ እግር ከበዛበት ቤት የተከበረች የታፈረች አፍቃሪ መጠበቅ ከጭልፊት መሀል ጫጩት ለማሳደግ ከመመኘት አይለይም:: በበኩሌ የጓደኝነቴን በቀጥታ ተዋት ለማለት ባልደፍርም ያጋጠመኝንና የሰማሁትን ሁሉ አንድ በአንድ ነግሬህ ነበር:: ካንድም ሁለት ጊዜ በቦሌ መስመር ዝንጥ ብላ ስታጋጥመኝ ሁኔታዋ ስላጠራጠረኝ ተከታትዬ ያየሁትን ነግሬሃለሁ::"

"ቦሌ ጓደኛ እንዳለቻት. . ." ሲል አቋረጠው::

"መስሎሃል! በጓደኛ፣ በዘመድ ካልተመካኘማ ምኑን ሸወደችህ! አንዱን ቀን ትልቅ አረንጓዴ በር ያለው ግቢ አንኳኩታ መግባቷን በሌላ ቀን ደግሞ ቦሌ መንገድ 'ፍላሚንጎ ባር' አጠገብ ቆማ ስትጠብቅ ቀይ ቶዮታ መኪና መጥቶላት ወደ ቦሌ መሄዷን ጠቁሜህ ነበር:: በዚያን ሰሞን የፈፀመችውን ውርጃና ታሪኩን ደግሞ ከገዛ የሰፈሯ ልጅ በጆሮህ ሰምተህ መልሰህ ገጠምክ:: አሁን ታዲያ ምን ያልተጠበቀ ነገር መጣ?

"አፈራ ደደሆ አፈራ ደደሆ

የፈራነው ሁሉ መጣ ድሆ ድሆ:: እንደሚባለው ሆነ እንጂ" አለው በጉምዛዛ ፈገግታ::

"ነገሩ ልክ ነው" አለ እንዳለ ውስጥ ውስጡን በሀብቴ አነጋገርና ተረት እየበሸቀ:: ለምን እንደሆነ ለራሱ ባይገባውም ሀብቴ ስለጻርምየለሽ ሲተች ያናድደዋል:: በደሷን ራሱ ሲያስበው የመጨረሻ አድርጎ ቢኮንነውም ከሃብቴ አፍ ሲሰማው የተጋነነና ተገቢ ያልሆነ መስሎ ይሰማዋል:: እንዳይቃወመው ትችቱን አፍርሶ ለማሳመን የሚያበቃ ሀቅ ያጥረዋል:: እናም ውስጥ ውስጡን እያረረ ዝም ይላል::

ሀብቴ፣ ቡተሰይ ጻርምየለሽ በስተመጨረሻ ያደረገችው እንዳለ ለሷ ያለውን ፍቅር ከመረዳት የፈፀመችው ድፍረት መሆኑን ደጋግሞ በማንሳት የተናደደለት መስሎ ይበልጥ አናደደው:: ያዘነለት መስሎም ይበልጥ አሳዘነው:: በክብሪቱ ላይ እንጨት ቆስቁሶ የንዴቱን ነበልባል ሲያይ ዳግማኛ እንደማይበርድ አረጋግጦ ልቡ ጮቤ ረገጠ::



# 31

"ግን እኮ እሷም አትጠላኝም" አለ ፈጠነ ሰዓቱን አይቶ ከመኝታው ቀና እያለ:: አንዳንዴ ዳር ዳር ሲላት ብታመናጭቅና ፊት ብትነሳውም እንዳላኮረፈችው በማሰብ::

"ካልጠላችህማ ለምን መጀመሪያ ከርሷ ጋር አትጨርስም ነበር?" አለው አለነ በራሱ መኝታ እንደተጋደመ::

"እሱንማ ነገርኩህኮ፤ ሳናግራት ቅን አትመልስልኝም:: ደህና ስታጫውተኝ ትቆይና ቁም ነገር ሳነሳባት ስል ትቆጣለች፤ አስቀድማ ትኮሳተርብኛለች::"

"ከጅምሩማ ካጣጣለችህ በቃ ቀድሞ ነገር አታስበውም ማለት ነው" አለ አለነ ፍርጥ አድርጎ::

"አታጣጥለኝምኮ!" አለ ፈጠነ የአለነ አነጋገር አብሽቆት::

"እንግዲያማ ምንድነው? ተተኮሳተረች፣ ተተቆጣች ብትጠላ መስሎኝ?" አለ ከእርሱ ይልቅ ስልጥኛለሁ የሚለው አብሮ አደጉ መጃጃል በበኩሉ እየነደደው::

"የባላገር ነገር! መቼ ጨረስኩና! ሴት ልጅ እኮ ካንጀት ለወደደችው ግልጽ አትሆንም:: እንዲያውም ከወደደች ቀና መልስ አይወጣላትም:: ቁጣ ቁጣ ኩርፊያ ኩርፊያ ነው የሚላት:: በተለይማ ተሰው ፊት ሲሆን!" አለ በማስተባበል ነገሩን ወደራሱ የሃሳብ ፍላጎት እያቀራረበ::

"አሁን የጥምቀት ለት ያገኘኋት ጊዜ ተሌላው ጊዜ ሁሉ ተስማምተን ነው የዋልነው:: ምን እነግርሃለሁ ራስህ አይተሃት የለም:: . . ."

"እኮ ያው ተሁለቱ ሰውነቷ መለስ ያለችዋ አይደለች? ጠጉሯን አንዠርጋ ቸርጉርጉር የለበሰችው?"

"አዎን አልኩህ! ስንት ቀን ልንገርህ! ተጃንሜዳ ወጥተን ስንንሸራሸር ቆየንና አብረን ስንገባ እናቷ እንዴት ደብ አላቸው መሰለህ:: ፊታቸው ፈክቶ ሽቁጥቁጥ አሉ" አለ ፈጠነ አለነ ክርክሩን ትቶ እንዲያደምጠው በመፈለግ::

"እንጃ!"

"እንዴት እንጃ?"

"አልመሰል ቲለኝ ነዋ! ያችን የመሰለች ያዲሳባ ሸጋ መቼም ጠፍራሙ የመሬ ባላገር አገባት ሲባል ታሁኑ. . ." ሲል አቋረጠው::

"ማነው ጠፍራሙ? ማነው ባላገር? እኔ ፈጠነ መሬም ሳለሁ ስልጡን ነኝ፤ እንኳንስ ከተማ ተመጣሁ:: አንተ እንጂ እድሜልክህን እማትሰለጥን:: ታገርህ ተመጣህ ያለ ሸንኮራ መሸጥ የማታውቅ:: ስስሙ ተወመኔ መሀል ነው

የምትውለው:: ለነገሩማ ወመኔና እረኛ ምን ለየው" አለው ብሽቅ እንዳለ:: አለነ ሁልጊዜም እንዳበሸቀው ነው:: አለነ በገጠር አብሮ አደጉ ሲሆን አዲስ አበባ የገቡት አብረው ነው:: ከአሥራ አራት ዓመት በፊት::

እንደመጡ ጥቂት ሰሞን በየቤተክርስቲያኑና በየበረንዳው እያደሩ ከተንገላቱ በኋላ ፈጠነ ስምና አድራሻቸውን ገጠር ሆኖ ባጠናው መሠረት አጎቱን አፈላልጎ ያገኛል:: ሁለቱም በጥገኝነት እርሳቸው ዘንድ ይገቡና ፈጠነ በነበረው የቤተክህነት ትምህርት ጉላ ሚካኤል ቤተክርስቲያን በድቁና ሲያገለግል አለነ የቀን ሥራ ዘንቢልና ከረጢት መሸከም ይጀምራል::

ከአራት ዓመት አገልግሎት በኋላ ችሎታውና ፀባዩ ያስደሰታቸው የቤተክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ከጠቅላይ ቤተክህነት ሰዎች ጋር ተነጋግረው በትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አስቀጠሩት:: ትምህርቱንም በማታ ከአምስተኛ ክፍል ጀመረ:: ከዚያ በኋላ ከቀን ወደ ቀን በሥራም ሆነ በዘመናዊ ትምህርት ራሱን አሻሽሎ የአሥራ ሁለተኛ ክፍልን በማጠናቀቅ የጥራዝ ክፍል ኃላፊ ከሆነ ሁለት ዓመት አልፎታል::

አለነም ከዘንቢል ሸከማ ወደ ሎተሪ፣ ከሎተሪ ወደ እቸሎኒ አዟሪነት ካለዋወጠ በኋላ ሸንኮራ ላይ ሲደርስ ተስማምቶት በበቆሎና ሸንብራ እሸት ንግድ እያጀበ አሁን በፈረንሳይ ለጋስዮንና አካባቢው የታወቀ ሸንኮራ ነጋዴ ሆኗል:: ከዚያ በተረፈ ንግስ ባለበት ቤተክርስቲያንና በዓል በሚከበርበት ሁሉ ሸንኮራውን ለንደቅ አስመስሎ ይገኛል::

ሁለቱም በሚያገኙት ገቢ ተረዳድተው ራሳቸውን ለመቻል በመለማማታቸው ከፈጠነ አጎት ቤት ከወጡ ሰምንት ዓመታቸው ነው:: አሁን ያሉባትን ቤት ተከራይተው የነበሩ አሮጊት ምንም ዘመድ የሌላቸው ስለነበሩና እርጅና ተጭኗቸው እቤት በመዋላቸው፣ በየጊዜው ሞቱ ቀሩ እያለ ያካባቢው ነዋሪ በሚጥልላቸው ጉርሻ እንደሚተዳደሩ አንድ አብሮት የሚሠራ ሰው ይጠቁመዋል:: ከዚያም አሮጊቷን አግባብተው የቤት ኪራያቸውን እየከፈለ እንደ እናት ሊጦራቸው ተዋውሎ ከአለነ ጋር ገቡ:: አሮጊቷም በተለይ አለነ ሲንከባከባቸው ከዓመት በላይ ቆይተው ሞቱ:: ከዚያ በኋላ የቤቱ ባለመብቶች ሆኑ::

ታዲያ በዚህ አብረው በኖሩበት ጊዜ ሁሉ ለቤቱ መሻሻል አንዳንድ ዕቃዎችን በመግዛት ሃላፊነቱን የወሰደው ፈጠነ ነው:: የእንጨት ወንበሮችና ጠረጴዛ፣ የመታጠቢያና ውሃ መያዣ፣ የመመገቢያና የማብሰያ ቁሳቁሶች፣ ቡሃቃና ሌማት ሳይቀር ገዝቶ አስቀምጧል:: በዚህም የቤት ባለቤትነቱ እየጐላ ከመምጣቱም በላይ እርሱ ዳርምየለሽን ሲያገባ አለነ ቤቱን ለቅቆ ሌላ ዘንድ ሊገባ ተስማምተዋል::



"ይልቅ ቁምነገሩን እናውራና ይሁን ተተባልክ ሠርጉን ለመቼ ታረገው ነው?" አለ አለነ አሁን ከልቡ ነው የጠየቀው::

"ለከርሞ አይሻልም? ወደ ጥቅምት ገደማ አስቤአለሁ:: እስከዚያው አንዳንድ ነገር ማሟላት አለብኝ:: የሙሽራ ልብስ፣ ጌጣጌጥ፣ ይቀረኛል::"

"ሚዜስ ሚዜ መርጠሃል?"

"የሚዜው ቀላል ነው:: አማረ፣ ያው እማይቀር ነው:: ሌላ ሁለት ወይንም ሦስት ሰው ከእንግዲህም ቢመረጥ ይደርሳል" አለ ፈጠነ የፊት መታጠቢያ ውሃ እያዘጋጀ::

"እንዴ! ታሁኑ ሁነኛ ሁነኛ ሰው መያዝ ያስፈልጋል" አለው አለነ::

"ብዙ ሰዎች አሉ:: ከመሥሪያ ቤት ባልደረቦቼ ከነአጐቴ ሠፈርም ከዚሁም አካባቢ የማስባቸው ሰዎች አሉ" አለ በህሳቡ ምስላቸውን እያማረጠ::

"እኔንስ ሚዜ አታደርገኝም?" አለ አለነ አብሮ አደጉ እርሱን ትቶ ሌሎችን ሲቆጥር ታዝቦት::

"አንተማ የራሴው ነህ:: እሚድር ወንድም ሚዜ ይሆናል እንዴ!" አለ ፈጠነ ጥያቄውን በዘዴ ለማለፍ እያሳሳቀ::

"በል ተወው:: ድሮስ ሸንኮራ ነጋዴ ሚዜ ሊሆን ነው?"

"እንደሱ አይደለም አለነ:: ከፈለግከም ሚዜ ላደርግህ እችላለሁ:: ለኔ ግን የሚበልጠው ደጋፊ፣ ተጠሪዬ ብትሆነኝ ነው:: እዚህ በሰው አገር ማን አለኝ ብለህ ነው? ያው አጐቴና አንተ ናችሁ:: ሠርግኮ ሚዜ ብቻ ሳይሆን ከዛ የበለጠ ሁነኛ ዘመድ ይፈልጋል::"

"ገብቶኛል፣ እኔም እንዳው ልቀልድህ ብዬ እንጂ መች አጣሁት" አለ አለነ ከቅሬታው መለስ እያለ:: "ይልቅ ለድግሱ በሚያስፈልግህ ሁሉ በገንዘቡም በምኑም እንረዳዳለን:: ባለኝ አቅም ሁሉ የወንድምነቴን አግዝሃለሁኝ::"

"እኔምኮ ይኼንኑ አውቄ ነው ሚዜ ያላደረግኩህ:: ሚዜ ሲመረጥኮ ገና ለወደፊት ዘመድ እንዲሆን ነው:: አንተና እኔ መቼም ካንድ ሆድ አንውጣ እንጂ ወንድማማቾች ነን:: 'መወለድ ቋንቋ ነው" አለ ፈጠነ የአለነ በገንዘብ ጉዳይ አግዝሃለሁ ማለት ውስጥ ውስጡን እያስደሰተው:: ጥሩ ገንዘብ ቀባሪ መሆኑን ያውቃል:: ትክክለኛ መጠኑን ባያውቅም በአራት ኪሎው 'አዲስ ባንክ' የቁጠባ ሂሳብ እንዳለው ሲያስቀምጥ ያዩት የሠፈር ሰዎች ነግረውታል:: ካልሰሰተ በቀር ሠርጉን ለመደገስ የማይናቅ ድጋፍ ሊሰጠው እንደሚችልም ገምቷል::

ፀጉሩን አበጥሮ አለባበሱን አስተካክለና ወጣ:: -ወደሥራ::

# 32

"ሳቢ ነኝ!" አለ የስፖርት ዓምድ አዘጋጁ ኢብራሂም ስልኩን አስቀምጦ የሰማውን ድምጽ በሽሙጥ እየደገመ:: የአቶ ስምኦንን አምድ የሚመለከት የተሳታፊ ደብዳቤ በስህተት እርሱ ጋር ደርሶ ሊሰጠው ከሌላ ቢሮ መጥቶ ነው ስልኩን በቁሙ ያነሳው:: እንዳለ ጠረጴዛው ላይ አቀርቅሮ በሥራ የተጠመደ ይመስላል::

"ሀብቴ ዝናቡን ፈልጋ ነው:: 'እፈልግሃለሁ በልልኝ' አለችኝ:: አንቱ ልሁን አንተ በምን አወቀች!"

"እሷ ይኸው ናት፣ የስልክ ሥነ-ሥርዓት የላትም" አለ አቶ ስምኦን እርሱም ሲያነሳ 'አንተ' እንደምትለው እስታውሶ::

"ሳቢ ማለት ይቺ ወንዳወንዷ አይደለች?" ሲል ጠየቀ ኢብራሂም አጥ ቋት ሳይሆን በርሷና በሥራ ባልደረባቸው ላይ ዘወትር የሚሰማውን አስተያየት ለመወርወር መንደርደሪያውን ሲያመቻች::

"አዎ! የሀብቴ. . . ምን እንደምትባል እንጃ:: -ገርልሀ ናት ሲሉት አይደለችም ይላል:: ሁልጊዜ ግን አብሯት ሲሽከረከር ይታያል" አለ አቶ ስምኦን::

"እሱማ ለኔም ሌላ ሴት ታጣብሰኛለች ነው ያለኝ:: ሁኔታቸው ግን እንደዛ አይመስልም:: አንድ ቀን እንዳውም መሃል መንገድ ላይ በጥፊ ላሰችው ብሎ ያየ ሰው ነገረኝ::"

"ኧረ ባክህ! እሷ ታደርጋለች" አለ አቶ ስምኦን ከት ብሎ እየሳቀ:: "እና ዝም አላት?"

"ምንም አላላት፣ አብረው ወደ ስድስት ኪሎ አቅጣጫ ወጡ አሉኝ:: ፎንቃ ሳይዛት አይቀርም:: ፎንቃ አይደል የሚባለው በአዲሱ የአራዶች ቋንቋ:: ከእርሱ ጋር ከገጠሙት እነዛ ጆሊ ጆሊ ጓደኞቿን ሁሉ ችላ ብላቸዋለች አሉ:: እንደድሮው ብዙ አብረው አይታዩም" አለ ኢብራሂም::

"ስሞኑን ደግሞ ቀሚስ ለብሳ እየኋት፣ ሴትነቱ ሳያምራት አልቀረም" አለ አቶ ስምኦን የንባብ መነጽሩን አውልቆ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠና ወደ ጀርባው እየተለጠጠ::

"አይተሃታል? ድፍን አራት ኪሎ ሰሞኑን እንደተአምር የሚያወራው እሱን ነው:: 'ሳቢ ጋይድ ተገየደች' 'ሳቢ ቀሚስ ለበሰች' የሰሞኑ የአካባቢው ወጣቶች ወሬ መክፈቻ ነው:: እንደ በፊቱ መንቀዥቀዥ የለ መላከፍ:: ስታልፍ



ስታገድም እንጂ እንደድሮ ደረቷን ነፍታ መገተር ሁሉ ትታለች አሉ::"

"ያራት ኪሎ ልጃገረዶች አረፉ በለኛ!"

"የሆነ ጋዜጠኛ . . . አንድ ጥርሱ ገጠጥ ያለ . . . አንድ ብርሃንና ሠላም የሚሠራ . . . ይሉሃል"

"ምን የሆነው?"

"የገየዳት ነዋ! ሀብቴ ዝናቡን እኮ ነው:: 'አውርዷታል. . .' 'በጣም ትወደዋለች. . . እሱ ነው ቀሚስ ያስለበሳት . . .' ምን የማይወራ አለ መሰለህ" አለ ኢብራሂም ከተለያዩ ሰዎች የሰማውን ቀጣጥሎ::

ስለ እርሱ እየተወያዩ ሳለ ሀብቴ ዝናቡ በመምጣቱ ጨዋታቸው ተቋርጦ ኢብራሂም ወደ ቢሮው ሲሄድ አቶ ስምኦን የስልኩን መልዕክት ነገረው::

ሀብቴ የሰዓት መቆጣጠሪያውን የጥዋት ፊርማ ፈረመና ተመልሶ ወጣ:: ለምናልባቱ ባካባቢው ትገኛለች ብሎ ወደገመተው ሁሉ ሄዶ ፈለጋት:: የለችም:: በቱሪስት ሆቴል አጠገብ ቁልቁል ወርዶ ወደ ግራ ታጠፈ:: ካሁን ቀደም ያመላከተችው ቤት በስተቀኙ ያለው አጥር አልባ ባለተራ የእንጨት መዝጊያ ነው:: ግጥም ብሎ ተዘግቷል:: ከውስጥ::

እስከምንጫቁ የተለቀቀው የባዕድ ሙዚቃ ከውስጥ ላለ ሰው መድፍ ቢተኮስ የሚያሰማ አይመስልም:: ሀብቴ በቆመበት አመናታ:: ለምን እንደሆነ ባያውቀውም ወደዚህ ቤት ሊመጣ ቀርቶ እርሷ ስታነሳበት እንኳን ደስ አይለውም:: እንዳውም 'ከቤ -ማይክ -ዴቪድ' እያለች የወንድ ጓደኞቿን ስም በሰበብ ባስባቡ ስትጠራ እና ስለጫት አቃቃማቸው፣ ስለመጠጥ አጠጣጣቸው፣ /እርሷ ውጦሽ ወይንም ጨብሲ የምትለው/ ስለ አጫጫሳቸውና ስለ ሁለመናቸው 'ጆሊነት' ስትተርክ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ታበሽቀዋለች::

ሊመለስ ፈለገ:: ሆኖም እስከአሁን የሚከነክነው ጉዳይ አለ:: እንደተቀራረቡ ሰሞን የምትገኝበትን ካመላከተችው በኋላ "የለችም ከተባልክ እንዳትገባ" ብላ ያስጠነቀቀችው:: ለምን? አንድ ቀን ከአስፋልቱ እንደቆመ ትንሽ ልጅ ልኮ የለችም ተብሎ ተመልሷል:: ሌላ ቀን ደግሞ እንደዚሁ በህፃን አስጠርቷት በውጪ ነው የመለሰችው:: መዝጊያው እስኪንቃነቅ ጠንከር አድርጐ ደበደበው:: የሙዚቃው ድምጽ ቀነሰና የመዝጊያው መወርወሪያ ሲሳብ ሰማ:: ወዲያው አንድ ወጣት በሩን ገርበብ አድርጐ በአንገቱ ብቅ አለ::

"አቤት? ምን ነበር?" አለው በሲታሴት ያነጋገር ዘይቤ:: ወጣቱን በዓይን ያውቀዋል:: ፊት ጊዜ ከሳቢ ጋይድ ጋር የማንድና ቅርንጫፍ ያህል ከማይለያዩት ሦስት ጓደኞቿ አንዱ ነው:: ግራ ጉንጩ በጫት ተወጥሯል::

"ሳቢን ፈልጌ ነበር:: ሳቢን?" አለ ሃብቴ::

ዳርምየለሽ ባህሩም በኋላኛው ሁኔታ ወርሃ ጥቅምት ላይ በ'የማን ልጅ ነኝ?' ጥያቄ እንድ ብሎ የጀመረ ችግሯ የፍቅር እጦቷን ከማህፀኗ መዳበር ጋር እያይዞ በመምዘዝ እዬዬና ብሶቷን አከፍቶታል። በዝምድና ከእናቷ፣ በወዳጅነት ከሩቂያ የቀረበ ባይኖራትም የደረሰባትን ሁሉ ከጅምሩ ከማማከር ይልቅ እንዳያውቁባት ቅርበታቸውን ፈርታ ስትሸማቀቅና ስትሳቀቅ እሷና ጭንቀት እንደተቆራኙ ወራትን ቆጠረች።

ያገኘችው መፍትሔ ባይኖርም ራሷን ከጉዳች በኋላ በብዙ ማውጣጣትና ውትወታ ባባት ጉዳይ የደረሰባትን ጭንቀት ለእናቷና ለሩቂያ አካፍላለች። ያንን ሳትገላገል፣ ህይወቷን ሰጥታ ለእስከ ህይወቷ ፍጻሜ ያመነችው እንዳለ ያለበደሏ የበቀል ቅርሱን አሸክሞ ጀርባውን ሰጣት። የፍቅርን ጣእም በርሱ እንዳየችው ሁሉ የመለየትንም መራራነት አቀመሳት። ዳግመኛ ፍቅር ቀርቶ የአዳምን አምሳል ቀና ብላ ሳታይ አስማላት።

በዕለቱ ገና በዚያ ጭር ባለው ጫካ /የቀድሞ መነን መናፈሻ/ በፍቅር ሥም ካለጊዜው የመጣባትን እንከን ስትገልጽለት አረካክሶና አበሻቅጦ ከተለያት ሦስት ወራት አልፈዋል። የዚያን ዕለት ከወደቀችበት ሊያነሳት ሲጠጋ እጁን ገፍታ አፈር የፋቀው ግንባሯን እያሸችና ደረቷን እየደገፈች እንባዋ ሲንዠቀዠቅ ምንም እንዳልደረሰባት ሁሉ በእልህ ቶሎ ቶሎ እየተራመደች ነበር ወደ ቤቷ የበረረችው።

ባጠገባቸው ስታልፍ መለስ እያሉ በመገረምና በርህራሄ የሚያስተውሏትን ወይንም በራሳቸው ግምት የደረሰባትን እስበው ከንፈራቸውን የሚመጥጡላትን ወይንም የሚስቁና የሚጠቃቀሱባትን ሁሉ ለማስተዋል በመላ ሰውነቷ የሚንተገተግ ንዴትና ደም ፍላቷ ጋርዷት 'ስቅ' እያለች በደመነብስ ቤቷ ገባች።

የገና ምሳ ለማድረስ ተፍ ተፍ የሚሉት እናቷ፣ ሳሉን ተቀምጠው ሥጋ የሚዘለዝሉት አባቷ፣ ሁለቱ እህቶቿና ወንድሟም ከየነበሩበት ተደናግጠውና ተጠራርተው ከበቧት። ምን እንደሆነች ሲጠይቋት የበለጠ ሆድ ብሷት ብታነባም ወድቃ መሆኑን ገለፀችላቸው። እምነው ሳይሆን ከእርሷ ወዲያ የሚያውቁት ምክንያት ባለመኖሩ እየከነከናቸው ሥራ ሥራቸውን ቀጠሉ።

እሷ ግን አዕምሮዋ እረፍት አልነበረውም። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የፍቅርን ክፋት፣ የወንዶችን ክህደት፣ የሴቶችን ተላላነት፣ ያ ከመጻህፍት ታነበው የነበረውና ከጅምሩ በፍቅርና ወንዶች ላይ የአመለካከት ተጽዕኖ አሳድሮባት የነበረውን ሁሉ እያብሰለሰለች፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ከገባችበት የህይወት ማጥ የምታመልጥበትን መንገድ ስታወጣና ስታወርድ ነው የከረመችው።



የካቲት አሥራ ሁለት ሆስፒታል ተመርምራ የሰባት ሳምንት ያህል ቅሪት እንዳላት የተገለፀላት ዕለት መደንገጧ ባይቀርም በእንዳለ ላይ የነበራት እምነት ከፍተኛ ስለነበረ ብዙም አልተጨነቀች። ህይወቷን ሰጥታው ህይወቴን ሰጥቼሻለሁ የሚላት እንዳለ ብልሃትና ጥረቱ እንኳንስ ለእርሷ ለሌላውም እንደሚተርፍ አልተጠራጠረችም። በቀላል የምታስወጣበትን መንገድ እንደሚፈልግላት ካልተሳካም ችግሯን ወደ ደስታ ለውጦ እንደሚቀበላት፣ እንዲያውም አጋጣሚው የጋብቻ ጊዜያቸውን ሊያፋጥነው እንደሚችል አስባ ነበር። አሳቧ ግን ከአሳብነት አላለፈም። የታመነችለት እንዳለ ከዳት። እሷን ከችግሯ ጋር አጋፍጦ ገሸሽ አለ።

ከተለያዩ በኋላ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንታት ማንም ሳይሰማ ለማስወጣት ሞክራ ነበር። አምፒሲሊኑን፣ የጨው ሙሚቱን፣ በደህና ቀን እንደዋዛ ጽንስ ማስወረጃ ነው ሲባል የሰማችውን ሁሉ ተጠቅማለች። አንዳቸውም ውጤት አልሰጧትም። በዝና ከምታውቃቸው የቀራት ነገር ቢኖር አንድ ብቻ ነው። እሱንም ለመጨረሻ የሞት ሽረት ሙከራዋ በሃሳብ ደግሳዋለች።

♣ ♣ ♣

ዕለቱ እሁድ ደብረዘይት በዋለ በሳምንቱ ነው። የቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ወፍራም የብርድ መከላከያ ልብሶች በለበሱና በተከናነቡ ምዕመናን ተሞልቷል። አብዛኞቹ በድምጽ ማስተላለፊያው የሚሰማውን ሥርዓተ ቅዳሴ ሲከታተሉ አንዳንዶቹ ደግሞ በተጨማሪነት መጽሐፍ ቅዱስ አለዚያም ልዩ ልዩ ውዳሴና ድርሳኖችን ይዘዋል። ከነዚህ ሌላ ቤተክርስቲያኒቱን ከውጪ አለዚያም ገባ ብለው በመሳለም የሚመለሱም በርካታ ናቸው።

"ለምን አስቀድሰሽ አብረን አንሄድም አሉ ወይዘሮ ብዙ ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው ወደ እርሷ በመጠጋት።"

"ተመልሼ ብተኛ ይሻለኛል።" አለች እርሷም እንደርሳቸው ዝቅ ባለ ድምጽ።

"ምነው? ምን ሆንሽ?" አሉ ጥቂት ደንገጥ ብለው።

"ምንም አልሆንኩም ትንሽ ራሴን ስላመመኝ እንዳይብስብኝ ፈርቼ ነው። የመጣሁትም ተሳልሜ ለመመለስ ነው።"

ብዙም ጫን አላሏት። በመመለሷ ተስማምተው ወደ ውስጥ ዘለቁ። ዳርምየለሽ አጥሩን በግንባሯ ደገፍ ብላ ፀሎት አደረገች። "እባታችን ሆይ. . " ብላ ጀመረችና ስትጨርስ ወደ ራሷ ብሶት ገባች።

"እባክሽ ድንግል ሆይ! በቃሽ በይኝ" አለች እንባዋ እየቀደመ። "ይቅርታህን ጌታዬ! ምህረትህን ላክልኝ ከተዘፈቅኩበት የመከራ ማጥ አውጣኝ!

ያላንተ ረዳት የለችምና ማረኝ::" የህዘን ሲቃ ጉሮሮዋን እንዳነቀው እንባዋን በለበሰችው ነጠላ ጫፍ እየጨመቀች ወደ ቤቷ አቅጣጫ አመራች:: ፈጠን ፈጠን እያለች::

እቤት ስትደርስ አስናቀች ተነስታ ወለሉን ስትጠርግ አገኘቻት:: መኝታ ቤት ገባችና ቀስ ብላ ወደ አልጋው ተጠጋች:: የኑንሺን ሁኔታ ለማረጋገጥ:: አቶ ባህሩ ክፍለ ሀገር ሲሆኑ ኑንሽ የምትተኛው ከእናቷ ጋር ነው:: ፊቷን ወደ ግድግዳው መልሳ በማንቀላፋት ላይ ናት:: ዳርምየለሽ ወደኋላዋ ተመለሰችና በሩን በዝግታ ዘጋችው:: ጫማዋን እዚያው አውልቃ በጣቷ እየረገጠች ወደ ቁምሳጥኑ ተጠጋች:: ፊልጋ ሳይሆን ከፊቱ በመቆሟ አሮጌው መስታወት የሚያሳያት እንቅስቃሴ ራሷን አስፈራት:: ምስሉ የሷ መሆኑን ተጠራጥራ ሽሺ ሽሺ አስኛት:: -ፈራች::

ራሷን አረጋግታ መቆለፊያውን ስታስተውል በላዩ ላይ አልነበረም:: በስጨት አለችና ለማረጋገጥ የተከፋቹን እጀታ ሳብ አደረገችው:: አልተከፈተም:: ነገር ግን ተስፋዋን አሟጥጣ ለመመለስ አልፈለገችም:: ቁልፉን ይዘው እንደማይሄዱ ርግጠኛ ናት:: ብዙ ጊዜ ከላዩ ላይ ከተነሳ እመኝታቸው ራስጌ ከፍራሹ ሥር እንደማይጠፋ ታውቃለች:: የኑንሺን እንቅልፍ እንዲያበረታላት ፈጣሪዋን በልቧ ተማፅነችና በጥንቃቄ ፍራሹን ከጠርዙ በኩል ቀና አድርጋ አየችው:: -የለም:: ከዚያ በላይ ብትገልጠው እንደምትቀሰቅሳት ስለሰጋች ጣቶቿን ዘርግታ በዝግታ ሰደደች:: ቁልፉን ነካችው:: ለመያዝ የበለጠ ማስገባት አለባት:: ቁልፉን ከነመያዣው ስትስብና ኑንሽ ወደርሷ በኩል ስትገላበጥ አንድ ሆነ:: ዳርምየለሽ እንደሌባ ልቧ ሲንቀጠቀጥ "ምን ሆንሽ?" አለቻት ኑንሽ ድንጋጤዋ ተሰምቷት:: ለምን እንደሆነ ግን አልገባትም:: መልስ ሳትሰጣት ወጥታ ሄደች:: አልቀናትም::

በጓሮ በኩል የቤቱ ውሃ ልክ ላይ ተቀምጣ ትንሽ እሰላሰለችና አንድ ሌላ ዘዴ መጣላት:: "ከሌብነቱ ሳይሻል አይቀርም" አለችና ተነሳች:: እማማ ሸዋ ቤት ስትሄድ በራቸው ከውጭ ተቆልፎአል:: በሙከራው ሁሉ ያስመሳካት ከእድሏ ጋር እየተነጫነጨች ስትመለስ እርሳቸው ከቤተክርስቲያን ወደ ቤታቸው ሲመጡ አገኘቻቸው::

"ምነው በጠዋት ልጄ! በደህና ነው የፈለግሽኝ?" አሉ ሰላምታ እንደተለዋወጡ እርሳቸው ዘንድ ደርሳ መመለሷን ስትነግራቸው::

"አይ በደህና ነው:: እማዬ እስክትመጣ ያመልጠኛል ብዬ እርስዎን ልጠይቅ መጣሁ"

"ምንድነው እሱ?" አሉ እማማ ሸዋ ዳርም የለሽን ካንጀት ስለሚወዷት አቅማቸው የፈቀደውን ሁሉ ለማድረግ በተዘጋጀ ስሜት::

"በኋላ እማዬ ከቤተክርስቲያን ስትመለስ የማመጣልሁ ሦስት ብር



እንዳለዎት ብዬ ነው:: ዕቃ ልገዛበት::" አለች መቀላመዷ እየተሰማት::

"ይቅር ይበልሽ! ውስጄ ምናለበት እንኳን ሦስት ብር" አሏት ወደ ቤታቸው ቀደም እያሉ::

ሦስቱን ብር ከእማማ ሸዋ ተቀብላ በቅርብ ወዳለው ሱቅ ሄደች::

"በረኪና አለህ?" አለች ከናፍሯ እየተንቀጠቀጡ:: ፈርታለች::

"የለም:: ደህና አደርሽ?" አለ ባለሱቁ እየተንጠራራ:: ገና መክፈቱ ነበር:: ለሰላምታው መልስ ሳትሰጠው ጀርባዋን አሳይታው ወደ ሌላ ሱቅ መንገዷን ቀጠለች:: ለወትሮው ምንም ይሁን ምን ለመግዛት ስትመጣ ሰላምታ ታስቀድም ነበር::

"ደብሯታል መሰል!" አለ ለራሱ የዛሬው ሁኔታዋ ገርሞት:: "በጥዋት ልብስ እጠቢ ተብላ ነው? ኡ. . . በዚ በብርድ? ያ አላህ!"

ዳርምየለሽ በረኪናውን አግኝታ በነጠላዋ ሥር ይዛ ተመለሰች:: ከዚያም ለድርጊቷ አመቺ ብላ ቀድሞውኑ ካሰበቻቸው ሁለት አማራጭ ቦታዎች ወደ ማዕድ ቤቱ አደላች:: መኝታ ቤት እንዳትገባ ኑንሽ አልወጣችላትም:: በረኪናውን ባዶ ከነበረ ሰባራ እንሥራ ውስጥ አስቀመጠችና እጇ ይዞት የተመለሰውን ጥቀርሻ ለበስ የሸረሪት ድር እየጠረገች ወደ ዋናው ቤት ተመለሰች::

ምላጭ ይኖራል ብላ ባሰበችበት ሁሉ ፈትሻ ስላጣች ሃሳቧን ቀየረችና የሸንኩርት ቢላዎ ይዛ ወደ ማዕድ ቤት ተመለሰች:: የፊት ለፊቱ በር ይንኳኳ ነበር:: አስናቀች 'ማነው?' እያለች አለፈቻት::

አስናቀች በሩን ስትከፍት አራት ሰዎች በረንዳው ላይ ቆመዋል:: ሦስቱን አይታቸው አታውቅም:: አንደኛው ግን እቤታቸው ከሚመጉት ሰዎች አንዱ ነው:: ፈጠን ብሎ ሰላምታ ሲሰጣት አፀፋውን መለሰችና እንዲገቡ ጋብዛ ወደ ውስጥ ቀደመች:: እንግዶቹም ተከታትለው ገቡ:: እንዲቀመጡ ወደ መቀመጫዎቹ መራቻቸው::

"የለም ይቆየን" አሉ ከመሃከላቸው ወፈር አጠር ብለው ግንባራቸውን እስከ መሃል አናታቸው የተመለጡ ባለኳፖርት አዛውንት:: "ይልቅ ወላጆችሽን ጥሪልን" አሉ ባርኔጣቸውን በጉልበታቸው አንጻር ይዘው::

"እትዬ ብዙን ጥሪያቸው" አለ ጰማሪም እርሳቸውን ተከትሎ::

አመጣጣቸው ግራ ቢያጋባትም እናቷ ቤተክርስቲያን መሄዳቸውን ነገረቻቸው::

"ኧረ!" አሉና አዛውንቱ አብረዋቸው የመጡትን ሰዎች ግራና ቀኝ ቃኘት አደረጉ:: እንዴት ይሻላል እንደማለት::

"እዚሁ እንጠብቃቸዋ፣ ሌላ ምን መላ አለ?" አሉ ፀጉር ከጢማቸው ሽበት የወረራቸው ሌላ አዛውንት ጋቢያቸውን ወደ ትከሻቸው እጥፈው

ባይናቸው የኋሊት መቀመጫ እየፈለጉ:: የቀሩትም በሀሳባቸው ተስማምተው ተቀመጡ::

"ይህቺ ናት እንዴ ልጅቱ?" አሉ ራስ በራው አዛውንት አስናቀች ወደ ውስጥ ስትመለስ:: በጨረፍታ ሰምታቸዋለች::

"አይ ይቺ ታናሿ ናት" ሲል መለሰ አማረ::

"ታላቋ ናት ማለት ነው እንዲህ የምታስደገድገን! ይህችም ቆንጆ ልጅ ናት" አሉ ራስ በራው አዛውንት ፈገግ እያሉ ለጨዋታ::

"ያቺኛዋ ትበልጣለች ፀጉሯ ብቻ ይበቃል:: እዚህ ቀረሽ አትባልም:: ብቻ እግዚአብሔር ይርዳን እንጂ ፈጠን እሷን አገባ ማለት እመቤቱን አገኘ ማለት ነው:: ፀባይዋ! እውቀቷ! . . ."

"በል ዝምበል ልጄ! እዚህ አይወራም:: ከዚህ እስክንወጣ የኛ ልጅ ይበልጣል" አሉና አቋረጡት ሸበቶው አዛውንት አፋቸውን እየተሙተሙ::

ሰዎቹ ዳርምየለሽን ለፈጠነ ሊጠይቁ ሽምግልና የተላኩ ናቸው:: አማረና እስካሁን ምንም አስተያየት ያልሰነዘረው አቶ መዝገቡ የሥራ ባልደረቦቹ ሲሆኑ ሸበቶው ባሻ ጥበቡ እና ራስ በራው አቶ ይገረሙ ደግሞ ሰፈርተኛ ጎረቤቶቹ ናቸው::

እርስ በእርሳቸው እየተያዩና አልፎ አልፎም የየራሳቸውን ሌላ ሌላ ወግ እያወጉ የወይዘሮ ብዙነሽን መምጣት መጠባበቅ ያዙ::

♣ ♣ ♣

ዳርምየለሽ በረኪናውን ካስቀመጠችበት አወጣችና ስለቱ እጅግም በሆነው ቢላዋ አንገቱ ላይ ከርክራ ቆረጠችው:: እንደአቸኳኮሏ ቶሎ ወደጁ ለመውሰድ ግን አልደፈረችም:: አሁን ፍርሃቷ መጣባት:: ደረቷ መንቀጥቀጥ ልቧ መደለቅ ጀመረ:: ውጤቱ ያልጠበቀችው ቢሆንስ? ካሁን ቀደም አንድ የሠፈራቸው ልጃገረድ ልታስወርድ በረኪና ጠጥታ ሞተች ሲባል ሰምታለች:: በረኪና ለውርጃ እንደሚውልም የሰማችው በዚያው የወሬ አጋጣሚ ነበር:: ታዲያ እርሷም እንደልጅቷ አስወርዳለሁ ስትል ብትሞትስ?

"ልሙታ ብሞትስ! ካለመኖር ቁጭት የለም::"

ግን ለምን ትሞታለች? ልጅ ላለመውለድ ይሄን ያህል መስዋዕትነት ያስፈልጋል እንዴ? ካለመኖር እኮ በመጨረሻው የችግር አዘቅት ውስጥም ቢሆን መኖር ይሻላል:: ከሞት የሚገኝ ምንም ነገር የለም:: ከመኖር ግን ሌላ ቢቀር ችግር አለ:: ችግርን ለማስወገድ ካለዚያም ለመቋቋም በሚደረግ ትግል መውደቅ መነሳቱም ህይወት ነው:: ከመኖር ችግር ያልፋል:: ጊዜም:: ከመኖር አዲስ ነገር አለ:: ከመኖር አጋጣሚ ይፈጠራል:: ከመኖር ዕድል ይከፈታል::



ማን ያውቃል ይኼ እስከራሷ የመጥፊያ ሰበብ ሊሆናት የሚችለውና እንዲጠፋ የፈረደችበት አላስፈላጊ ጽንስ ቢወለድ እኮ እንዳሰበችው ላይከብዳት ይችላል:: ጥርሷን ነክሳ ብታሳድገው ምናልባት 'እንኳን ወለድኩት' የሚያሰኝ 'ታላቅ' የተባለ ሰው ሊወጣው ይችላል:: ምናልባት ያገር መሪ፣ ምናልባትም ዝነኛ ደራሲ፣ ፈላስፋ፣ ሳይንቲስት . . .

"ኩሊስ ቢሆን? ምናልባትም በምን ቀን ወለድኩት የሚያሰኝ ለአገር ለወገን የማይጠቅም ወሮ በላ፣ ሌባ፣ ውሸታም . . . ቢሆንስ? ኧረ እንዲያውም እዛ ሳይደርስ 'ወልዳለችን ብቻ ስም ትቶልኝ ቢሞትስ? ገና ከማህፀኔ ሳልወጣ ቅሪት የዕድሜ ዋስትና ሊሰጠኝ የሚችል ማነው?"

"በአካልም በመንፈስም ተጐሳቁዬ መጨረሻው ባያምርልኝ የማን ያለህ እላለሁ? አለጊዜው አለፍላጐቴ የመጣ በመሆኑ መወገድ አለበት" አለች ፍርሃትን ተንተርሶ በሃሳቧ የተመላለሰውን መካር በህሳቧ እየተቃወመች:: መልሳ ደግሞ ፈራች::

ብቻውን ባይወገድስ? እሷንም ይዟት ቢሄድስ? -ልጅቷን አስታወሰች::

"ይሂዳ! ከሞት በኋላ ዕረፍት እንጂ መከራ የለም:: ግልግል ነው:: በራሴ ደርሶ ያየሁትን የህሊና ስብራት በልጄ ላይ ማስከተል አልፈልግም:: -አባት የሌለው ልጅ::

"አባቱ ማን ነው? ሲለኝ ማን እለዋለሁ? ገና ሳይበቅል የካደውን:: ነብስ እንደሁ. . ."

"ዳርም!" ብላ ዘው አለችባት:: -አስናቀች:: ሁለቱም ያልጠበቁት ጉዳይ በመሆኑ ተደናገጡ::

ዳርምየለሽ ቅንድቧን አኮማትራ ትናንሽ ዓይኖቿን በእህቷ ላይ አፈጠጠቻቸው:: በሩን መዝጋት እንደነበረባት ትዝ አላት:: አስናቀች ዳርምየለሽ ወደ ማድቤት ስታመራ ስላየቻት በእንግዶቹ የተሰማትን ጥርጣሬ እና መደነቅ ልትነግራት ነው የመጣችው:: አጋጣሚውን ማመን አልቻለችም::

"ምን እየሰራሽ ነው?"

"ምን ስሰራ አየሽኝ!" አለች ዳርም የለሽ ቁጣዋን መቆጣጠር ተስኗት::

"እህ! ታዲያ በረኪናው ምን ያደርግልሻል? በረኪና እሚነከር ቀርቶ የሚታጠብ ልብስ በቤቱ የለም:: ቅድም ወጥተሽ የመጣሽው እሱን ለመግዛት ነው ለካ? እኔ ደግሞ ማድቤት የገባሽው ሥራ ለመሥራት አስበሽ መስሎኝ"

"አያገባሽም:: አርፈሽ ወደ ሥራሽ ሂጂ!" አለች ዳርምየለሽ በሃሳቧ በረኪናውን ቶሎ ብላ ከመጨለጥና እህቷን በዘዴ አስወጥታ ያለምንም

ስጋት ከመጠጣት የትኛው እንደሚቀል እያመነታች:: እርሷ ቆማ ልትጠጣ ብትሞክር ሳትቀምሰው፣ ብትቀምሰውም በላስቲኩ ጠባብ ጉሮሮ እስኪንቆረቆር ብዙም ሳትወስድለት ትይዛታለች:: በተቻላት መጠን ለደቂቃም ቢሆን ወጣ እንድትልላት የሚያደርግ መላ አሰበች::

"አሁን ለምን ፈለግሽኝ?" አለች ረጋ ያለች ለመምሰል በሚሞክር ገጽታ::

"የፈለኩሽማ. . . ግን ከዛ በፊት ከዚህ መውጣት አለብን:: እሱን አስቀምጪና ውጭ እነግርሻለሁ" አለች አስናቀች ከመጣችበት ይልቅ የበረኪናው ሚስጥር አሳሰባትና አስፈርቷት::

"ለምን? እዚሁ ልትነግሪኝ አትችይም?" ስትል ጠየቀቻት እንደማትወጣላት ተረድታ:: በተቻላት ፍጥነት ሳትይዛት ለመጠጣት ቆረጠች:: ሆኖም ቀድሞውኑ ሲሞግታት የነበረው የህሊናዋ ፈሪ ክፍል እንደገና አገረሸ:: በጽንሱ ላይ ስትፈርድ በራሷ መኖርና አለመኖር ላይም አንድ ልብ ሆና መወሰን እንዳለባት አስታወሳት:: እጇ በፍርሃት እና በማመንታት ሲንቀጠቀጥ ወደ አፏ ሳይደርስ ታነቀ:: አስናቀች ባለ ፍጥነትና ጉልበቷ ተወርውራ እጇ ላይ አረፈች:: ብዙም ሳይታገሉ ሀዘንና ትካዜ አጉሳቁሎ የታናሿ ታናሽ ያደረጋት፣ በዚያም ላይ ህሊናዋ ድርጊቱን በመፈፀምና ባለመፈፀም ተከፋፍሎ የነበረችው ዳርምየለሽ ተሸነፈች::



# 34

"እንዴ! ኧረ በግዜር! ተቀመጡ እንጂ!" አሉ ወይዘሮ ብዙ የጥዋት ሰላምታ ሰጥተዋቸው የእንግዶቹ ኖር እንዳሉ ቆሞ መቅረት ከብዷቸው::

"እስቲ መቀመጡ ይቆየንና የመጣንበትን ለመቀበል ቃል ይግቡልን" አሉ አቶ ይገረሙ ባርኔጣቸውን ጉልበታቸው ላይ ለጥፈው እንደያዙ::

"ምንድነው እሱ? ለማንኛውም ለምን አትቀመጡም?" አሉ ወይዘሮ ብዙ አዝማሚያው እየገባቸው::

"እንዲህ ነው" አሉና ጀመሩ ባሻ ጥበቡ የአቶ ይገረሙ ጥቅሻ 'አግዙኝ' መሆኑን ተረድተው:: "መቼም የመጣንበት ሰዓትና ዕለቱ ራሱ ኧረ እንዲያውም አቋቋማችን" አሉ በራሳቸው አነጋገር ፈገግ እያሉ:: "ለጥሩ ነገር እንደሆነ ሳይገልጽልዎ አይቀርም::"

"ለዓለም ለደስታ ፍለጋ ነው" አሉ አቶ ይገረሙ ቀበል አድርገው በመርዳት::

ወይዘሮ ብዙ ቢቸግራቸው ዝም ብለው ማዳመጥን መረጡ:: ሰዎቹ ዳር ዳር ከማለት አልፈው ለመልስ የሚጋብዛቸው ግልጽ ጥያቄ እስኪያነሱባቸውና ለመናገር ዕድል እስኪሰጧቸው::

ለእናትና ለአባት የልጅን አበባ በህይወት ከማየት የበለጠ ዓለም እንደሌለ፣ ልጅ ወልዶ አሳድጉ ለዚህ ወግ ማዕረግ ማድረስና በተለይ በዛሬ ዘመን ጨዋ ልጅ አላችሁ ተብሎ በክብር መጠየቅ ትልቅ እድል መሆኑ፤ የእርሳቸውም ልጅ ለዚህ በመታጨቷ ሊኮሩባት እንደሚገባና ፈጠነም ቢሆን ቁም ነገረኛ፣ ትሁትና ራሱን ለማሻሻል ተፍጨርጫሪ ጉበዝ፣ እንደዛሬ ዘመን ወጣት ከዚያ ከዚህ የማይወሰልት አቻዋ መሆኑ፤ ሌላም ሌላም ያለ የሌለው ማግባቢያ ሁሉ በየተራ ተነሳና ማሳረጊያው ልጃቸው ዳርምየለሽ ባህሩን ለፈጠነ ምህረቱ እንዲፈቅዱላቸው የሚለምን ሆነ::

ወይዘሮ ብዙ በተለይ የጠያቂውን ስም ከሰሙ በኋላ ሌላው ሁሉ ስብከት አልተዋጠላቸውም:: ለማስላሰልም ዕድል አልሰጡት:: በንዴት ጦፈዋል::

"ሆይ ባዕዳ! ባዕዳ ዞሮ ዞሮ ባዕዳ ነው:: . . . የባዕዳ ዘመድ የቤንዚል አመድ የለውም አሉ!" ይላሉ በየመሃሉ ለራሳቸው በማጉመትመት::

ሽማግሌዎቹም የመጡበት ነውና እንደቆሙ ማግባባታቸውን ቀጠሉ:: ወይዘሮ ብዙነሽ ግን የሚበገሩ አልሆኑም::

"እንዴ! እሱኮ ወንድሟ ነው:: መቼም የባዳ ነገር ሆኖ ነው እንጂ ከሰራልኝ ውለታ አንጻር በበኩሌ እንደ ሥጋ ዘመድ ነው የማየው:: ታዲያ እሱ ወንድም ሆኖ መዳር እንጂ ዳርምየለሽን ለራሱ መመኘት አለበት?"

"እርስዎ ደግሞ ልክ አይደሉም!" አሉ ባሻ ጥበቡ ልመናው ስልችት አድርጓቸው:: "በእውነት ልክ አይደሉም:: አሁን ሁለቱ ቢጋቡ ይኼ የሚሉት ዝምድና ይጠብቃል እንጂ ይፈርሳል? በእውነት እርስዎም ትልቅ ሰው መሰሉኝ፤ እስቲ እኛ እንኳ እንክበድዎ! የወንድሜ ራስ የሸሸው፣ የኔ ፀጉር እንዲህ ጥጥ የመሰለው ዕድሜአችንን ሊናገር እኮ ነው:: እነርሱም ቢሆኑ ህፃናት አይደሉም:: ታዲያ ሽማግሌ ካልፈሩ ማንን ሊፈሩ ነው? በባህላችን ዕድሜ ክቡር ነው:: እንዲህ እንደዘመኑ ሳይሆን"

"እምቢ አላችሁኝ እንጂ በግዜር አልኳችሁ እኮ"

"በእግዜር ካሉ እሺ ይበሉን" አሉ አቶ ይገረሙ::

"አዎ! ካከበሩን እሺ ነው መልሱ" አለ እስካሁን ብዙም ያልተናገረው አቶ መዝገቡ:: ሌሎቹም በአዎንታ ራሳቸውን ነቅንቀው የወይዘሮ ብዙን ምላሽ ጠበቁ::

"ለማንኛውም አባቷ ይምጣ:: እኔ ብቻዬን የምወስንበት ጉዳይ አይደለም:: በዚህ እንደማትቃወሙኝ ነው መቼም:: ልጅን ለመስጠት እናትና አባት ዘመድ አዝማድ ሳይቀር መማከር እንዳለበት የምታውቁት ባህል ነው::"

"እንደሱ እንኳን ይሻላል:: ይኼ ራሱ መልስ ነው" አሉ አቶ ይገረሙ:: ሌሎቹም ሊቃወሙት ወይንም ሊያስተባብሉት የሚችሉት ጉዳይ ባለመሆኑ በወይዘሮ ብዙነሽ ህሳብ ተስማምተው ቀጠሮ ለፋሲካ ዕለት ያዙ::-አቶ ባህሩ ሲመጡ::



# 35

"ለምን ታለቃይኛለሽ ዳርምየለሽ? ምን አደረግኩሽ? ገደልሺኝ እንጂ! አዋረድሽኝ" አሉ እንባቸው ዱብ ዱብ እያለ:: እንግዶቹን እንደሸኙ አስናቀች ዳርምየለሽን እንዴት እንደያዘቻት ስለነገረቻቸው መኝታ ቤት አስገብተው ነው የጠየቋት:: ማርገዟን አረጋግጠዋል::

ዳርምየለሽ ከእንባ በቀር መልስ አልነበራትም:: ስቅስቅ ብላ አለቀሰች:: እርሷም ለራሷ በራሷ እርሳቸውም ለራሳቸው በልጃቸው ላይ መላቀስና መዋቀስ ይዘዋል:: እርሷ በልቧ እርሳቸው በአንደበታቸው::

"ለመሆኑ ስንት ወርሽ ነው?" አሉ በልባቸው አንድ ወር ሁለት ወርን ተመኝተው::

"አራት" አለቻቸው እንዳቀረቀረች::

"ምነው ያኔ እንደተኳረፍን በቀረን ኖሮ! ምናለ እግዚአብሔር ገድሎኝ በነበር" -በልቧ::

"ምነው ልፋቴን መና አደረግሺው ልጄ? ፈጣሪ ይይልሽ! ለስንት ቁም ነገር ስጠብቅሽ አሳፈርሽኝ እንጂ:: እኔ ጉዴን አላውቅ 'የኔ ልጅ' እያልኩ ስመጻደቅ:: እስቲ አሁን ምን አፍ አለኝ? ምን ሊውጠኝ ነው? ምናለ ከሆነስ በኋላ ቶሎ አትነግሪኝም ነበር? ካራት ወር ወዲያ ምን ማድረግ ይቻላል! በረኪና ጠጥተሽ እስክራስሽ ለመጥፋት ነው? ወይስ 'ልጂ ልታስወርድ በረኪና ጠጥታ ሞተች' ልታስኚኝ? ያገር መሳቂያ መሳለቂያ መጠቃቀሻ ልታደርጊኝ? ምነው ምን አደረግኩሽ? እዚህ ደረጃ ሳትደርሺ በትኩሱ ብትነግሪኝ እናትሽ አይደለሁም? እግዚአብሄር ይይልሽ! ባንቺ ያየሁት ጉድ አንሶኝ ሌላ ጉድ! ወላዲት አምላክ ምነው ረገምሽኝ!"

ልጃቸውን፣ ዕድላቸውንና ፈጣሪያቸውን ረግመው፤ የአምና ካቻምና የሃያ ምናምን ዓመታት ሰንካላ ነጠመኛቸውን ሁሉ በዘንድሮ ላይ አማርረው አለቀሱ:: የኑሮአቸውን ፣ የትዳራቸውን አለመመቸት፤ የአካላቸውን መጐሳቆል፣ የጤናቸውን መታወክ፣ ሌሎች ችግሮቻቸውንም በየተራ እያነሱ ታፍኖ በኖረ ብሶታቸው ላይ ሁሉ አለቀሱ:: በተለይ በዳርም የለሽ ክፉኛ አዘኑባት::

ቀድሞውኑ ባነሳችባቸው የአባቴ ማን ነው? አስደንጋጭ ጥያቄ ሲሳቀቁና

ሲጨነቁ እንዳልነበር ሌላ ጭንቀት ሌላ እዬዬ መጣባቸው:: የፊተኛውን ጉድ ሳያራግፉ ሌላ ጉድ አሸከመቻቸው:: -ልጃቸው:: በጉድ ላይ ጉድ:: ይሁን እንጂ ይበጃል ያሉትን ሁሉ ከማስላሰል አልቦዘኑም:: ሰው ሳይሰማው ፀሃይ ሳይሞቀው እንደፊተኛው ሚስጥር ከቤታቸው ከልባቸው ተቀብሮ የሚቀርበትን መላ::



## 36

በቤቱ ያሉት እርሱና እርሷ ብቻ ናቸው:: ዳርምየለሽ እግሮቿን ወደ አልጋው ሽክፉ ከቀኝ ጐኗ ጋደል በማለት ትራሱን በክንዷ ተደግፋ ፀጉሯን በግራ ትከሻዋ ወደ ፊቷ ለቃ እያሽሞነሞነች ግማሽ ተቀምጣለች፤ ግማሽ ተጋድማለች:: ትናንሽ ዓይኖቿን ወደ እርሱ እያንፀባረቀች ፊቷ በፈገግታ ተሞልቷል:: እርሱም በነጠላ ጫማ እንደሆነ ከግርጌዋ በኩል ተቀምጦ በፍቅርና በጉጉት ያስተውላታል::

"ሠርግ እንዲህ ደስ ይላል? እንዴት ደስ አለኝ መሰለህ!" አለችው::

"እኔስ የኔ ቆንጆ! ደስታዬ ከቁጥጥር ውጪ ነው ያደረገኝ:: አቤት ያች ዕለት እስክትደርስ የነበረኝ ጭንቀት! ሀሳቡ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ . . ." አለ እርሱም ወደቀኙ ዘመም ብሎ ሰውነቷ ላይ እያረፈ::

"ከሁሉም በላይ ደግሞ አንቺን ውድ ባለቤቴን ተረክቤ ፍቅሬን ለመወጣት ከመጓጓቴ የተነሳ ቀኑ ርቆብኝ ናፍቆቱ አስቸግሮኝ ነበር::"

"እውነት ግን ትወደኛለህ?"

"መውደድ ነው! ልቤ እስኪጠፋ ነዋ!"

"እኔምኮ እወድሃለሁ"

እቅፍ አደረጋትና ወደ ከንፈሯ ቀስ እያለ በስመመን ከንፈሩን ሲያስጠጋ እርሷ ደግሞ ስልምልም እያለች በመረታት ዓይነት አንድያውን ወደ ትራሱ ስትንጋለል . . .

"ኤጭ! ምቀኛ! ምን ያንቀገቅገቸዋል! ማን ነው?" አለ ግማሽ በስመመን ግማሽ በእውኑ እንዳለ ተነጫንጮ::

"ኸ! ምቀኛ? ኸረ እኔ እታገኘ ሠርቶ መብላት እንጂ ምቀኝነት አላውቅም:: ቀዥቃዣ? እግዚአብሔር ይስጥህ! ራስህ በጧት ቀጥረኸኝ ስድብ?" ብላ እየተማረረች ተመለሰች:: ጨርቅ አጣቢዋ እታገኘ ነበረች:: በጥዋት መጥታ የሚታጠቡ ልብሶችን እንድትወስድ የቀጠራት ራሱ ነው:: -ፈጠነ::

የቆሸሹ ልብሶቹ ጠርቀምቀም ብለውበት ራሱ ለማጠብ ሲሰንፍ ብቻ ነው አልፎ አልፎ የሚያሳጥባት:: የዚያን ዕለት ታዲያ በታዘዘችው መሠረት

ስታንኳኳ እርሱ ከገባበት የህልም ጫጉላ አቋረጠችው:: ተማርራ ስትመለስ ቢሰማትም ወዲያውኑ ሊጠራት አልፈለገም:: ይልቁንም አናድዳዋለች:: ህልም ህልም መሆኑን ቢያውቀውም ከንፈሩ ከንፈሯ ላይ ሳያርፍ በመንቃቱ በሽቋል:: እታገኘን ረገማት:: አለንንም:: ለምን ብዙ ሳታንኳኳና ሳትቀሰቅሰው አልከፈተላትም? የምን ግዴ እንጂ እውነት እንቅልፍ ጥሎት አልመሰል አለው:: መልሶ ተሸፋፈነና ያለመውን እንደገና ከልሶ በሃሳቡ ከንፈሩንና ከንፈሯን ሲያገጣጥም በፍቅር ስሜት ሲግልና ሲቀዘቅዝ ሞከረ:: -ማን እንደ.ህልም:: እውናዊ ህሊናው ብቻውን መጋደሙን እያስታወሰ ፊልሙን አበላሸበት::

ይህ የሆነው ከፋሲካ መዳረሻ ቀናት በአንዱ ነው::



# 37

ደብረዘይት ለፋሲካ አንድ ወር ከዚያውም ላይ አንድ ሳምንት የተነሳለት:: ሦስት ሳምንት:: ሦስት የጉጉት፣ የምኞትና የተስፋ ባንፃሩም የስጋት የጥርጣሬና የፍርሃት ሳምንታት:: -ለፈጠነ ምህረቱ::

ከእሺታው መልስ በኋላ ድል ያለ ሠርግ ደግሶ ዘመድ አዝማዱ ከአገር ቤት፣ ሠፈርተኛው ከጐረቤት አብረው ሠሪዎቹ ከመሥሪያ ቤት ተጠራርተው ሲበሉና ሲጠጡ፣ ሲጨፍሩና ሲደልቁ፣ ዕልልታው ሆታው ሲደራ:: -ያስባል::

እርሱና ዳርምየለሽ እንደ አዲስ አበባው ወግ በሱፍ ልብስና በክራቫት፣ በቬሎና በጌጣጌጥ አሸብርቀው ጀነን ቆነን እያሉ በሚዜዎቻቸው እርዳታና አጀብ ከመኪና ሲወርዱ:: መምጣታቸውን በጉጉት ሲጠባበቅ የነበረው እድምተኛ ዳር እስከ ዳር ከመቀመጫው ተነስቶ ደስታውን ሲገልጽ::

'እል -ል -ል -ልል!
'ይሄት ይሄት ደረሰ
ይሄት ደረሰ . . .
'የወይን አበባዬ የወይን
እኛም ወደናል ትሁን::

'ፀጉሯ ወርዶ ወርዶ . . .' እያለ ሠርገኛው ሁላ ሲደልቅና ሲፍለቀለቅ:: -ይታየዋል:: እርሱና ዳርምየለሽ በቀስታ ርምጃ ንግስትና ንጉስ መስለው፤ ከፊታቸው ቀይ የበግ ሙክት ተጋድሞ ለወግ ያህል እርሷ ይዛለት እርሱ ሲባርክ፤ ከዚያም በደሙ ላይ ተራምደው ቈረጋውያን እየመረቁአቸውና ወጣቶች እያሞገሱአቸው ወደተዘጋጀላቸው የክብር ሥፍራ ሲያመሩ:: በተለይ ደግሞ በድፍን መራቤቴ በቅኔና የክህነት ችሎታቸው የተደነቁት አባቱ መሪጌታ ምህረቱ 'ይደልዎ' እያሉ ጋብቻቸውን በቅኔና በዜማ ሲያወድሱ፣ ሲመርቁ. . . ሁሉም ሁሉም ደስታና ፈንጠዝያ ይታየዋል::

በሌላ በኩል ደግሞ ሊያስበው አይፈልግ እንጂ የእምቢታ መልስ ሰጥተውት ዳርምየለሽን በሚስትነት ቀርቶ በተራ የእህትነት አቅርቦት ሲያጣ

ይታየዋል:: መቼም ለጋብቻ ጠይቆ የተከለከለበት ቤት እግሩ ድርሽ እንደማይል ራሱ ያውቀዋል:: አብዛኛውን የሀሳቡን ጊዜ የሚሻማው ግን በጐ በጐው ነገር ነው:: -ከእሺታቸው በኋላ::

ከወላጆቿ እሺታ በኋላ ዳርምየለሽን ከእጁ አስገብቶ ያንን አዘውትራ በአንድ ጉንጉን ሠርታ በትከሻዋ ወደፊት እያመጣች ደረቷ ላይ የምትቋጨው ፀጉሯን እየዳበሰ ስመው እንዳልጠገቡት ማራኪ ህፃን ልብ ሠራቂ ዓይኖቿን፣ ከስተር ስትል ግርማ ሞገስን የሚያላብሷት ቅንድቦቿን ጭምር፣ ግንባሯን፣ አንገቷን፣ አገጯን፣ ጉንጯን ከሁሉም በላይ ደግሞ ከንፈሯን እያገላበጠ ሲስማት፤ ለዓይን የሚያሳሳ ልስልስ ሰውነቷን ዳሰስ አያደረገ ወደ ጉያው በማስጠጋት ሲያቅፋትና ካልጋው እንደተቀመጡ ተስለምልሞና ተስለምልማ ወደ ኋላ ወይንም ወደጐን ይዟት በመጋደም. . . :: በተለይ የመጀመሪያው ቀን እንዴት እንደሚሆኑ ይታየዋል::

"መቼም ልጃገረድ መሆን አለባት"

ግን ባትሆንስ? ባትሆንማ ምን ያደርጋል:: አገር ቤት ቢሆን እንጂ አዲስ አበባ መቼም ድንግልና አይጠየቅም:: ሁለቱ ከተዋደዱ ጉዳቸውን ተሸፋፍነው ለይስሙላ 'ብርአምባር' ይዘፈንና በማግስቱ ለ'ምሥራች' ከጨከነ ሙሽራው የራሱን ሰውነት አንዱ ቦታ ላይ በምላጭ ቆርጦ፣ አለዚያም የዶሮ ደም በመቀባት፤ ዘመንን ካሉም ቀይ ጽጌረዳ ይዞ 'እስቲ አምጣው የደሙን ሸማ፣ እንዳንታማ' ለሚለው የሴት ቤተዘመድ መላክ ነው::

"ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ"

ሁሉም በየሆዱ፣ ገፋም ሲል ዳርዳር አያለ ማማቱ ባይቀርም በሚዜ አስጨፋሪነት የምስራቹ ምልክት እንደ ድል ዋንጫ ከፍ ተደርጐ ትከሻ ይደለቃል:: የደስደስ ይዘፈናል:: እልልታም ይቀልጣል:: እንዲህ ነው አዲስ አበባ::

እናሳ ያ ሁሉ ሠርግ ተደግሶ ልጃገረድ ባትሆን እሱም የሙሽራ ጐዶሎ ተቀብሎ ዝም ሊል? የማንንም ትራፊ?. . . ታዲያ ትሁና! በዛሬ ጊዜ እንደሆን ፋሽን ሆኗል:: ኧረ ባገኛትና እንኳን ትራፊ የትራፊ ትራፊም በሆንች:: . . .

ሥራው ላይ ያስባል፤ ያወጣል ያወርዳል:: መኝታው ውስጥ ሆኖም ማለቂያ እንደሌለው ፀሎት እንቅልፉ እስኪገላግለው ያስባል:: መንገድ ሲሄድ፣ ሲያርፍም ሲመገብም፤ ሌላው ቀርቶ የተፈጥሮ ግዳጁን ሲከፍል ያስባል:: -ስለሠርጉ፣ ስለዳርምየለሽ፣ ስለጐጆአቸው:: አራት ነጥብ የሌለው ሃሳብ -ምኞት፣ ተስፋ:: ከዕድሜ ልኩ የበለጠ ምኞት ተስፋና ጉጉት የታጨቀባቸው ከሃያ የሚበልጡ ሃያ አራት ሰዓታት:: እያንዳንዳቸው እንደ ሃያ አራት ዓመት



ከብደው ሲጐተቱ፤ ሲያዘግሙ፤ በማን እንደለገሙ ሳይታወቅ በሃሳብ ዋና የቸኮለውን ፈጠን ጥለው አለፉ::

# 38

ከበአላት ሁሉ የሆድ አባት የሆነው ፋሲካ የከብት ዘር፣ የዶሮ ዘር፣ የእህል፣ የቅቤ፣ የሽንኩርትና የመጠጥ ዘር ፈጅቶ አለፈ:: እንዳያልፍ የለምና ፋሲካም አለፈ:: ለጠገበ ብስና፣ ለሠከረ የዞረ ድምር፣ ለሳቀ ትዝታን፣ ለከፋው ብሶትን ለሁሉም አንዳንድ ነገር ትቶ:: ለፈጠነም አድርሶታል:: ጉጉቱን ገድሎበት ምኞቱን አምክኖበት ተስፋውን ቆርጠበት ሄደ:: ያ ሁሉ! የህሳብ ግንብ ፈረሰ:: ዳርምየለሽ ለፈጠን የህልም ቅቤ ሆና ቀረች:: -ህልም::

ከዚያ በኋላ ፋሲካም ፋሲካ አልነበረም:: ፈጠነም ፈጠነ:: ናላው ተበጥብጦና አካላቱ ተጨብጦ ሲበሳጭ ሲራገምና በመናቁ ሲቆጭ እልህ እየተናነቀው የቁጭቱን መወጫ የእልሁን ማስታገሻ መንገድ ሲያሰላስል ይኸው አለ:: የአለነና የአማረ የጧት ማታ ምክርና ማጽናኛ ሊመልሰው አልቻለም:: ያለዕረፍት የሚያሰላስለው ነገር ቢኖር አንድ ብቻ ነው:: -ጠለፋ::

ይህ ደግሞ ለገጠር በቀሉ ፈጠነ አዲስ አይደለም:: ባገር ቤትም ቢሆን ሴት ልጅ ለምኖ የተከለከለ ሲያመቸው ጠልፎ ይወስድና ካሣ ከፍሎ ከወላጆቿ በሽማግሌ ይታረቃል::



# 39

ቅዳሜ ለዳግሚያ ትንሳኤ ዋዜማ:: እንዳለፉት ቀናት ሁሉ ፈጠነ ምህረቱ ሥራ የገባው ለስሙ ነው:: ደመወዝ ከሚያገኝበት ይልቅ የሃሳቡ ስውር ሥራ በዝቶበት አሉተውሉቱን ወደ ውስጥ እየጐተተ አፍዝዞታል:: ሰዓት ደርሶ ከቢሮ እንደወጡ ከአማረ ጋር መከሩበት:: ከሰሞኑ የተረፉቸውን::

"አሁን በምን ወሰንክ?" አለው አማረ ሊሰናበተው አስቦ::

"ያው ነዋ! አንዱን ቀን በተስኪያን ልትስም ስትወጣ ተሸክሞ መሮጥ:: በስተቀር ከቤት አትወጣም አላልከኝም? ምን አማራጭ አለ?"

"ከቤትማ አትወጣም:: ብትወጣም ቋሚ የሆነ ቦታና ጊዜ እስካልሆነ ለጠለፋ አይመችም:: አንተ እንዳልከው ግን በተስኪያን አዘውትራ እምትስም ከሆነ ይቻላል::"

"እርግጠኛ ነኝ:: በዚህ አትጠራጠር:: እኔ እንኳን አዘውትሬ ከተከታተልኳት ዛሬ ስምንት ቀን መሆኑ ነው:: መጀመሪያ ያየኋት የቅዳሜ ሹር ዕለት ነው:: ከዚያ ወዲህ የፋሲካ ዕለት ራሴም መልሱን ስጠባበቅ ከቤት አልወጣሁም:: ከሰኞ ጀምሮ ግን ሥራዬ ብዬ በየቀኑ ተከታትያለሁ:: ሳታቋርጥ እስከ ዛሬ መጥታለች:: ስለዚህ ከዚህ የተሻለ አማራጭ አይኖርም" አለ ፈጠነ::

"ለነገሩ ግን በእግር ነው በመኪና የምንጠልፋት? መቼም እኔንም በጉዳይህ ስላስገባኸኝ ሰሞኑን ሁሉ ሲያሳስበኝ ነው የሰነበተው::"

"ምን ታደርግ አማረ! ችግሬ ችግርህ ቢሆንም አይደል:: በእግር ብናደርገው ወይ ትጮህና ሳንርቅ እንያዛለን::"

"ታዲያ ለምን በመኪና አናደርገውም?"

"የሚሻለውም እሱ ነበር:: ግን. . ."

"ግን ምን ፈጠነ?"

"መኪናው ከየት ይገኛል:: ታክሲምኮ ለመኮናተር ሰው ያስፈልጋል:: ለእንዲህ ያለው ብርቱ ጉዳይ ለመተባበር ፈቃደኛ የሚሆን ባለታክሲ ካልተገኘ ድርጊታችንን እንደ ወንጀል ፈርቶ ያስይዘናል::"

መለያያቸው ላይ ከመንገድ ዳር እንደቆሙ ብዙ ከተወያዩ በኋላ አማረ አንድ የሚያውቀው ታክሲ ሹፌር ስላለ በኮንትራት ጠይቆት መልሱን እስከማታ አለዚያም እስከነገ ውሎ ሊነግረው ተስማምተው ተለያዩ::

ከእንግዲህ የሚላካ አይደለም:: አንደኛ ነገር አምስት ወር ደርሳለች:: የአምስት ወር ጽንስ ለማስወረድ መሞከር በጣም አደገኛ እንደሆነ የልጃቸውንም ህይወት ሊያሳጣቸው እንደሚችል ተሰማቸው:: ሁለተኛ ነገር ደግሞ የሚላካ ቢሆን እንኳ በእርሳቸው በኩል የሚያውቁት ምንም ዓይነት የውርጃ ዘዴ የለም:: ድንገት ሀሳባቸውን አቋርጠው ጥባቸውን አስቀመጡና በበኩሏ እህህ ወደምትለው ልጃቸው ሄዱ:: መኝታ ቤት::

"መዘዘኛ!" አሏት በልባቸው:: ማርገዟን ከሰሙባት ቀን ወዲህ ልባቸው ከፉኛ ተቀይሟታል::

"ስሚ! ከዛሬ ጀምሮ ከቤት መውጣት፣ ወደዛ ወደዚህ ማለት የለም!" አሉ በትዕዛዛዊ አነጋገር::

"ባትይኝስ መች ወጥቼ አውቃለሁ? እቤት አይደለም እንዴ የምውለው ከገና ወዲህ የት ወጥቼ አውቃለሁ::"

"እሱን አላልኩሽም:: ባጠቃላይ በግቢም ሆነ በቤት ውስጥ መታየት የለብሽም:: በተስኪያን መሳሙንም ታቆሚያለሽ! ከዛሬ ጀምሮ ቤተስኪያንሽም፣ ቤትሽም፣ ግቢሽም፣ ምንሽም ምንሽም ይቺው ክፍል ናት:: የምትፈልጊው ነገር እዚሁ ይቀርብልሻል:: አንድ ሰው እንዲያይሽ ወይንም እዚህ መኖርሽን እንዲያውቅ አያስፈልግም:: እዚህ ቤት እንደሌለሽ ይቆጠር:: ትሰሚኛለሽ?!"

"አዎ!" አለች ዳርምየለሽ የተከፋ ፊቷን ቀና አድርጋ:: ምን ለማለት እንደፈለጉ ገብቷታል:: እርሷም ሌላ አማራጭ እንደሌላት ታውቀዋለች::

"እንጂ እኔ ብዙነሽ ተከብሬ በኖርኩበት ሠፈር 'ልጂ ዲቃላ ወለደች' እየተባልኩ የለቅሶ ቤት አፍ መክፈቻ የቡና ላይ መተረቻ መሆን አልፈልግም:: እዚችው ተደብቀሽ ትወልጃለሽ:: ከዚያ በኋላ የማይታወቅ አገር ጉዲፈቻም ቢሆን እንሰጣለን" አሉ እንደ አዲስ እየተናደዱ:: ስለዚህ ጉዳይ ለማንም ትንፍሽ እንዳይሉ ለልጆቻቸው በሙሉ ልመናም ማስጠንቀቂያም አዘል መመሪያ ሰጡ:: ከዚያ ቀን በኋላ ከውጪ በሚመጣም ሆነ በሚጠይቅ ሰው ሁሉ ስለዳርምየለሽ የሚታወቅ ነገር ቢኖር ከአዲስ አበባ ውጪ ስለመሄዷ ነው::

"ደብረ ብርሃን አንድ የኔ ዘመድ አለ:: እዚህ ከምትቀመጥ ሥራ አስይዛታለሁ ብሎ ወሰዳት" ይላሉ ወይዘሮ ብዙ ዳርምየለሽ የት እንደሄደች ለሚጠይቃቸው ሁሉ:: በተረፈ ከቤተሰቡ አባላት በስተቀር ወደ መኝታ ቤት የማንም ሰው እግር ቀርቶ ዓይን ዝር እንዳይል ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ:: ከውጪ ሰው የሚገባ ቢኖር፣ ለዚያውም ስትገባ ወይንም ስትወጣ ሰው እንዳያያት ጥብቅ ጥንቃቄ እየተደረገ ሩቂያ ብቻ ናት:: እርሷንም ወይዘሮ ብዙ እንድትገባ አልወደዱም ነበር:: ዳርምየለሽ እንደተደበቀች አንድ ቀን መልሰዋታል::

"የለችም" አሉአት ቆጣ ብለው::

"የት ሄደች?" የሩቂያ ጥያቄ ነበር::

"ደብረ ብርሃን ዘመድጋ ለመኖር ሄዳለች" አሉ ደጋግመው በማሰብና



በመናገር የእውነት ያህል የለመዱትን ውሸት::

"ታዲያ ለምን አልነገረችኝም?" አለቻቸው አባባላቸውን ባንድ በኩል አምና በሌላ በኩል ሊደብቋት የፈለጉት ነገር እንዳለ እየገመተች::

"ምናውቃለሁ ስላልተገናኛችሁ ይሆናል!" አሉ አፋቸው ባይናገርም ከዚያ ያለፈ እንዳትጠይቃቸው እየተመኙ::

"ግቢም አላልኩሽ ሥራ ይዤ" አሉ ተሰናብታቸው ልትሄድ ስትል::

"ለቀባሪ አረዱት" ሳይሆን "ለቀባሪ ደበቁት" መሆኑን ያወቁት ግን ሩቂያን ሸኝተው መጥታ እንደነበር እና እንዴት እንደመለሷት ለዳርምየለሽ ሲነግሯት ነው::

"ታውቃለችኮ!"

"ምኑን ነው የምታውቀው?"

"እንዲህ መሆኔን ነዋ!" አለች በዓይኗ ሆዷን እየጠቆመች:: ነጠላ ካልለበሰች በስተቀር ገፋ ብሎ ያስታውቃል::

"እንዴት! ምን ልታደርጊ ነገርሻት?" አሉ ተቆጥተው::

"መጀመሪያ ላይ የማደርገው መላ ጠፍቶኝ ስጨነቅ ለማስወጣቱ እንድትረዳኝ ብዬ"

"ለዚህ ነዋ ተንገፍጠሽ የቀረሽው! እስቲ ምን ፈየደችልሽ? ከንቱ ነዋ የኔ መጨነቅ:: ሰው እንዳያይሽ ሰው እንዳያውቀው እያልኩኝ በሃሳብ የምባክነው:: አንቺው ራስሽ በአዋጅ የለፈፍሽውን ነው ለካ!"

"እኔ ለማንም አልለፈፍኩም:: ያማከርኩት ሰው ቢኖር አንድ እሷ ብቻ ናት" አለች ይህን መሰሉን የእናቷ ምሬት አየተላመደችው ቢሆንም ሆድ ብሷት እልህ እየተናነቃት::

"ኧረ ወዲያ! እሷ የናትሽ ልጅ ናት ወይንስ እናትሽ? ከዚህ ወዲያ ምን ማወጅ አለ! ሚስጥር እንደሆነ ትንሽ ቀዳዳ ከሰጡት አገር ያካልላል:: የሚስጥር ቀዳዳ ስፌ ነው::"

"አምናታለሁ:: ሩቂያን ከእናቴ ልጅ ለይቼ አላያትም:: እሷም የኔ ብጤ ሆና ስለማታውቅበት ምንም ልትረዳኝ ባትችልም ስለኔ ጉዳይ ለማንም ታወራለች ብዬ አልጠረጥራትም" አለች::

ለሩቂያ የነገረቻት በጓደኝነቷ ማወቅ ይገባታል ብላ አይደለም:: ሲጨንቃት መላ እንድታፋልጋት እንጂ:: እንዲያውም ባትነግራት ትመርጥ ነበር:: በኋላ ላይ ግን ሌላው ቢቀር ችግሯን አወያይታ ስለምታጽናናት እና ስለምታበረታታት ማወቋን ወዳዋለች:: አሁንም እንድትርቃት አትፈልግም:: ችግሯን ተረድታ፣ በሀሳብ የምታጽናናት፣ ቋንቋዋ የሚገባት ሳትጨነቅና ሳትፈራ ፍቅሯን ከጥላቻ፣ ሀዘኗን ከደስታ ችግሯን ሁሉ ያለሃፍረት ልትናዘዝ የምትችለው ለእርሷ ብቻ ነው:: በተለይ ዘንድሮ እንደችግሯ ስፋትና እንደጭንቀቷ ክብደት ብቻዋን አምቃ ይዛው ቢሆን ኖሮ ፈንድታ ትሞት ነበር::

ይኼን ሁሉ አብራርታ ባትነግራቸውም የሩቂያን ታማኝነትና አንዴ ካወቀች በኋላ መደበቁ የሆን ያልሆን ጥርጣሬ አድሮባት ሚስጥራቸውን ለመጠበቅ ጥንቃቄ እንዳትወስድ የሚያደርጋት መሆኑን ዘርዝራ እንድትጠይቃት አስፈቀደቻቸው:: በፈቃዳቸው መሠረትም አስናቀች ስልክ ደውላ ጠራቻላት:: ከዚያ በኋላ ሩቂያ ከትምህርት ቤት በሚተርፋት ጊዜ ሁሉ እየመጣች ትጠይቃታለች::



# 41

ሲጥል በነበረው ሀይለኛ ዝናብ ታስረው የቆዩ እግሮች ከየአቅጣጫው መፈታት ጀመሩ:: በየቡና ቤቱ፣ በየሱቁ በረንዳና መጠለያ ባለበት ሁሉ ተፋፍጉና ተጨናንቆ ሰማዩን ሲገላምጥ የቆየው መንገደኛ በጊዜ ወደቤቱ ለመድረስና፣ ዝናቡ እንደገና እንዳይዘው ባደረበት ስጋት ይመስላል ከላይ ከታች እየተጣደፈ የፒያሳንና አካባቢዋን መንገዶች አንዳፍታ ወረራቸው:: ገና አንድ ሰዓት ገደማ ቢሆንም ፀሃይዋ ከወትሮ ቀደም ብላ በመሸሿ ውድቅት ይመስላል::

አትረምርሞ ያልወጣለት የሐምሌ ደመናም ከሰው ሠራሾቹ የከተማው ከዋክብት በላይ ጥቁሩን ጨለማ ለብሶ ይዝታል:: ይፎክራል:: አልፎ አልፎም የንዴትና የቁጣ ዘግናኝ ሳቁን ወደምድር ብልጭ ሲያደርገው ህዝበ አዳምን ያስፈራራል:: ያስደነግጣል:: ያስደነብራል::

ከሥራ በኋላ በተለመደው ቀጠሮ ሳይሆን በፍላጐታቸው መሠረት ዝናብ ሳያግዳቸው በየአመቻቸው መንገድ መጥተው ከዘወትር ማምሻቸው 'አራዳ ቡና ቤት' የተገናኙት ጋዜጠኛው እንዳለ ተመስገንና ሀኪሙ ዶክተር አብደላ መሐመድ የውጪው ዓየር ሁኔታ ያሳሰባቸው አይመስሉም:: ከወደጥግ ካለ ጠረጴዛ ላይ በተቃራኒ ወንበር ይዘው መጠጥና ሲጋራውን በጨዋታ ያከታትላሉ::

እንዳለ ከዳርምየለሽ ኩተለዮ እንኳንስ እንደበፊቱ ሊያመሽበት አራት ኪሎ የተባለ ሠፈር ላይኑም አስጠልቶታል:: የግድ ነውና ለሥራው ጧት ገብቶ ምሳውን ሳይቀር እዚያው ብርሃንና ሰላም የሠራተኞች ክበብ ይበላል:: አስር ሰዓት ሲሆንም በቀጥታ ወደ ፒያሳ ይሽሎጥጣል::

በዚህ ሁኔታ ፒያሳ ማምሸት እንደጀመረ ሰሞን ነው ከዶክተር ጋር የተገናኙት:: እንደዋዛ በሲጋራና በመለኪያ የተጀመረ ትውውቃቸው በሃሳብ መግባባትና በመላመድ ታግዞ ወራትን እያስቆጠረ ነው::

ዶክተር አብደላ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በህክምና የመጀመሪያ ዲግሪውን ተቀብሎ ለአምስት ዓመታት የድህረ ምረቃ ትምህርቱን ሲከታተል

ቆይቶ ከፈረንሳይ የተመለሰ ሰሞን ነበር። ሁለቱም ብቻ ለብቻ ተቀምጠው ከየራሳቸው ጋር ሲነጋገሩ ቆዩና።

"ይቅርታ!" አለ ዶክተር ያልተለኮስ ሲጋራውን አስቀድሞ ከመቀመጫው በመነሳት።

እንዳለ 'ምንም አይደል' እንደማለት በተቀመጠበት እንገቱን ዝቅ አድርጎ የራሱን የተለኮስ ሲጋራ አስጠጋለት።

"ሜርሲ!" ብሎ በፈረንሳይኛ ካመሰገነው በኋላ እንደተሳሳተ ሰው ቶሎ ብሎ "አመሰግናለሁ" አለው ቋንቋውን አርሞ።

"ኖኖ! ምንም አይደል። ለሲጋራ ምስጋና የለውም። እኔም ሌላ ቀን አንተን ባይሆን ሌላውን ማስቸገሬ አይቀርም" አለ እንዳለ የሰውዬው ትህትናና አቀራረብ እንዲናገር ገፋፍቶት።

"ታንኪዩ!" ካለ በኋላ ጠርሙሱን ጨልጦ ብርጭቆውን ይዞ ተመለሰ። "እንግዲያውስ ሌላ ይቅርታ ልጠይቅና ከጉንህ ለመቀመጥ ትፈቅድልኛለህ? ማለቴ ብንተዋወቅ? ሰሞኑን ሁሉ ሳይህ እንደኔ ብቸኛ መሰልከኝ" አለ ዶክተር።

"እሺ ደስ ይለኛል።"

"እጅ ለእጅ ተጨባበጡ።"

"ዶክተር አብደላ መሀመድ ካርዲዮሎግ፣ ማለት የልብ ስፔሽያሊስት። በቅርብ ነው ከፖሪስ የተመለስኩት።"

"እንዳለ እባላለሁ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ባህል ዓምድ አዘጋጅ ነኝ።"

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በየምሽቱ ይገናኛሉ። ዛሬ ለነገ ቀጠሮ ይዘው ሳይሆን ሁለቱም ለየግል ፍላጐትና ልማዳቸው። በእያንዳንዷ ምሽትም እንደዋዛ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በባህልና በልዩ ልዩ የሙያና የዝንባሌ ጉዳዮች ላይ ይወያያሉ። ይከራከራሉ። የየራሳቸውን አመለካከት እያነሱም በሀሳብ ይፋጫሉ ይጋጫሉ አንዳንዴም ይስማማሉ። ካልተስማሙም ያለመቃቃር አቁመው ሌላ ጨዋታ ይጀምራሉ። አንደኛቸው የሚያውቁትን ለሌላኛቸው ያካፍላሉ። የውጭና የሀገር ውስጥ መጽሐፍትን ይዋዋሳሉ።

"የሚመጣውን እሁድ የት ታሳለፋለህ?" አለ ዶክተር።

"ምን ማሳለፊያ አለ? እስካሁን ያሰብኩት ነገር የለም። ምናልባት በጀርባዬ ካልጋዬ ላይ ሂ! እንዳልኩኝ ወይ መጽሐፍ ወይንም ሀሳብና ትዝታን እያነበብኩ. . . እቤት ካልዋልኩኝም ሠፈር ለሠፈር ብርጭቆና ጠርሙስ እያበላለጥኩ ሲጋራዬን ስለምና ስስብ ምናልባት ደግሞ ቀኑ በሚወልደው ያላሰብኩትና ያልጠበኩት አጋጣሚ ላይ ስሯሯጥ። ብቻ ባሁኗ ደቂቃ እዚህ ቦታ እንዲ ሳደርግ እውላለሁ ብዬ በፕሮግራም የያዝኩት ነገር የለም።"

"አይ እኔ እንኳን ምናልባት ቀጠሮ እንዳለህ ብዬ እንጂ. . ."

"በፍጹም የለኝም። የዕሁድ ቀጠሮ መያዝ ከተውኩ ሰንት ጊዜዬ። ካንተም ጋር ከተዋወቅን እሁድ ተገናኝተን እንደማናውቅ ልብ ሳትል አትቀርም።



ዕሁድን እቤቴ መዋል ስለምፈልግ ባብዛኛው ከቀጠሮ ነፃ እያደረግኩት ነው" አለ እንዳለ።

"በርግጥ ከኔ ጋር የተገናኘንበት ዕሁድ የለም። እኔም ብሆን ዕሁድ ዕሁድ እዚህ ስለማልመጣ ምናልባት አንተ ትመጣ እንደሁ ብዬ ነው የጠየቅኩህ።

"መጥቼ አላውቅም። በኔ በኩል እሁድ ለማንኛውም ፕሮግራም ዝግ ነው።"

"ሌላ ቢቀር ለፕቲት አሚ መክፈትህ አይቀርም" አለ ዶክተር ክራቫቱን ደረቱ ላይ እየላገ። ተዛንፎበት ወይንም አስቸግሮት ሳይሆን ልማድ ሆኖበት ክራቫቱን መነካካት ይወዳል።

"ፔቲታሚ ደግሞ ምንድነው? አንድ ፊቱኑ ፔሬድ ይዞን ፈረንሳይኛ ብታስተምረኝ ሳይሻል አይቀርም" አለ እንዳለ የሳበው ጢስ ካፉ ሳይወጣ ፈገግ ብሎ። ከዶክተር ጋር ከተገናኙ ጀምሮ ካፉ የሚያመልጡትን ፈረንሳይኛ ቃላት በመልቀም በጥራዝ ነጠቅ ለምዷቸዋል።

"ይሻላል" አለ ዶክተር እርሱም ፈገግ ብሎ። በአማርኛ ሲያወራ አንዳንድ የፈረንሳይኛና እንግሊዝኛ ቃላት ጣልቃ ይገቡበታል።

"ፕቲት አሚ 'ገርል ፍሬንድ' ማለት ነው።"

"ገርል ፍሬንድ?" አለ ሳይታወቀው ከዶክተር ንግግር መሃል አውጥቶ በመድገም።

"ምነው?" አለ ዶክተር የእንዳለን ገጽታ መለዋወጥና የተንጠለጠለ ጥያቄ አገናዝቦ እንደተረበሸ ስለገባው ጥፋተኛነት ተሰምቶት።

"አይ ዝም ብዬ ነው"

የዶክተር ጥያቄ መልሶት ስሜቱን ደብቆ አቃለለው እንጂ 'ገርል ፍሬንድ?' ሲል ሀሳቡ ወደ ዳርምየለሽ ሄዶ ነበር። መልክና ፀባይዋ ያማረ ከዕ ድሜዋ ቀድማ የምታስብ የሴት ጓደኛ እንደነበረችው፤ አፍቅራ ስለሸሸችው፣ ሲያምናት ስለከዳችው፣ በድብብቆሽ ጨዋታዋ ከቋጠረችው ዘሯ ጋር 'እርም' ብሎ እንደተዋት ቅር እያለው አሰበ።

ለምን እንደሆነ ባይገለጽለትም ስለዳርምየለሽ ሲያስብ መንፈሱን የሚረብሸውና ቅር ቅር የሚለው ነገር አለ። እንዲያውም 'ተፍቶ መላስ' እንዳይሆንበት እንጂ አንዳንዴ መሄድ መሄድ ይለዋል። -ወደሷ።

ግን ለምን?

ለራሱ ጥያቄ መልስ ሲያጣ ዳግመኛ ዓይኗን ላለማየት የማለበት ቀናተኛና ኩሩው ልቡ ውሳኔውን አጽንቶ ይቆጣጠረዋል።

"ኖኖ! ከፊትህ ላይ የሚነበብ ነገር አለ። ሶሪ! አነጋገሬ አላስደሰተህም መሰለኝ" አለ ዶክተር ጭንቅላቱን ነቅንቆ።

"ባንተ አይደለም ዶክተር። እንዲሁ በራሴው ጉዳይ ነው። ይቅርታ ግን

እንዲያውም ጊዜና ምክንያት እየጠበቀ ይረብሽሃል።

"አ ሞን አሚ፣ በበኩሌ ማንኛውም በኔ ላይም ሆነ በሌሎች ላይ የሚደርሰው ስህተትና ትክክል፣ ክፉም ሆነ በጐ በማንኛውም ሰው የተባለ ሁሉ ባጋጣሚ ወይም ሆን ተብሎ ሊከሰት የሚችል ጤናማ የህይወት ገጽታ አድርጌ ስለምመለከተው ሶሲዮቴ ያሰኘውን ቢል ደንታ አይሰጠኝም። ይኼ ኮንፍሊክት የሚያመጣ ከሆነ መቼም . . ." አለና በምን እንደሚደመድም ሲያመነታ እንዳለ ቀደመው።

"ያመጣል እንጂ ምን ጥርጥር አለው። በህብረተሰብ መሀል ለመኖር ወግና ልማዱን፣ እምነትና ባህሉን፣ አጠቃላይ ሥነ-ልቦናና ፍላጐቱን መጠበቅና መከተል ግዴታ ነው።"

"እንደዛማ ከሆንኩ ምኑን ከርሱ ተሻልኩ። አውቄ ላለማወቁ ከተበለጥኩ፣ ቀድሜው በመቅረቱ ከተጐተትኩ የኔ ማወቅና የኔ መማር ምን ትርጉም አለው?" አለ ዶክተር የእንዳለን አባባል መቃወም ብቻ ሳይሆን ማጣጣል በሚመስል የአነጋገር ስልት።

"ልክ ነህ። ካንተ በአስተሳሰብ ወደኋላ የቀረውን ህብረተሰብ ወደ አለህበት ደረጃ መሳብ እንዳለብህ አምናለሁ። ሆኖም ግን የህብረተሰብን ዕምነትና አስተሳሰብ አስፍቶ ከራስ ጋር ለማቀራረብ መጀመሪያ ከርሱ ጋር ተቀላቅሎ ያወገዘውን በማውገዝና የወደደውን በመውደድ የራስን ዕምነትና ፍላጐት በሚስጥር ይዞ ቀስ እያሉ ማለዘብ ያስፈልጋል።የአንድ ሰው ዕውቀትና ንቃተህሊና ብቻውን ለራሱ እንጂ ለህብረተሰብ ምኑም ሳይሆን ይችላል። ይልቁንም ከህብረተሰብ ጋር አቀራርቦ እና አግባብቶ ተቀባይነትን ሊያስገኝለት የሚችለው በውስጡ የዳበረው ንቃተ ህሊና ሳይሆን ማህበራዊ ግንኙነቱ የተመሠረተበት ውጫዊ የስብዕና ቅርበቱ ማለትም ባህሪው ነው። ባህሪ ማህበራዊ ሃብት ነው። ይሄ ሀብት ደግሞ የሚገኘው ራስን አጋልጦ በውስጣዊ ንቃተ ህሊና ተጽዕኖና ግፊት ግዴለሽ ሆኖ ወደ ህብረተሰብ በመቅረብ ሳይሆን የራስን ዕምነትና ፍላጐት ቆጠብ አድርጐ የህብረተሰብን እምነትና ፍላጐት በማዳመጥ፣ ወግና ልማዱን በማክበር ነው። ህብረተሰብን ከአሮጌ ባህል ተጽዕኖ ማውጣትና የአስተሳሰብ ዕድገቱን መምራት ብረት ውስጥ ተቀብሮ የኖረን ጥምዝምዝ ምስማር ማለት 'ብሎን' እንደማላቀቅ ብልሃትና ጥንቃቄን ይጠይቃል።"

"ስክሩውን ወደ ላይ ለማውጣት ጠመንጃ መፍቻህን ወደታች እየተጫንክ ትጠመዝዘዋለህ። ተሳስተህ ወደቀኝ ብትጠመዝዝ የበለጠ ታጠብቀዋለህ። ቸኩለህ ወደላይ ብትስብ መፍቻህ ብቻውን ተንጠልጥሎ ይቀራል። ረጋ ብለህ ካሰብክና ወደ ተቀበረበት እየገፋህ በማባበል ወደ ግራ ከጠመዘዝከው ግን ራሱ ወደላይ እየገፋህ ይመጣል።"

"ምሳሌህ አልተዛመደልኝም። ብሎን ለማውጣት ፎርስ ተጠቅሞ ወደግራ መጠምዘዝ እንጂ ምን ማባበል ያስፈልጋ፡ ያን ጊዜ መውጣት ስላለበት ይወጣል" አለ ዶክተር ስሜቱ ገፋ ብሎ።



"ያስፈልጋል እንጂ ዶክተር። ካለበለዚያማ ምናልባት ጠብቆ ወይንም ዝጎ ቢሆን ከጅምሩ ባለ ሀይልህ ስትጠመዝዘው አናቱን ሸርፈህ ታሳርፈዋለህ። ወይንም ደግሞ ካንተ መፍቻ ጥምዝምዙ ሚስማር ከጠነከረ ጫፉን ቸርችፎ አለዚያም ሰብሮ ያሳርፍሃል።"

"አ! ይሄማ አንተ ምንም ልታደርግ የማትችለው አጋጣሚ ነው።"

"አስቀድመህ ካመዛዘንክ ብዙ ነገር ማድረግ ትችላለህ። ለምሳሌ የዝገት ማስለቀቂያ ቅባት ማለት ፔንትሬቲንግ አይል ተጠቅመህ ጥብቀቱን በማላላት ወይንም ደግሞ ጉልበትህን ተቋቁሞ ሙሉ ኃይልህን ለማሳረፍ የሚያስችልህን ዓይነት ጠመንጃ መፍቻ መጠቀም ትችላለህ። እነዚህን ወይንም ሌሎች አማራጭ መንገዶችን ማግኘት ካልቻልክ አስቀድመህ ከሙከራህ መቆጠብ ነው። ውጤቱ ጥፋት ሲሆን ለማፈርና ለመወገዝ እራስህ የተካንከውን፣ ነገር ግን ሰው ያላወቀልህን ብሎን የመፍታት ችሎታ ከመናገር ይልቅ በውስጥህ ቀብረህና በአላዋቂነት ስም ቀርበህ ተመልካች መሆን ይቀላል። አውቃለሁ ያስጠብቃል። አለቦታው አለጊዜው ራስን ለመግለጽ መሞከርም ያስንቃል። አላውቅም ግን ይደብቃል። በተለይማ ራስህን አጋልጠህ ድክመትና ሽንፈትህን ካሳየኸው ነፃነት ብሎ ነገር ሊኖርህ አይችልም። ሰው ነህና ውድቀትህ በከፈተው የህሊና ቀዳዳ የሚገባውን ንፋስ መቋቋም ሲያቅትህ ትታጠፋለህ። ትሰበራለህ።"

"ሌስ ቶምቤ! እርሳው! ወደአላሰብነው ሙግትና ክርክር ገባንኮ" አለ ዶክተር ውይይታቸው መቋጫ ወደ ሌለው ክርክር በማምራቱ። ይልቁንም ከተነሱበት ነጥብ እየራቁ መሆኑ ተሰምቶታል።

"እዎ ቢበቃን ይሻላል ዶክተር። በማህበራዊ ጉዳይ ላይ፣ እንኳን በመጠጥ ቤት የመለኪያ ስብሰባ በታላላቅ አዳራሾች ጥናታዊ ኮንፈረንስ መደምደሚያ መስጠት ያስቸግራል።" አለ እንዳለ ምንም እንኳን ያሰበውን ያህል መናገርና ለዶክተር ማስጨበጥ አለመቻሉ ቢሰማውም ሀሳቡን ደግፎ። ከኪሱ አዲስ ሲጋራ አውጥቶ ከለኮሰ በኋላ ፖኬቱን ወደ ዶክተር አስጠጋለት።

"ታንኪዩ!" አለ የለኮሰውን ሲጋራ አንዴ ሳብ አድርጐ። "እኔ እንኳን ቅድም ዕሁድን የት ታሳልፋለህ ያልኩህ ይኼን ሁሉ ክርክር ለማምጣት አልነበረም።"

"እኔምኮ ሳላስብ ነው። ባጭሩ ምነው ጠየቅከኝ? ብልህ ይቀል አልነበር።"

"እኔም ብሆን በቀላሉ ዕሁድን እኔ ቤት እናሳልፍ ማለት ይቀለኝ ነበር። አንተ ግን ከገርል ፍሬንድ ጋር የተያዘ ቀጠሮ ልታስታውስ የማትፈልገው ሚስጥር አለህ መሰለኝ? ግን ይቅርታ ካስቸገርኩህ" አለ ዶክተር ስለ እንዳለ ሚስጥር ለማወቅ እንደገና እየሞከረ። ጫፍ አግኝቶ እስከ ወዲያኛው ጫፍ ሳያውቅ መተው ደስ አይለውም። በተለይማ ሚስጥር ካረገበት ቀላሉ ነገር እረፍት ይነሳዋል። አውጣጥቶና አግባብቶ ሲነግሩት የሰዎቹን ውስጣዊ ስብዕና ያገኘ ስለሚመስለው በጣም ይደሰታል። በተቻለው መጠንም ከመርዳት ወደኋላ አይልም።

"በፍጹም አላስቸገርከኝም። ግን እንዴት እንዲህ ልትለኝ ቻልክ?"

"እንዴ! ስለሚስጥር አስፈላጊነትና ራስን ስለመደበቅ ሽንጥህን ገትረህ መከራከርህ ምናልባት ራስህን ለመከላከል አስበህ ይሆናል ብዬ ነዋ! መነሻችንም ገርል ፍሬንድ የምትለዋ ቃል ናት::"

"እንደዛ እንኳን አይደለም" አለና ሲጋራውን ሳብ አድርጐ የታችኛውን ከንፈሩን በማስረዘም ተነፈሰ:: ወደ ላይ የሚቦነውን ጭስ ተከልሎ የዶክተርን ፊት ቃኘት አደረገው::

"ያን ያህል ከሰው የሚያስደብቅ ምስጢር እንኳን የለኝም::"

"እኬ ታዲያ ለምን አትነግረኝም?"

"አልነግርህም ዶክተር ይቅርታ! አንተን ቅር ላሰኝህ ሳይሆን ራሴ ማስታወስና መነካካት የማልፈልገው ቁስል ስለሆነ ነው::"

"ኬስከሴ? ምንድነው እሱ? ፍቅር መሆን አለበት"

እንዳለ የዶክተር የማውጣጣት ሙከራ አስደነቀውና በዝምታ አስተዋለው::

"ፍቅረኛ አላችህ ወይንም ሚስት?"

"ሁለቱንም የለኝም ብቸኝነቴንኮ ነገርኩህ"

"በህይወትህ አፍቅረህ አታውቅም?"

"አፍቅሬስ አውቃለሁ:: የጀመርኩትን ለመጨረስ አልታደልኩም እንጂ::"

"ፑር ኗ? ለምን?" ካለ በኋላ በልቡ 'ሞታበት ይሆን' ብሎ ገመተና መጠየቁ ሰቀጠጠው!: እንዴ ካፉ ስለወጣ ግን ምንም ማድረግ አልቻለም::

"ተወኝ ዶክተር! ወደምሸሸው እና ወደምፈራው ትውስታ አትመልሰኝ:: ባንድ ወቅት የምወዳትና ትወደኛለች የምላት ፍቅረኛ እንደነበረችኝ ከነገርኩህ ይበቃል:: ከዚያ ውጪ ግን በልቤ የተሸከምኩትን ገና ያልጠገገ ቁስል ደጋግሜ እያደማሁ ራሴን ለህሊና ለቅሶ መዳረግ አልፈልግም:: እባክህ ዶክተር ይህን አስመልክቶ ሌላ ጥያቄ አትጠይቀኝ" አለ እንዳለ ገጽታው በሀዘን ጨፍግጐ::

"ዠመ ኤክስኪዩዝ! ይቅርታ እንዳለ! እኔ ያን ያህል ሲርየስ ስላልመሰለኝ ነው:: ይቅርታ!" አለ ዶክተር የእንዳለ ደፍራሳ ዓይኖች ላይ የሚንከራተተውን የእንባ ጉም ሲያይ ደንግጦና ልቡ በሃዘን ተነክቶ::

እንዳለ መለኪያውን ጨልጦ እጁን አጨበጨበ:: ፈጣኑ የቡና ቤት አሳላፊ ጠርሙሱን ይዞ ከች አለ::

"ይልቅ ከፈረንሳይ ትዝታዎችህ አንድ ሁለቱን ወርውርልኝ" አለ መለኪያውን አስሞልቶ ከተጎነጨ በኋላ::

"አጫርሰኸኛልኮ" አለ ዶክተር ፈገግ እያለ በቀልድ:: ከተገናኙ ጀምሮ ብዙ አጫውቶታል::

"ትንሽ ትርፍራፊ አይጠፋም:: ለምሳሌ በግል የገጠሙህን ጥሩና መጥፎ ገጠመኞች ብዙም አላጫወትከኝም::"

"አሎር!" አለ ጥቂት ካሰላሰለ በኋላ::

"እንግዲያው ለፈገግታ እሚሆን አንድ ላጫውትህ::"



እንዳለ በእሺታ ጭንቅላቱን ነቅንቆ ጠበቀው::

"ዊንተር ሲቃረብ ቶሎ ይጨልማል፣ ቶሉ አይነጋም:: ለሊቱ በጣም ረዥምም ነው:: ከዚህ እንደሄድኩ ሰዓት ገዛሁና ከኮርስ መጀመሪያው ሰዓት ቀደም አድርጋ እንድትቀሰቅሰኝ ሞላኋት:: ደወለችና ከእንቅልፌ ስነቃ ጨለማ:: ሰዓቷ ልክ አይደለችም ወይንም ከአሞላሌ ተሳስቻለሁ አልኩና ተመልሼ ተኛሁ:: ትንሽ ቆየሁና እንደገና ተነሳሁ:: አሁንም ጨለማ ነው:: ተመልሼ ተኛሁ:: በኋላ ላይ ጫጫታ ሰምቼ መስኮት እከፍታለሁ ተማሪ ከክፍል ወጥቶ ወደየዶርሙ ይመለሳል:: ሰዓት ላይ ስድስት ሰዓት ይላል:: ስድስት ሰዓት ስልህ የእኛ አገር ጠራራ ፀሀይ እንዳይመስልህ:: የጀምበር መግቢያ ነው የሚመስለው::"

ትንሽ ተሳሳቁና ዶክተር አብደላ ጨዋታውን ቀጠለ::

"እንዴ ደግሞ ምን ሆንኩ መሰለህ! ባቡር ጠበቅኩና ተሳፈርኩ:: ገብቼ ወንበር ከመያዜ ውስጥ የነበሩ ሰባት ያህል ነጭ ጉረምሶች እንዴት እንዴት እንደተግባቡ አልገባኝም:: ብቻ ተጠቃቀሱና ፊሳቸውን ፈስተው በሩ ከመዘጋቱ በፊት ተሯሩጠው ወረዱ::"

እንዳለ ሳቁን መቆጣጠር አልቻለም:: ሌሎች ጠጭዎች በመገረም እስኪመለከቷቸው ድረስ ተሳሳቁ::

"ዝም አልካቸው?" አለ እንዳለ ሳቁ መለስ ሲልለት::

"ምን ልበላቸው ታዲያ?"

"ማለቴ ዝም ብለህ ተቀመጥክ?"

"ምን ላድርግ? በሩ አውቶማቲክ ነው ተዘግቶብኛል:: በኋላማ ተነስቼ መስኮት ከፈትኩኝ:: የተሰማኝ ንዴት ግን ምን ልበልህ! አሁን ስላለፈ ያስቀኛል::"

"ባለጌዎች ናቸው::"

"በጣም! አየህ፣ የሰለጠኑና የመጠቁ ፈረንጆች የመኖራቸውን ያህል በጣም ወራዳና ገና ከዘረኛ አመለካከት ያልወጡ፤ የሰለጠኑ ቢመስላቸውም ያልሰለጠኑ ፈረንጆች በጣም ብዙ ናቸው::"

"አውሮፖ ውስጥ ዘረኝነት ከናዚ ጀርመን ጋር ያከተመ ይመስለኝ ነበር" አለ እንዳለ እየገረመው::

"ኖኖ ኖኖ አሁንም አለ:: በርግጥ በህግ ደረጃ የዘር ልዩነት የለም:: እንዲያውም ዲስክሪሚኔሽን በህግ ያስቀጣል:: በተግባር ግን አሁንም ያልሰለጠኑ ነጮች አሉ:: ለምሳሌ አንዳንድ ቡና ቤት ጥቁር ከሆንክ የሚያስተናግድህ አታገኝም::"

"ያማ ከደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ ምኑን ተለየ!"

"ይኼኛው ትንሽ ረቀቅ ይላል፡፡ ደቡብ አፍሪካ የለየለት ነው፡፡ ነጮች በሚገለገሉበት የመዝናኛ ሥፍራና የመጓጓዣ ዘዴ በሌላውም ማህበራዊ ፖለቲካዊ አውታር ጥቁሮች መጠቀም እንደማይችሉ በይፋ የታወቀ ነው፡፡ ስለዚህ አንተም ለነፃነትህ ከመታገል በቀር አትደርስባቸውም፡፡ አውሮፖ ግን መፈክሩ ሁሉ ሰብአዊ መብትና እኩልነት ነው፡፡ እኩል ነን እያሉህ ዘረኝነታቸውን በዘዴ ያራምዳሉ፡፡ ወደ ሆቴሎች ያለዘርና ቀለም ልዩነት መግባት ትችላለህ፡፡ ሕጋዊ መብትህም ነው፡፡ አንዳንድ በታ ታዲያ ይኼን መብትህን በዘዴ ይገፉሃል፡፡ አስተናጋጁ ከኋላህ ለመጡ ነጮች እየታዘዘ አንተን ያልፍሃል፡፡"

"በህግ እሚያስጠይቅ ከሆን አይፈራም?" አለ እንዳለ አቋርጦት፡፡

"በግልጽ እምቢ አይልህምኮ! 'ጋርሶን' እያልክ ስትጣራ እንዳላየ እንዳልሰማ ይዘጋሃል፡፡ በህግ እንኳ ቢጠየቅ 'አልሰማሁም' እንጂ ልዩነት ማድረጌ ነው አይልም፡፡ ደሞስ ማነው ጠያቂው፡፡ ጮኸህ ጮኸህ ሲሰለችህ ያላባራሪ ራስህ ተነስተህ ትወጣለህ፡፡"

የዘር ልዩነት ያለው ደቡብ አፍሪካ ብቻ አድርጉ ዓለም ሁሉ ወደ አንድ አቅጣጫ የሚጮኸው የየራሱን ጉድ ለመደበቅና ለማረሳሳት መሆኑን በስፋት ተነጋገሩበት፡፡

"ኤ! ወዳላሰብነው ብሶት ገባን፡፡ ይልቅ የሚያስቀን አንድ ልንገርህ" አለ ዶክተር ለመሳቅ ብሎ ያነሳው ገጠመኙ እንዳለን እያናደደው መሆኑ ገብቶት ጨዋታቸውን ወደ መዝናናት ለመቀየር፡፡ እንዳለ ስሜቱ ባይለወጥም መስማማቱን ገለፀለት፡፡

"አንዱ፣ የኛ ጓደኛ ምን አረገ መሰለህ? ክርስቲያን ጉንደሬ ነው፡፡ አበባው ይባላል፡፡ አንድ ቀን ቤተክርስቲያን ሊሳለም ይሄዳል፡፡ እንደምታውቀው ባገራችን ጫማ ተደርጐ አይገባም፡፡ አበባው ሆዬ ታዲያ ያን የመሰለ ንጹህ ግቢ እንኳ በእግሩ ለመርገጡ ፈጣሪውን ይቅርታ እየለመነ ጫማውን አውልቆ በረንዳ ላይ ያስቀምጥና ይገባል፡፡ ፀሎቱን አድርሶ ሲመለስ ጫማ እሚባል ነገር የለም፡፡ እፍረትም ንዴትም እየተናነቀው በባዶ እግሩ መንገድ እንደጀመረ ሁለት የዛ አገር ጐረምሶች አየተሳሳቁ ወረወሩለት፡፡"

ዶክተር ራሱ በሚያወራው ከልቡ ቢስቅም እንዳለ ግን ሁለት ዓይነት ስሜት ነው የተሰማው፡፡ የኢትዮጵያዊው ሁኔታ ለፈገግታ ቢኮረኩረውም የሁለቱ ነጭ ጐረምሶች ተንኮል ግን አስቀድሞ ከተሰማው የዘረኝነት ጉዳይ ጋር ስላያያዘው አናድዶታል፡፡ ዶክተርን ለማስደሰት ያለልቡ ፈገግ አለ፡፡

ሲጫወቱ አምሽተው ዶክተር አብደላ እንዳለን ለእሁድ እርሱ ቤት እንዲያሳልፍ ቀድሚያ ቀጠሮ አስይዞት ተለያዩ፡፡



# 42

ጥቁር፡፡ ሐምሌ ሐምሌ የሚል ማለዳ፡፡ ድፍን አዲስ አበባ በጉም ታፍናለች፡፡

መኪኖች እንደምሽት ሁሉ መብራቶቻቸውን በረዥሙ ለቀው በዝግታ ነው የሚንቀሳቀሱት፡፡ -እንዳይጋጩ፡፡ የቦሌ ሠፈሩ ዶክተር አብደላ ቢጫማ ፔዦ አምስት መቶ አራት ሞዴል አቶሞቢሉን እያሽከረከረ ከሥራ በታው ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ደረሰ፡፡

ህክምና ለማግኘት ለሊት ሲወርድ ያደረውን ዶፍ ተቋቁመው በሆስፒታሉ አጥር ጥግ ተኮልኩለው ያነጉ ተመላላሽ ታካሚዎችና በሆስፒታሉ የተኙ ዘመዶቻቸውን ለመጐብኘት ካልገባን የሚሉ ጠያቂዎች እየተተራመሱ የመግቢያ በሩን አካባቢ አጨናንቀውታል፡፡ ዘበኞችን ይለምናሉ፡፡ ይለማመጣሉ፡፡ ባስ ሲላቸውም ይሳደባሉ ይመናጨቃሉ፡፡ በሆስፒታሉ ግቢና በህንፃዎቹ መተላለፊያዎችም ላይ ቁጥራቸው ትንሽ የማይባል ተመላላሽ ታካሚዎች ወዲያ ወዲህ እያሉ ነው፡፡

ዶክተር አብደላ ሁሉን እየታዘበ ወደ ቢሮው ገባና ኮቱን ሳያወልቅ ነጭ የሥራ ካፖርቱን ደረበ፡፡

"ዛሬ ደግሞ ቅዝቃዜው ሀይለኛ ነው፡፡" አለ፡፡

"እዡርዱይ ኢል ፌ ፍሯ" አለች ሲስተር ሲሳይ፣ የዶክተር አብደላ ረዳት ሀኪም በራሷ ፈረንሳይኛ እየሳቀች፡፡ በአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሴዝ የሦስተኛ ክፍል ተማሪ ስለሆነች በየአጋጣሚው ከዶክተር አንዳንድ አባባሎች ለመማር የምታውቃቸውን ቃላት ሰበብ ፈልጋ ትወረውራለች፡፡ አሁንም 'ዛሬ ይበርዳል' ማለቷ ነው በፈረንሳይኛ፡፡

"ዊ! ኢልፌ ፍሩዋ፡፡ ኢል ነፌ ፖ ሾ ሲስተር" 'አዎ ይበርዳል' የሚለው ቢገባትም በተጨማሪ የተናገረው ስላልገባት ፊቷን ጭምድድ አደረገች፡፡

"አዎን ይበርዳል አይሞቅም ነው ያልኩሽ፡፡ ነ. . .ፖ አፍራሽ መሆኑን ታውቂያለሽ ሾ ደግሞ ሴ አሽ አ ኢዩ ዴ ማስኩላን ሆኖ ሙቀት ማለት ነው" አለና አስረዳት ዶክተር፡፡

"ሜርሲ! እዚችው አንድ ቃል አወቅኩ ማለት ነው፡፡ 'ከመፍራት ማጉርናት' ትላለች አባዬ፡፡ ከመፍራት መሳሳት" አለች እያንዳንዷን ቃል በፈገግታ እጅባ፡፡

# 43

ለአንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ መንገደኞች ቦታቸውን ይዘው አውቶብሱ ሞተሩን ማሟሟቅ ጀመረ::

እንዳለ እህቱን በመሰኮት ተሰናብቶ ወደ ቤት እንድትሄድ ካደረገ በኋላ የማስታወሻ አጀንዳውን ገለጥ አድርጐ ሐምሌ ሃያ አራት ላይ የዕለቱን የመጀመሪያ ቀለም ጠብ አደረገ::

"ያለሁት አውቶብስ ላይ ነው:: ሰዓቱ አሥራ ሁለት ከአርባ ሰባት ደቂቃ ይላል:: ልትሸኘኝ የመጣችው እህቴን አሰናብቼ ይህን ማስታወሻ ጀመርኩ::"

"በሥራ አጋጣሚ አልፎ አልፎ ወጣ ብልም ወደ ወሎ ስሄድ የመጀመሪያዬ ነው::"

'ኧረ ደሴ ደሴ ገራዶ ገራዶ
አለቀልሽ ልቤ ተንዶ ተንዶ::'

"ዘፈኑ ሁሉ ደሴና ባቲ የሆነበትን ሚስጥር ለማወቅ፤ በተለይም በዘመነ ዛጉዌ የተቀረጹትንና ኢትዮጵያ የዓለምን ዓይን እንድትስብ ካደረጓት ቅርሶቿ ቀዳሚውን ሥፍራ የሚይዙትን የላሊበላ ገዳማት በዓይኔ ለማየት በጣም ጓጉቻለሁ:: ቸኩያለሁም:: የአካባቢውን ባህል እና ልማድ፣ መልክአ ምድራዊ አቀማመጡን ወ.ዘ.ተ. ካየሁና ካወቅኩ በኋላ ለዝግጅት አምዴ የሚሆን አዲስ ነገር ይገኜ ለመመለስ:: እግረ መንገዴንም መላዋ ኢትዮጵያን ለመጐብኘት ያለኝን ፍላጐት በትንሹ ለማርካት::

"አውቶብስ ተራ እንደልማዱ በተጓዦች፣ በሸኚዎች፣ በግቢው ሠራተኞችና በትላልቅ አውቶብሶች ተጨናንቋል:: ለማኞችና መንታፊዎች አዟሪዎችን ጨምሮ በህዝቡ መሃል ይሹለከለካሉ:: የእንባ መነጽር የደቀኑ ዓይኖች የተኮማተሩ ፊቶችና የሚውለበለቡ እጆች /ከሸኚዎችና ከመንገደኞች/ ይታዩኛል:: . . ."

ማስታወሻውን አቋርጦ ወደ ኋላው ዞረ::



"ባዳሜ ተነጥቆ ከአዳሜ መመጽወት
ዋ! የነፍስ ነገር ሆድ አያውቅ ኩራት::
አግኝታችሁ አትጡ ወገኖቼ ቀን አይጉደልባችሁ:: ኩራት ከንቱ"

አንድ ቁመናው ከሰውነቱ መፈርጠም ጋር ቱጃር ያስመሰለው ለማኝ ነው:: ተሳፋሪዎቹ ከንፈራቸውን እየመጠጡ ሳንቲም በብዛት ዘረጉለት:: እንደ ትኬት ተቀባይ ከኋላ ወደፊት እየሰበሰበ መጣ:: እንዳለም ለመምሰል ከኪሱ ሳንቲም አውጥቶ ሰጠ:: የቀደመው ለማኝ ሳይወርድ ሌላ ምጽዋት ጠያቂ መጣች:: ይችኛዋ ደግሞ ወፈፍ የሚያደርጋት ናት::

"አንተዬዋ አገሬን ውሰደኝ እስቲ?" አለች ሹፌሩን:: መልስ ሲነሳት ወደ አንዱ ተሳፋሪ ዞረችና ስጠኝ እንደማለት እጇን ዘረጋችለት::

"ከወደዱም አይቀር ይወዳሉ አምስት
ሁለቱን ለማታ ሁለቱን ለጧት
አንዱን ለውሃ ጥም ለኩለ ሌሊት" አለች በዜማ:: መንገደኞቹ በግጥሟ እየሳቁ መሃረብና ኪሳቸውን ዳበሱላት::

"ስጥቶ እማይሰለቸው ህዝብ!" አለ እንዳለ የአዲስ አበባን ህዝብ መጽዋችነት እያደነቀ:: ሴትዮዋ ቀሚስ ተብዬ ቡትቶዋን በእጇ ይዛ እንደ እስክስታም እያደረጋት ዘፈኗን ቀጠለች::

"አሃሃይ! አሃሃይ! አሃሃይ!
እንዴነህ እንዴነሽ አንባባልም ወይ
ሰው ከአባቱ ገዳይ ይታረቅ የለም ወይ::
አህህስ!
እህህስ!
እህህስ እህህስ እህህስ!
አይ ፍቅር
ሲያልቅ እያምር" አለችና ዘፈኗን አቁማ ሳንቲሟን መሰብሰብ ያዘች:: እቃ መጫኛውን ጠራርጎ የጨረሰው ዋሾፌሩ ረዳት ገባና እንድትወርድ አምባረቀባት::

❖

"ውረጅ እንሂድበት!"
"እሺ ጋሼ! አትቆጣ ታረጃለህ"

አውቶብስ ሙሉ ሳቀ:: እርሷ የነጠላዋን ትልታይ እየሰበሰበች ወረደች::

አውቶብሱ መናኸሪያውን ሲለቅ ዓይኖች ተከትለውት ዓይኖች

ቀርተውበት ነበር:: መሄድና መቅረት ተለያይተው ተፈላላጊ ዓይኖች እስኪጠፉ:: -የመንገደኞችና የሸኚዎች::

የአዲስ አበባን ግማሽ መሃል ለመሃል አቋርጦ በስተሰሜን ምሥራቅ ወጣ::-አውቶብሱ::

"አይ ፍቅር

ሲያልቅ አያምር" የለማኟ ዘፈን መቋጠሪያ ከነአነጋገር ስልቷ ደጋግሞ በህሊናው የደወለው እንዳስ የእርሱና ዳርምየለሽን መጨረሻ ዋቢ ይዞ ሲያሰላስል ቆየና፣ "ኤጭ! ምን የማልረባው ነኝ" በማለት ራሱን ወቀሰ::

ዳግመኛ ስለእርሷ ላያስብ የሚምለውን ያህል በየአጋጣሚውና በየምክንያቱ ወደኋላ የሚመለስ ህሊናውን ናቀው:: ጐን ለጐን በመቀራረብ ስሜት እያወሩ የሚሄዱ ወይንም በየመዝናኛ ቦታዎች ተቀምጠው አፍ ለአፍ ገጥመው የሚንሾካሾኩ፣ ሌሎችም በእርሱ ግምት ፍቅረኛሞች የሚመስሉ ሁሉ ዳርምየለሽን ይጠሩበታል:: -በሀሳብ:: ስለ ፍቅርና ፍቅረኛ በተነሳበት ሁሉ ትመጣበታለች:: አሁንም የለማኟን ግጥም ምክንያት አድርጐ ስላሰባት ራሱን ወቅሶና ሰድቦ ከዚያ በኋላ ሁለተኛ በክፉም ሆነ በደግ ላያስታውሳት እንደሰመደው በልቡ ማለ:: እንዲረሳት ብሎም በመንገዱ ግራና ቀኝ የለገዳዲና አካባቢዋን ሜዳ እስከ አድማስ መጋጠሚያ በዓይኑ እያማተረ ሳይደነቅ መደነቅ ያዘ:: -ከሀሳብ ለመሸሽ::

አውቶብሱ ከአዲስ አበባ፣ እንዳስም ከዳርምየለሽ ሀሳብ እየሸሹ የሰንዳፋን፣ የአሌልቱን፣ የሸኖን፣ የደብረብርሃንንና ሌሎችንም ጥቃቅን ከተሞች መንገድ ሸምጠው ጣርማ በር ደረሱ:: የጣርማ በር ፍተሻ ከሌሎች ካለፏቸው ፍተሻ ጣቢያዎች ሁሉ ጠበቅ ያለ ነው:: እንዳለ የተሳፈረበት አውቶብስ ተራ እስኪደርስ ወዲያውም ለፍተሻ መውረድ ስላለበት ወረደ:: ከመንገዱ በስተግራ በኩል እየተናፈሰ በርቀትና በቅርበት የሚገኙትን የእርሻ ማሳዎች፣ የአካባቢውን መልክዓምድራዊ አቀማመጥና የልምላሜውን ውበት በእርካታና በደስታ አደነቀ::

ወደኋላው መለስ ብሎም ተቃራኒውን አቅጣጫ /የመንገዱ ቀኝ/ ሲመለከት ክብድ ያለ ኮረብታ መሰል ጉብታ ወደ መንገዱ እሚገለበጥ መስሎ ታየው:: ብዙም ስላልሳበው ዕይታውን ወደ ተጓዦችና ኬላ ጠባቂ ፖሊሶች ትርምስ መለሰ:: ሻንጣ ይበረበራል:: መኪኖች ይታሰሳሉ:: ሰው ልብሱ ወልቆ ቆዳው መላጥ እስኪቀረው ይታሻል:: የቀበሌ መሸኛና መታወቂያ ያልያዘ ለብቻ ተሰይቶ የፖሊሶቹ ግልምጫና ስድብ እየወረደበት ይመረመራል:: ሰብአዊ መብቴን ብሎ መከራከር የለም:: በምትኩ ልመና ልምምጥ ካመችም ዘወር አርጐ ምናምን ወሸቅ ነው:: በተረፈ መብቴን ብሎ መከራከር ጥፊና ስደፍ ያመጣል::



"ሰው ባገሩ!" አለ እንዳስ ለራሱ ተገርሞ:: አንዱን የሀያዎቹ ቤት ወጣት፣ ፖሊሶች በስድብና በድብደባ ሲቀባበሉት አስተውሎ:: ማንም ሊያስጥለው ወይንም ሊገላግለው የሞከረ የለም:: ሲበቃቸው ግማሽ ገጽ ወረቀቱን ፊቱ ላይ ወርውረው እንዲሄድ ፈቀዱለት:: እንዳስ የሚባባሉትን ባይሰማም በርቀት እንደታዘበው ውዝግቡ በመሸኛ ወይንም በመታወቂያ የተነሳ መሆኑን ገምቷል::

በመንግሥትም ሆነ ሕዝባዊ ድርጅቶች አገልግሎት ለማግኘት-መታወቂያ:: ከበር ለመግባት -መታወቂያ:: ከቦታ ቦታ ስመዘዋወር-መታወቂያ፣ መሸኛ:: ለምን አስፈለገ? በገዛ ሀገር ለመዘዋወር ኢትዮጵያዊ ምስልና ቁመና አይበቃም ይሆን? ድብደባና ግልምጫን ምን አመጣው? መልሱ እርሱን የማይመለከት ጉዳይ:: መታወቂያውን አሳዩና ተፈትሾ ወደ ራሱ አውቶብስ ገባ::

አውቶብሱ ረጅም መብራቱን ለቅቆ ዋሻውን ዝግ ብሎ መሹለክ ሲጀምር እንዳስ ሰዓት ያዘ:: አንድ ደቂቃ ከአምሳ ስድስት ሰከንድ:: ሌሎች ሁለት ብርሃናማ አጫጭር ዋሻዎችን አለፈና ደብረሲናን ቁልቁል ብቅ ጥልቅ እያደረገ ሲጠማዘዝ ወረደ:: -አውቶብሱ:: እንዳስ ከሰማይ ወደ ምድር እንደመውረድ ያህል የመንገዱ በብልሃት መሠራት እና የደብረሲና ከጣርማ በር በመንገድ መገናኘት አስደነቀው::

"ምሳ እንብላ!" አለ ሹፌር መኪናውን ጥግ አስይዞ:: "አሁን ለስድስት ሩብ ጉዳይ ነው ስድስት ከሩብ እዚህ" አለ በማስጠንቀቅ::

## 44

ደሴ ከገባ አራት ቀን ሆኖታል:: ቀን ቀን የመጣበትን ሥራ ሲከታተል ይውላል:: ከሥራ መልስ መሸት እስኪል ከተማዋን ከዳር ዳር እየዞረ ያካልላታል:: የዳውዶን፣ የአራዳን፣ የአረብና በርበሬ ገንዳን፣ የመናኸሪያና የአገር ግዛት፣ የፒያሳን፣ የሮቢትን አካባቢዎች እየተዘዋወረ ተመልክቷል:: ማታዎቹንም በአንድ ምሽት ሁለት ከዛሬ ሌላ በስድስት ሆቴሎችና ቡና ቤቶች አሳልፏል:: አሁንም በፒያሳና መናኸሪያ መሀል ቆም እያለ ሲንሸራሸር ቆየና ሊጨልም ስማዩ ሲጠቋቁር ከአንዱ ሆቴል ጐራ አለ::

ራቱን በልቶ ወደ ቡና ቤቱ ወጣና ቢራ አዘዘ:: ጆሮው እርሱ በተቀመጠበት ማዕዘን ከፍ ብሎ ከተሰቀለው ስፒከር በሚወጣው የቆየ ሙዚቃ ተጠለፈ:: ድምጹ የምኒልክ ወስናቸው ይመስላል:: ዘፈኑን ግን ከዚያ ቀደም ሰምቶት አያውቅም::

"ጊዜ ቢያሳየኝም ጥፋትሽን አጉልቶ
እኔ እንዳንቺ አልሆንም አልጠላሽም ከቶ"

ከቶ ስቃይ:: የዜማውና የድምፃዊው ለዛ ቢማርከውም ግጥሙ በጆሮው አልፎ ልቡ ላይ ወጋው:: የቆየ ቁስሉን ነካበት::

ግን ለምን? ዘፈኑ የሚያወራው ስለአለመጥላት:: ከዳርምየለሽና ከእርሱ ጋር ምን አገናኘው?

ካልተገናኘ ታዲያ ለምን መጣችበት? አሁንም ተስፋ አልቆረጠም ማለት ነው? አሁንም ይወዳታል ማለት ነው?

በፍጹም:: በፍጹም ጥላቻው ከፍተኛ ነው::

ታዲያ ለምን አይረሳትም? ስለፍቅር ሲዘፈን እንዴት የጠሉት ትዝ ይላል?

እርሱ ከሀሊናው ቢሟገትም ያልተደፈነ ጆሮው ዘፈኑን ማስገባቱን



አልተወም::

"በፍቅርሽ መንምኖ ያ ሁሉ ዘመኔ
አሁን ብትተይኝ አልጠላሽም እኔ::"
የበኑ ይሁን የከፉ ለራሱም ግራ እስኪገባው ግጥሙ አጥንቱን ሰብሮ ገባ::

"ለምን አልጠላት? በቅንነቴ በእምነቴ ላይ ስትጫወትበት" አለ በዘፈኑ የወረረውን ስሜት ተቃውሞ:: ሕናም ተሸቀንጥሮ ወጣ:: ከዘፈኑ መሸሹን እንጂ መጠጥ ማዘዙን ረስቶታል:: እንደወጣ ሲጋራ ለኮሰና ደጋግሞ ሳበው::

"ለውዬው ያመዋል እንዴ!" አለች አስተናጋጇ የታዘዘችውን ይዛ ስትመለስ እርሱ ሲወጣ አይታ:: በስተቀኙ ደሴ ላይ ሊወድቅ መስሎ የቆመውን የጦሳ ተራራ እየገላመጠ ወደ ፒያሳ ወጣ::

"ለምን አትተወኝም? ለምን አልረሳትም? በደልን ተቀብሎ 'አልጠላሽም' ብሎ ነገር:: ዘመናትን በፍቅር አመንምኖ 'ብትተይኝም አልጠላሽ' ብሎ ፈሊጥ ዘፈን ነው እንጂ እውነት መሆን አይችልም" አለ ከሀሊናው መሟገቱን ቀጥሎ::

"ኪነት የገሀዱ ህይወት ነፀብራቅ ናት:: ግጥም ቢገጠም፣ ልቦለድ ቢጻፍ፣ ተውኔት ቢተወን፣ ስዕል ቢሳል፣ ሁሉም ሁሉም ከገሀዱ ዓለም እውነትና እምነት አይወጣም" አንድ የዓምዱ ተሳታፊ ልክለት በአንድ ወቅት ለንባብ ያበቃው አባባል ነው:: ያን ጊዜ 'እውነት' ብሎ ነበር አሁን ግን ከዚህ ዘፈን ጋር አባባሉ ሊታረቅለት አልቻለም::

እንዲያውም በጉዳዩ ላይ ሲያሰላስል ጥላቻው እንደ አዲስ ገነፈለበት:: የዘፈኑ ግጥም ያመጣበትን የትዝታ ስሜት ለመቋቋም ጥላቻውን አጠነከረ:: እንዳቀፈችበት አቅፎ እንደለወጠችው ለውጦ በአካል ባይሆን በመንፈስ ሊበቀላት እንደሚገባው ለመጀመሪያ ጊዜ ወሰነ:: በስመ ሴት እርም ብሎ መራቁ ራሱን መበደል መስሎ ታየው:: አዲስ ሴት የመሻት አዲስ ስሜት ተጠናወተው:: ግን ማንን?

"ማንም ትሁን ብቻ ሌላ ሴት"

ሸዋ በር መታጠፊያ ሲደርስ በስተግራ አንዲት መጠጥ ቤት አየና ዘው ብሎ ገባ:: መጠጥ ቤቷ ጠባብ ብትሆንም ከመጠጥ መደርደሪያው መሀል ካለው ባለ ከፍተኛ ኃይል ቴፕሬከርደር የሚወጣው ሙዚቃ ጩኸት የእርሷን አስር ጊዜ ለሚሰፋ አዳራሽ ይበቃል:: ከመደርደሪያው ራስጌ ግድግዳው ላይ ሀረግ መሰል የልደት መብራት ቦግ ድርግም እያለ አላፊ አግዳሚውን ይጠቅሳል:: በባንኮኒው ትክክል ኮርኒሱ ላይ የተሰቀሉት ብልጭልጭ ጌጦችም፣

እንዳለ በነገረችው ታሪክ ልቡ ተነክቷል:: በፍቅር ሳቢያ ቤተሰቧን፣ በህይማኖት ሳቢያ ፍቅሯን አጥታ ይህን ወደ መሰለው ጣዕም የለሽ የራስን መሸጥ ህይወት መገፋቷ አሳዘነው::

እነርሱ እያወሩ ሳይታወቃቸው ሰዎች እየበረከቱና ጫጫታው ከክፍሏ አቅም በላይ እየሆን መጣ::እንዳለ ዘርትሁንን አምስት ሰዓት ላይ መጠጥ ቤቱ ሲዘጋ ሊወስዳት ተስማሙና ከመጠጡ ሂሳብ ሌላ ሀያ ብር አስጨበጣት:: ወደአረፈበት ሆቴል ሲሄድ ድል እንደቀናው ጉበዝ እግሮቹን በፍጥነት እየወረወረ ነው::

"ማንም ትሁን ሌላ ሴት!"

♣ ♣ ♣

የእጅ ሰዓቱ ለአምስት ሃያ አምስት ጉዳይ ይላል:: እንደገባ እግሩን አንጠልጥሎ በተዘረጋበት ከአንድ ሰዓት በላይ አንቀላፍቶ መንቃቱ ነው:: ካመሸበት መጠጥ ቤት ሴት ሊያመጣ መዋዋሉን አስታወሰና በመሄድና በመቅረት መሃል እመነታ:: አሁን ተረጋግቷል:: ቅድሙንም በመጠጥ ሳይሆን በነገር ብዛት፣ በፍቅርና ጥላቻ የህሊና ግጭት ነበር የሰከረው:: እናም አድራጎቱ ፀፀተው::

"ማን ለምን? የማንን እምነት አጉደለ? ማን የሚላት አስችውና ነው? ሳጤው እንዳለ ሴት ይዞ ቢያድር ምንድነው ነውሩ?"

"ሴት ቢሉ ሴት ሁሉ አንድ አይደለም'

"እንዴት? ዘርትሁንምኮ ልቅም ያለች ቆንጆ ናት::"

"ቆንጆ ብትሆን ላሰብከው የሴትን በሴት መተካት በቀል የምትሆን አይደለችም::"

"ለምን?"

"ያንተ አይደለችማ"

"ታዲያ የማን ናት?"

"የማንም:: ገንዘብ ለቋጠረ ሁሉ ናት"

"ሌላ ሴት:: ትቅርብኝ" አለ እንዳለ የህሊናውን ሙግት ወደ አንድ አቅጣጫ እየቋጨ::

አዎ ትቅርበት:: ዘርትሁን የማንም ናት:: ዳርምየለሽን መጥላትና መርሳት ቢኖርበትም በዚህ መልክ አይደለም:: ሌላ ሴት፣ ብር ቆጥሮላት ሳይሆን ፈቅዳውና ፈቅዶ የሚቆራኛት:: ገዝቶ ሳይሆን ተግባብቶ የሚወድቅላት:: -ሌላ ሴት:: ለመኖር ሳይሆን፣ ለማስመሰል ሳይሆን ስሜቷ ሲፈቅድ የምትፈካ:: -ሌላ ሴት:: ከዚያን ጊዜ በኋላ በዳርምየለሽ የተቆለፈ ልቡን ከፍቶ አዲስ እንግዳ ሊቀበልበት ለራሱ ቃል ገባ:: ደጋግሞ "ሌላ ሴት" እያለ ልብሱን አውልቆ ተኛ::



# 45

ሰኔ ሲጋመስ ጀምሮ ድፍን ሐምሌን እኝኝ እንዳለ ሲያለቅስና ሲጨቃጨቅ የመጣው ክረምት ነሐሴንም አልደከመው:: እንዳያያዙ ለመስከረምና ለጥቅምትም የሚበገር አይመስልም:: ዘለዓለም ዓለምን ክረምት ለማድረግ የተነሳ ነው የሚመስለው::

"እንደዘንድሮ ሆኖ አያውቅም"
"ዘንድሮ መቼም የተለየ ነው::"

ይላል የያዘውን ዘመን 'ዘንድሮ' እያለ በክፉም ሆነ በደጉ ከአሳለፋቸውና ወደፊት ከሚመጡት ዘንድሮዎች ማስበለጥ የሚቀናው የአዲስ አበባ ነዋሪ::

ዝናብ አስቸገረ -ዘንድሮ

ፀሐይ ገረረ -ዘንድሮ

ጨው ተወደደ -ዘንድሮ

በርበሬ ረከሰ -ዘንድሮ

ምንም ምንም ሆነ 'ዘንድሮ' ማለት ይቀናዋል:: ክረምት እንደሚዘንብ፣ በጋ እንደሚጠርር፣ ወቅትና ዘመን ጠብቀው የሚከሰቱ ሌሎችም ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ አይቀሬ ክስተቶችን እያወቀ በዘመን አመካኝቶ ያማርራል:: በዘመን አመካኝቶ ይጽናናል::

❦

ዘንድሮም እንዳለፉት ብዙ ዘንድሮዎች በርካታ መወቀሻዎቹን ይዞ ሊገባደድ የመጨረሻ ወሩን ይዟል:: በተለይ ክረምቱ፣ በጋው በየስርቻውና በየመንገዱ ዳር ሰብስቦና አጠራቅሞ ያቆየውን የቆሻሻ መዓት እያግበሰበሰ በየአስፋልቱ ሲያጋጨው፣ መልሶም ሲጠርገው፣ አንዱን አጽድቶ ሌላውን ሲያቆሽሽ የፀዳለትም የቆሸሸበትም እኩል በአድናቆትና በምሬት 'አይ ዘንድሮ' እንዳሉት፣ የመንደር መራመጃ የሥራ መላወሻ አሳጥቶ "ኤጭ እንዳው ዘንድሮስ!" እየተባለ በመግፋት ላይ ነው:: -ክረምቱ::

ጀመረች::

"ምነው አመመሽ እንዴ?" አለቻት ኑንሸ ካጠገቧ ተቀምጣ ዳንቴል ለመሥራት ክር በኪሮሽ ታፍተለትል ነበር::

"እም! ኡፍ . . .ፍ! ወየው አ . . . እ! መሞቴ ነው" አለችና ከተቀመጠችበት እንደምንም ተነስታ የእጆቿን መዳፎች አቆላልፋ የአልጋው ግርጌ እንጨት ላይ በማሳረፍ ጉልበቷን ፈርከክ አድርጋ ቁጢጥ አለች:: ጭንቅላቷን እጆቿ ላይ አስደገፈች:: ታቃስታለች ታምጣለች::

ኑንሸ በእህቷ ሁኔታ ተደናግጣ እናቷን ጠራቻቸው::

"እንዴት ነው የሚያደርግሽ?" አሉ በቁማቸው ቁልቁል እያስተዋሏት:: የሚሰማትን ሁሉ ዘርዝራ ነገረቻቸው::

"ምጥ መሆኑ ነው:: መቼ ነው የጀመረሽ?"

"በጣም የተሰማኝ አሁን ነው:: እህ! . . . ኡፍ. . .!" ደጋግማ በረዥሙ ትተነፍሳለች::

"ምጥ ነው:: ቀንሽ ደርሶ የለም:: ከህዳር ስድስት ሲቆጠር ዘጠኝ ወርሽ ያለፈው እየሰብ እኮ ነው:: እንዲያውም ስድስት ቀን ተላልፏል:: አይዞሽ! አንቺ ያችን ትንሿን ፍራሽ አምጭና ያንን የልብስ ሳጠራ አንስተሽ አንጥፊላት" አሉ ኑንሸን እያዘዙ::

ሰባት ሰዓት ቀለብተኞቹ ሲወጡላቸው ተመልሰው ወደሷ መጡ:: ሁለቱ እህቶቿም ጭንቀቷን ተጨንቀው የሚይዙት የሚጨብጡት አጥተዋል:: ስታለቅስ ያለቅሳሉ:: ስታቃስት በመንፈስ ያቃስታሉ:: ወይዘሮ ብዙ ግን ምጧ ሳይሆን ያስጨነቃቸው የማዋለዱ ጉዳይ ነው:: እርሳቸው አያውቁበትም:: ለራሳቸውም ቢሆን ከኑንሸ በላይ ያሉትን ልጆቻቸውን ያዋለዷቸው ሚጿ የቀኛዝማች ሚስት ወይዘሮ አይቼሽ ነበሩ:: ኑንሸንም ሆስፒታል ነው የወለዷት::

ምን እንደሚያደርጉ ጨንቋቸዋል:: ሆስፒታል እንዳይወስዷት ከአራት ወር በላይ የደበቁት ጉዳቸውን ሰው ሊያይባቸው ሆነ:: እቤት እንዳትወልድ ራሳቸው ማዋለድ አይችሉም:: አዋላጅ እንዳይጠሩም ያው የፈሩት ሚስጥር የመውጣት ጉዳይ ከበዳቸው::

ይህንን ሳያስቡ ሲደብቁና ሲጨነቁ መኖራቸው ከንቱ ድካም ሆኖ ተሰማቸው:: በራሳቸውም ተናደዱ:: ወሳዲት አምላካቸውን አማረሩ:: ጣጠኛ ልጃቸውን በልባቸው ረገሙ::



ዳርምየለሽ ምጡ እያፋፋማትና እየበረታ መጣ:: ታለቅሳለች:: ትንበረከካለች:: ትቀመጣለች:: ትንቆራጠጣለች:: ኑንሸና አስናቀችም ግራና ቀኝ ደግፈዋት አብረው ያምጣሉ:: አብረው ያቃስታሉ:: አብረው ያለቅሳሉ::

"እማዬ ምነው እስከትሞት ነው እንዴ የምታያት?" አለቻቸው አስናቀች ጭንቀቷ ሲብስባት:: እናቷ ሚስጥር ለመጠበቅ ሲሉ እንዲያ እየተሰቃየች በዝምታ ማየታቸውን ጭካኔ አድርጋ በመታዘብ::

"ታዲያ ምን ላድርግ ልጄ?" አሉ ትክዝ እንዳሉ::

"እንዴ! ሀኪም ቤት ይዘናት እንሂድ እንጂ:: ገና ለገና ሰው እንዳያያት ታፍና ብትሞትስ?" አለቻቸው የልቧን አውጥታ::

"ሀኪም ቤት መውሰዱን መች አጣሁት:: ከሰው ዓይን ብትገባ የሚያሳፍር ነገር ሆኖብኝ እንጂ::"

"ይዩአታ! ግፋ ቢል ወለደች ነው:: መውለድ ደግሞ በእርሷ አልተጀመረም:: በሠፈራችን ማን ያልወለደ አለ?"

"ታዲያ ጥሩ አደረጉ ያለ ማን ነው? በየቡናውና በየልቅሶው ቤት አንዱ በአንዱ እየሳቀና እየተቸ እናቶቻቸው በልጆቻቸው መንዘላዘልና ዲቃላ ማቀፍ ሲያፍሩ እንጂ ማንኛቸው ሲኮሩበት አየሽ? 'የእርሷ ልጅ ጨዋ ናት!' . . . 'መውለድ እንደሷ ነው!' ተብዬ በኩራሁብትና በተከበርኩብት ሠፈር መዋረዱን አልፈልግም:: ደግሞምኮ ለራሷም ነው:: ነገ ወልዳ ስትነሳ መቆሚያ የላትም:: ባል ቢመጣላት እንኳ ልጅ አላትን ሲሰማ ይሸሻል:: ልጃገረድነቱ ቢቀር ልጅ ያላትን ማን ይፈልጋል::"

"ታዲያ ምንድነው መፍትሔው?" አለች አስናቀች በእናቷ አይበገሬነት ጭንቀቷና ብስጭቷ ተባብሶ::

"ምን አውቃለሁ" አሉና እንባቸውን እርግፍ እርግፍ አደረጉ::